ምዕራፍ 15

ምሥጢረ-ሥጋዌ

ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያዎች የክርስትና ዘመናት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላትና የሐዋርያትን ትውፊት አጥንታና በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ የሚከተለውን የተረጋገጠ ትምህርት ገለጸች፡፡

1. የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ፣ ወልደ እግዚአብሔር፣ ማለትም የቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ አካል መለኮታዊ ባሕርይውን ሳይ ተው ሰብአዊ ባሕርይንም ለበሰና ሰው ሆነ፡፡ ይህም ማለት ዘለዓለማዊው የአምላክ ልጅ ንጹሕ በሆነው የማርያም ማሕፀን ውስጥ ከተፈጠረው ሰውነት (ሥጋና ነፍስ) ጋር ተዋሐደ፡፡ ይህ በአምላክ ባሕርይና በሰው ባሕርይ የቆመው አካል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ይህ ምሥጢር ደግሞ «ምሥጢረ-ሥጋዌ» ወይም «ትስብእቱ» ይባላል፡፡

2. ጌኢክ. የቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ አካል ስለ ሆነ ከአብ ጋር እኩል ነው፡፡ ምንም እንኳን በሰብአዊነቱ (በነፍስና በሥጋ) የተፈጠረ ቢሆንም በመለኮቱ ከዘለዓለም ጀምሮ ከአብ ጋር የ ነበረ ነው፡፡ «ብርሃን፣ ከብርሃን፣ እውነተኛ አምላክ ከእውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ» አምላክ ነው፡፡ አርዮስ ይህን ትምህርት በመቃወሙ የተሳሳተ መናፍቅ ሆነ፡፡ አርዮስ «ወልደ አምላክ ከዓለም በፊት ተፈጠረ እንጂ አምላክ አይ ደለም» ብሎ ስለ ሰበከ እ.ኤ.አ. በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ ላይ በተሰበሰቡት 318 ርቱዓነ ሃይማኖት (አቡኖች) ተወገዘ፡፡

3. ጌኢክ. ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው፣ ምክንያቱም እርሱ የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ አለው፡፡ እነዚህ ሁለ ት ባሕርያት ደግሞ በአንድ አካል የሚጠቃለሉ ናቸው፣ ማለ ትም ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብና የእግዚእትነ ማርያም አን ድ ልጅ ነው እንጂ ሁለት የተሰማሙ ልጆች አይደለም፡፡ ምክ ንያቱም የኢየሱስ ሰውነት ብቻውን እኔነት (PERSONALITY) የለውም፡፡ ይህንን ትምህርት በመቃወም የተሳሳተው መናፍቅ ንስጥሮስ ነው፡፡ እርሱ፣ «በኢየሱስ ውስጥ ያሉት ሁለት ባሕርያት በአንድ ላይ እንደ ተጋጠሙት ሁለት ልጆች ነው፣ አንዱ የአብ ልጅ ነው፣ አንዱ ደግሞ የማርያም ልጅ

ነው» ብሎ ስለ ሰበከ እ.ኤ.አ. በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ ላይ ተወገዘ፡፡



የአምላክ ልጅ በማርያም ማሕፀን ውስጥ አድሮ ሥጋ ለበሰ

አስተውል

እንደ ንስጥሮስ አስተሳሰብ ማርያም የሰብአዊው ልጅ እናት ብቻ ናት እንጂ የመለኮታዊው ልጅ እናት አይደለችምና የአምላክ እና ት ልትባል አትችልም፡፡ በኤፌሶን ጉባኤ ላይ የተሰበሰቡት አቡኖች

ነው» ብሎ ስለ ሰበከ እ.ኤ.አ. በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ ላይ ተወገዘ።



የአምላክ ልጅ በማርያም ማሕፀን ውስጥ አድሮ ሥጋ ለበሰ

አስተውል

እንደ ንስጥሮስ አስተሳሰብ ማርያም የሰብአዊው ልጅ እናት ብቻ ናት እንጂ የመለኮታዊው ልጅ እናት አይደለችምና የአምላክ እና ት ልትባል አትችልም። በኤፌሶን ጉባኤ ላይ የተሰበሰቡት አበ-ኖች

ግን ማርያም ወላዲተ-አምላክ (የአምላክ እናት) መሆኗን ገለጹ። ምክንያቱም እርሷ የወለደችው ሕፃን የሰውን ባሕርይ የለበሰ አምላክ ነው።

4. ሰብአዊ ባሕርይና መለኮታዊ ባሕርይ በአንድ አካል ውስጥ ተዋሕዶው ስላልተቀላቀሉና ስላልተደባለቁ ከሁለቱ አንዱ ባሕርይ እንኳን አልጠፋም። ይህንን ትምህርት በመቃወም የተሳሳተው መናፍቅ አውጣኪ ይባላል። አውጣኪ «አንድ ጠብታ ወተት በ ውቅያኖስ ውሃ ውስጥ ተቀላቅሎ እንደሚጠፋ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስም የሰው ባሕርይ ከአምላክ ባሕርይ ጋር ስለተቀላቀለ ጠፍቷልና ኢየሱስ መለኮታዊ ባሕርይ ብቻ ነው ያለው» ብሎ ስለ ጸና ይህ ትምህርቱ ኢ.ኤ.አ. በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ በ630 አቡኖች ተወገዘ።

5. ጌ.ኢ.ክ. ሁለት ባሕርይ ስላለው፣ ሁለት ፈቃድም አለው (ምክንያቱም ፈቃድ የባሕርይ ውጤት ነውና) ይህ ሁለት ፈቃድ ግን በፍጹም ስምምነት ነው የሚካሄደው (ሉቃ.22፡ 42)። ይህንን ትምህርት በመቃወም የተሳሳተው አቡነ ሰርግዮስ ነው። እርሱ፣ «በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ፈቃድ ብቻ ነው ያለው» ይላል። ስለዚህ ኢ.ኤ.አ. በ680 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ላይ ትምህርቱ ተወገዘ። እርሱ ግን አስቀድሞ ሞቶ ነበር።

አስተውል

1. ከላይ የተመለከትነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ክርስቶስ በ ሁለት ባሕርያት የቆመ አንድ የቅድስት ሥላሴ አካል መሆኑን ያ ስረዳናል። እኛ ድኅነትን ልናገኝ የቻልነው ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ስላለው ነው፣ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ ቢኖረው ኖሮ ድኅነታችን ከንቱ በሆነ ነበር፣ ለምሳሌ እንደ አውጣኪ አስተሳሰብ ክርስቶስ መ ለኮታዊ ባሕርይ ብቻ ቢኖረው ኖሮ ሊሞትልን ስለማይችል ድኅነት ባላገኘንም ነበር። እንዲሁም እንደ አርዮስና እንደ ንስጥሮስ አስተ ሳሰብ ሰብአዊ ባሕርይ ብቻ ቢኖረው ኖሮ የክርስቶስ ሞት እንደ ማንም ተራ ሰው ሞት በሆነ ነበርና ከቶ ባልጠቀመንም ነበር። ምክንያቱም ማንም ተራ ሰው ወይም መልአክ ቅዱስ ሚካኤልም ቢሆን መንግሥተ-ሰማይን ሊከፍት አይችልምና። ስለዚህ ትክክለ ኛውና ቀናው ትምህርት «ሁለት ባሕርይ በአንድ አካል» የሚለው ነው።

2. የጌ.የኢ.ክ. ሞት በሰብአዊነቱ ብቻ ነው፣ በአምላክነቱ ሊሞት አይ ችልምና። (አምላክ አይሞትም)። «ክርስቶስ በሥጋ ሞተ» (1ጴጥ.3፡ 18)። የሞቱ ዋጋ ግን ከመለኮቱ ይገኛል። የተሰቃየው አምላክ ነውና የሕማማቱ ዋጋ ወሰን ስለሌለው የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ኃጢአት ሊደመስስና ቁጥር የሌላቸውን ሕዝብ ሊያድን ይችላል።

ጌ.ኢ.ክ. ማን መሆኑን የሚገልጹልን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት

መጽሐፍ ቅዱስ ጌ.ኢ.ክ. በእውነት አምላክና ሰው መሆኑን ይገልጽ ልናል። አሁን የሚያስፈልጉንን ጥቅሶች እንመልከት።

ሀ) ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው

ጌ.ኢ.ክ. በስሙ ብዙ ተአምራትን በማድረጉ አምላክ መሆኑን አሳየ፣ ምክንያቱም የዓለምን ኃይሎች ማዘዝ የሚችል አምላክ ብቻ ነው፣ ማዕ በልን ጸጥ ማድረግ የሚችል አምላክ ብቻ ነው፣ ሙታንን የሚያስነሣ፣ ሕመማንን የሚፈውስና ኃጢአትን የሚደመስስ አምላክ ብቻ ነው። ይህንን ሐቅ አይሁዶችም ያውቁት ነበር። (ማር.2፡ 6)። የሰውን ልብና ኩላሊት የሚመረምር (የሰውን አሳብ ማወቅ የሚችል) አምላክ ብቻ ነው (1ሳሙ.16፡ 7፣ ማቴ.9፡ 4)። ጌ.ኢ.ክ. እነዚህን ሁሉ ድንቅ ነገሮች ስለ ፈጸመ አምላክ ነው። ሰዎች አምላክነቱን እንዲያምኑ ሥራዎቹን አሳያቸው። «በእኔ እንኳ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ» አላቸው (ዮሐ.10፡ 38)

በቃላቱ ስለ መለኮቱ ተናግሯል፣ ማለትም ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል መሆኑን ገልጿል። «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ.10፡ 30)። «አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል፣ እኔም እሠራለሁ» (ዮሐ.5፡ 17)። «አብ የሞ ቱትን እንደሚያስነሣና ሕይወትን እንደሚሰጣቸው፣ ወልድም እንዲሁ ለፈለገው ሰው ሕይወትን ይሰጠዋል» (ዮሐ.5፡ 21)። በእነዚህ በጠቀስና ቸው ጥቅሶች ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል መሆኑን ገለጸ። ስለዚህ ከአብ ጋር እኩል መከበር ይገበዋል። ምክንያቱም «ወልድን የማያከብር፣ ወልድን የላከውን አብንም አያከብርም» ብሏልና (ዮሐ.5፡ 23)።

አይሁዶች ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል መሆኑን በገለ ጻላቸው ጊዜ ሊገድሉት ወሰኑ፣ «እግዚአብሔር አባቴ ነው። በማለቱና ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከሉ ሊገድሉት ፈለጉ» (ዮሐ.5፡ 18)። በቀያፋ ፊት ቀርቦ «የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ» ሲል (ማቴ.26፡

64) በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ገለጸ። ምክንያቱም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን የሁሉም እስራኤላዊ ዕድል ነበር፣ አሁንም ክርስቲያኖች በሙሉ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፣ ግን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አይደሉም። በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነው። ክርስቶስ እንግዲህ በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነው። ምክንያቱም የእርሱ መለኮትና የአባቱ መለኮት አንድ ነው (ልዩነት የለውም)። ምንም እንኳ ኢየሱስ ሞት እንደፈረዱበት ቢያውቅም ይህን ሐቅ ሳይገልጸው አልቀረም።

ሐዋርያት ክርስቶስ አምላክ መሆኑን በሚከተሉት ጥቅሶች ገልጸውታል።

1ዮሐ.5:20 «ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው»።

ዕብ.1: 6 «እግዚአብሔር የበኩር ልጁን ልኮ ወደ ዓለም ሲያስገባ፣ 'የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይስገዱለት' ይላል» ይህም ማለት ክርስቶስ ከሁሉም መላእክት፣ ከሚካኤልም ጭምር በጣም እንደሚበልጥ፣ ኧረ እንዲያውም ፍጡር አለመሆኑን ይገልጻል። ምክንያቱም ለፍጡር ልንሰግድለት አንችልም። ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ ነው።

ቆላ.1:15 «ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው። እርሱ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው። ምክንያቱም በሰማይና በምድር ያሉት፣ የሚታዩትና የማይታዩት፣ የሰማይ ኃይሎችና ገዥዎች፣ አለቆችና ባለሥልጣኖች (መላእክትና ሊቃነ-መላእክት) ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በእርሱና ለእርሱ ነው»። ይህ ጌ.ኢ.ክ. ከመላእክት እንደሚበልጥ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪያቸው መሆኑንም ይገልጻል። ስለዚህ ክርስቶስ አምላክ ነው።

ለ) ጌ.ኢ.ክ. ሁለት ባሕርይ አለው።

የጌ.የኢ.ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ በሚከተሉት ጥቅሶች ይገለጻል።

ዮሐ.1:1፣ 18 «ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ።... በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድ ልጁ...» ይህም ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ሳይፈጠር ከዘላለም ጀምሮ ከእግዚአብሔር አብ ስለ ተወለደ የአምላክ ባሕርይ አለው። (ክአምላክ የሚወለድ አምላክ ነው)።

ዮሐ.1:14 «ቃል ሥጋ ሆነ» ማለት ወልደ እግዚአብሔር አምላክነቱን ሳይለቅ ሰብአዊነትን ስለ ጨመረ ሰብአዊ ባሕርይም አለው። ስለዚህ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ፣ ማለትም መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርይ አለው።

ፊልጲ.2:6 «ክርስቶስ የመለኮት ባሕርይ አለው ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደ ያዘ መቅረት አልፈለገም። ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ አገልጋይ መሆንን መረጠ፣ በሰው ምሳሌም ተገለጠ»። ይህ ጥቅስ ወልደ እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ ሰው መሆኑን ያስረዳል። ስለዚህ ክርስቶስ የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ አለው። ማለትም ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው።

የአንዳንድ ጥቅሶች ማብራሪያ

ጌ.ኢ.ክ. አምላክ መሆኑን የማያምኑት (የጥንቱ አርዮስና የዛሬዎቹ ጀሆቫውያን) የሚከተሉትን ጥቅሶች መሠረት በማድረግ ነው።

1. «አብ ከእኔ ይበልጣል» (ዮሐ.14: 28)።
2. «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአብ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም የሚያውቅ የለም» (ማቴ.24: 36)።
3. «ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» (ቆላ.1: 15) ስለዚህ እርሱ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው ይላሉ


ምን እንመልስላቸው?

1. «አብ ከእኔ ይበልጣል» ሲል በትስብእቱ ብቻ ከአባቱ እንደሚያንስ መግለጹ ነው። የሚለምን ከሚለመን ያንሳል፤ ክርስቶስም አባቱን ስለሚለምንልን በትስብእቱ (በሰውነቱ) ከአባቱ ያንሳል። በመለኮቱ ግን አባቱን ለምኖ አያውቅም፣ እኩል ናቸውና። በቅድስት ሥላሴ መካከል ትልቅና ትንሽ የለም።
2. በእርግጥ አብ የሚያውቀውን፣ ወልድም ያውቀዋል፣ ወልድና አብ አንድ ናቸውና (ዮሐ.10: 30)። ስለዚህ ወልድም ቢሆን አያውቅም ማለቱ ልገልጽላችሁ አይገባኝም ማለቱ ነበር። ቀጥሎም «ሁልጊዜ

ዝግጁ ሁኑ» በማለት ሰው የሚመጣውን ጊዜ እንዲያውቅ መልካም አለመሆኑን ገለጸላቸው።።

3. ቅዱስ ጳውሎስ «ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» ካለ ለኋላ ቀጥሎ «እርሱ ከሁሉ ነገር በፊት ነበረ» (ቆላ.1፡ 17) ስለሚል ክርስቶስ አልተፈጠረም። በዚህ ጥቅስ ውስጥ «በኩር» ማለት በልዕልናም ሆነ በዘለዓለማዊነት ከሁሉም በፊት ነው ማለት ነው። ቀጥሎም «ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ነው የተፈጠረው» (ቆላ.1፡ 16) በማለቱ ክርስቶስ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አለመሆኑን ገለጸ።

ስለዚህ ወልደ እግዚአብሔር ከአባቱ ጋር እኩል ነው እንጂ ፍጡር አይደለም። አርዮስን ያወገዙት 318 ርቱዓነ-ሃይማኖት ጠንቤልን በደንብ የተረዱ ናቸው። ምክንያቱም እነርሱ የማትሳሳተው የክርስቶስ ማኅበር (ቤተክርስቲያን) መሪዎች ነበሩ። በገዛ ፈቃዳቸው ወንጌልን የሚተረጉ ሙት ግን ስሕተት ይፈጽማሉ።



ኢየሱስ በመተኛቱ ሰው መሆኑን፣ ተነሥቶ ማዕበሉን ጸጥ በማድረጉ ደግሞ አምላክ መሆኑን አሳየ (ማር.4፡ 39)

ሐ. ጌ.ኢ.ክ. ፍጹም ሰው ነው

ክርስቶስ አምላክ እንጂ ሰው መሆኑን የማያምኑ መናፍቃን አልታጡም «ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የማያምኑ ብዙ አሳሳቾች በዓለም ውስጥ አሉ» (2ዮሐ. 7)። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው፣ ምክንያቱም እውነተኛ ሥጋ ባይኖረው ኖሮ ሕማማቱና ሞቱ ከንቱ ቢሆን ነበር። ክርስቶስ ሰው መሆኑን ማመን አለብን። ይህንን ሐቅ የሚያስረዱን ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

«ቃል ሥጋ ሆነ» (ዮሐ.1፡ 14) ማለት ወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ ሥጋ ለበሰ፣ ሥጋውም ከዳዊት ዘር (2ጢሞ.2፡ 8) ከእናቱ ከእግዚእትነ ማርያም (ማር.6፡ 3 ሉቃ.2፡ 27) የወሰደው ነው። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ «ሰው» ተብሏል (1ጢሞ.2፡ 5)። ልክ እንደ አዳም ሰው ሆኗል (1ቆሮ.15፡ 21፣ ሮሜ.5፡ 12)። እንደ ማንኛውም ሰው ይራባል፣ ይበላል፣ ይጠጣልም (ማቴ.4፡ 2)፣ ይተኛል (ማቴ.8፡ 24)፣ ይደክምም ነበር፣ (ዮሐ.4፡ 6)፣ እንደ ማንኛውም ሰው ዕንባውን አፈሰሰ (ዮሐ.11፡ 35)፣ አላበው፣ እንዲያውም የደም ላብ አላበው (ሉቃ.22፡ 44)፣ ማርያምና ሰምዖን አቀፉት (ሉቃ.2፡ 28)፣ በሕዝብም ተነካ (ሉቃ.8፡ 44)፣ በተለይም ሐዋርያት ዳሰሱት «በእጆቻችን የዳሰስነው» (1ዮሐ.1፡ 1)፣ ጠላቶቹም ነክተውታል፣ ምክንያቱም በእነርሱ እጅ ታሰረ፣ ተገረፈ፣ ተቸነከረ፣ እነዚያ የቀበሩት ሽቶ ቀብተው ገንዘውታል (ዮሐ.19፡ 39)። እስከ ዛሬ ድረስም የሰውነቱ ምስል በመግነዣው ላይ ታትሞ ይታያል። ከኃጢአት በስተቀር በሁሉም ነገር እንደ እኛ ተፈትኗል (ዕብ.4፡ 15)። አይሁዳውያንም ኢየሱስ ሰው መሆኑን ስለ አወቁ ነው አምላክነቱን ያላመኑት። እንግዲህ እኛ ኢየሱስ ሰው መሆኑን አንጠራጠርም። ሰው ስለሆነም ሊሞትልን ቻለ፣ እኛም ድኅነትን አገኘን።

ስለ ጌ.ኢ.ክ. ሞትና ትንሣኤ ማብራሪያ


ጌ.ኢ.ክ. በእውነት መሞቱን የሚያስረዱን ነፍሱ ከሥጋው መለየቷ (ማቴ.27፡ 50)፣ ጐኑን በጦር መወጋቱ (ዮሐ.19፡ 34) እስከ መጨረሻ ጠብታ ድረስ ደሙን ማፍሰሱን የሚመሰክሩ ጥቅሶች ናቸው። እ.ኤ.አ. በ1851 ዓ.ም. የሞተው ጳውሎስ ጀርመናዊ «ክርስቶስ አልሞተም» ይላል። ነገር ግን አሳቡ መሠረት ስለሌለው ተቀባይነት የለውም።

ክርስቶስ በአምላክነቱ ነው ወይስ በሰውነቱ ነው የሞተው? በሰውነቱ ብቻ ነው የሞተው። ምክንያቱም በአምላክነቱ ሊታመምና ሊሞት አይችልም። «ክርስቶስ በሥጋ ሞተ፣ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ጴጥ.3፡ 18)።

ዝግጁ ሁኑ» በማለት ሰው የሚመጣውን ጊዜ እንዲያውቅ መልካም አለመሆኑን ገለጸላቸው።

3. ቅዱስ ጳውሎስ «ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» ካለ ለኋላ ቀጥሎ «እርሱ ከሁሉ ነገር በፊት ነበረ» (ቆላ.1፡ 17) ስለሚል ክርስቶስ አልተፈጠረም። በዚህ ጥቅስ ውስጥ «በኩር» ማለት በልዕልናም ሆነ በዘለዓለማዊነት ከሁሉም በፊት ነው ማለት ነው። ቀጥሎም «ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ነው የተፈጠረው» (ቆላ.1፡ 16) በማለቱ ክርስቶስ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አለመሆኑን ገለጸ።

ስለዚህ ወልደ እግዚአብሔር ከአባቱ ጋር እኩል ነው እንጂ ፍጡር አይደለም። አርዮስን ያወገዙት 318 ርቱዓነ-ሃይማኖት ጣንኤልን በደንብ የተረዱ ናቸው። ምክንያቱም እነርሱ የማትሳሳተው የክርስቶስ ማኅበር (ቤተክርስቲያን) መሪዎች ነበሩ። በገዛ ፈቃዳቸው ወንጌልን የሚተረጉሙት ግን ስሕተት ይፈጽማሉ።



ኢየሱስ በመተኛቱ ሰው መሆኑን፣ ተነሥቶ ማዕበሉን ጸጥ በማድረጉ ደግሞ አምላክ መሆኑን አሳየ (ማር.4፡ 39)

ሐ. ጌ.ኢ.ክ. ፍጹም ሰው ነው

ክርስቶስ አምላክ እንጂ ሰው መሆኑን የማያምኑ መናፍቃን አልታጡም «ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የማያምኑ ብዙ አሳሳቾች በዓለም ውስጥ አሉ» (2ዮሐ. 7)። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው፣ ምክንያቱም እውነተኛ ሥጋ ባይኖረው ኖሮ ሕማማቱና ሞቱ ከንቱ በሆነ ነበር። ክርስቶስ ሰው መሆኑን ማመን አለብን። ይህንን ሐቅ የሚያስረዱን ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

«ቃል ሥጋ ሆነ» (ዮሐ.1፡ 14) ማለት ወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ ሥጋ ለበሰ፣ ሥጋውም ከዳዊት ዘር (2ጢሞ.2፡ 8) ከእናቱ ከእግዚእትነ ማርያም (ማር.6፡ 3 ሉቃ.2፡ 27) የወሰደው ነው። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ «ሰው» ተብሏል (1ጢሞ.2፡ 5)። ልክ እንደ አዳም ሰው ሆኗል (1ቆሮ.15፡ 21፣ ሮሜ.5፡ 12)። እንደ ማንኛውም ሰው ይራባል፣ ይበላል፣ ይጠጣልም (ማቴ.4፡ 2)፣ ይተኛል (ማቴ.8፡ 24)፣ ይደክምም ነበር፣ (ዮሐ.4፡ 6)፣ እንደ ማንኛውም ሰው ዕንባውን አፈሰሰ (ዮሐ.11፡ 35)፣ አላበው፣ እንዲያውም የደም ላብ አላበው (ሉቃ.22፡ 44)፣ ማርያምና ሰምዖን አቀፉት (ሉቃ.2፡ 28)፣ በሕዝብም ተነካ (ሉቃ.8፡ 44)፣ በተለይም ሐዋርያት ዳሰሱት «በእጆቻችን የዳሰስነው» (1ዮሐ.1፡ 1)፣ ጠላቶቹም ነክተውታል፣ ምክንያቱም በእነርሱ እጅ ታሰረ፣ ተገረፈ፣ ተቸነከረ፣ እነዚያ የቀበሩት ሽቶ ቀብተው ገንዘውታል (ዮሐ.19፡ 39)። እስከ ዛሬ ድረስም የሰውነቱ ምስል በመግነዣው ላይ ታትሞ ይታያል። ከኃጢአት በስተቀር በሁሉም ነገር እንደ እኛ ተፈትኗል (ዕብ.4፡ 15)። አይሁዳውያንም ኢየሱስ ሰው መሆኑን ስለ አወቁ ነው አምላክነቱን ያላመኑት። እንግዲህ እኛ ኢየሱስ ሰው መሆኑን አንጠራጠርም። ሰው ስለሆነም ሊሞትልን ቻለ፣ እኛም ድኅነትን አገኘን።

ስለ ጌ.ኢ.ክ. ምትና ትንሣኤ ማብራሪያ

ጌ.ኢ.ክ. በእውነት መሞቱን የሚያስረዱን ነፍሱ ከሥጋው መለየቷ (ማቴ.27፡ 50)፣ ጐኑን በጦር መወጋቱ (ዮሐ.19፡ 34) እስከ መጨረሻ ጠብታ ድረስ ደሙን ማፍሰሱን የሚመሰክሩ ጥቅሶች ናቸው። እ.ኤ.አ. በ1851 ዓ.ም. የሞተው ጳውሎስ ጀርመናዊ «ክርስቶስ አልሞተም» ይላል። ነገር ግን አሳቡ መሠረት ስለሌለው ተቀባይነት የለውም።

ክርስቶስ በአምላክነቱ ነው ወይስ በሰውነቱ ነው የሞተው? በሰውነቱ ብቻ ነው የሞተው። ምክንያቱም በአምላክነቱ ሊታመምና ሊሞት አይችልም። «ክርስቶስ በሥጋ ሞተ፣ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ጴጥ.3፡ 18)።

ጌ.ኢ.ክ. በእውነት ከሞት መነሣቱን የሚያስረዱን መቃብሩ ባዶውን መቅረቱ፣ መላእክት መነሣቱን ማወቃቸው፣ ብዙ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ በደንብ የተመለከቱትና የመረመሩት ሐዋርያት (በተለይም ቶማስ) ማየታቸውን የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅድስ ንባቦች ናቸው። የተነሣውም እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋም ነው እንጂ መንፈሱ ብቻ አይደለም። «እጆቼንና እግሮቼን (የችንካር ምልክቶችን) አይታችሁ እኔ ራሴ መሆኔን ዕወቁ፣ ዳስሳችሁም እዩኝ፣ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም» አላቸው (ሉቃ.24፡ 39)።

ጀሆቫውያን ግን «ክርስቶስ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» የሚለውን የጴጥሮስ ቃል ሳይረዱት «ሥጋው ጠፋ፣ ሞቶ የነበረው መንፈሱ ግን ወደ ሕይወት ተመለሰ» ብለው ይተረጉሙታል። ይህ ትርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይስማማም። ምክንያቱም «በመንፈስ ሕያው ሆነ» ማለት በመንፈሱ ሳይሞት ቀረ ማለት ነው። ሥጋውም አልጠፋም፣ ክርስቶስ ራሱ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት አሳይቷልና (ሉቃ.24፡ 39)። ነቢዩ ዳዊትም አስቀድሞ መሲሕ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋውም በመቃብር ፈርሶ እንደማይቀር ተናግሯል (የሐዋ.ሥራ2፡ 31)። ስለዚህ ሞቶ የነበረው ሥጋው በሦስተኛ ቀን ታድሶ እንደገና ከ መንፈሱ ጋር ተዋሕዶ ተነሥቷል።

ክርስቶስ በእርግጥ በሥጋውና በአጥንቱ ተነሥቷል፣ ይሁን እንጂ ከሞት የተነሡት ሁሉ የሚያገኙትን አኗኗር ስላገኘ (1ቆሮ.15፡ 43) ሥጋው ረቂቅ፣ ቀላልና ብሩህ ስለሆነ መላእክትን ይመስላል። ስለዚህ ግዙፋዊ የመርገጫ ቦታ አያስፈልገውም። በተዘጋ ግድግዳ ውስጥ ማለፍንና በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ መገኘት ይችላል። ይህ ነገር አሁን ሊገባን አይችልም። እኛም ከሞት ከተነሣን በኋላ ሥጋችን የተከበረውን የክርስቶስ ሥጋ ይመስላል። (ፊል.3፡ 20)፣ ያኔ ልንረዳው እንችላለን (ይገባናል)።

ወደ ዓለም የተላከው መሲሕ አንድ ብቻ ነው

ጌ.ኢ.ክ. ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ስለ መድኃኔ ዓለም ተነግረው የነበሩት ትንቢቶች በእርሱ ላይ ስለ ተፈጸሙና ብዙ ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን ስለ አመጣ፣ መሲሕ ብቻ ሳይሆን የአምላክ ልጅ፣ ማለትም ራሱ እግዚአብሔር መሆኑ ተገለጸ። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ (ዮሐ.1፡ 1) የነቢያትን ትምህርት አሟላው (ዕብራ.1፡ 2) ለድኅነታችንም ሲል ሞትን ተቀበለ። ከእርሱ በኋላ ሌላ መሲሕ ይመጣል ተብሎ

በፍጹም አይታሰብም፣ ምክንያቱም ኢየሱስ እንደ ማንም ተራ ነቢይ ሐላፊ አይደለም፣ ለዘላለም ነዋሪ ነው እንጂ። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው፣ አይለወጥም» (ዕብራ.13፡ 8)። ከ እርሱ በኋላ ሌላ መሲሕ መጥቶ ሊያስተምረን አይገባም፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ. ድሮ ተሠውሮ የነበረውን ምሥጢር ሁሉ ገልጾልናል (ኤፌ.3፡ 9)። ከእርሱ ማለትም ከአምላክ የሚበልጥ መምህር ደግሞ ከቶ አይገኝም። ስለዚህ ዛሬ አንዳንድ ነቢያት ቢነሱ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ለማጠንከርና ለመቀጠል እንጂ የእርሱን ቦታ መ ውሰድ ወይም ራሳቸውን እንደ ክርስቶስ መቁጠር የለባቸውም። ቅዱሳን በሙሉና ጳጳሳት ሕዝበ ክርስቲያን የክርስቶስን ትምህርት በተግባር ላይ እንዲያውሉ አገሏቸው እንጂ ሌላ አዲስ ሃይማኖት አላስተማሯ ቸውም።

ዛሬ አንድ ነቢይ ተነሥቶ የክርስቶስን ቦታ ቢይዝ ሐሰተኛ መሆኑ ግልጽ ነው። ጌ.ኢ.ክ ክርስቶስም «ማንም ሰው እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ! ምክንያቱም ብዙዎች 'እኔ መሲሕ ነኝ!' እያሉ በስሜ ይመጣሉ፣ ብዙ ሰዎችንም ያሳስታሉ።» ብሎ አስጠንቅቆናል (ማቴ.24፡ 4)። እንዲሁም ማንም ሰው «እነሆ ክርስቶስ እዚህ አለ! ወይም እዚያ አለ ቢላችሁ አትሙኑ» ብሏል (ማቴ.24፡ 23)። ከዚህ ስሕተት እንድንጠነቀቅ 2ኛው የቫቲካን ጉባኤም «ጌ.ኢ.ክ ያመጣልን አዲስ ኪዳን ፍጹም ስለ ሆነ አያልፍም፣ ስለዚህ ከዳግመኛ መምጣቱ በፊት ሌላ መገለጽ (ማለትም ሌላ የእግዚአብሔር ልኡክ) እንዲመጣልን መጠባበቅ የለብንም» በማለት ነገሩን ግልጽ አድርጉታል (2ኛ የቫቲካን ጉባኤ2፡ 4)።

አይሁዳውያን ትንቢቶችን በደንብ ስላልተገነዘቡና ፖለቲካዊ ንጉሥን ስለ ተጠባበቁ ጌ.ኢ.ክ የእግዚአብሔር መሲሕ መሆኑን ሊያውቁ አልቻ ሉም። ስለ ሆነም ሌላ መሲሕ እንዲመጣላቸው መጠባበቅ ጀመሩ። ከ ጥቂት ጊዜ በኋላ ሌላ ነቢይ መጥቶ መሲሕ ተባለ፣ ኧረ እንዲያውም ብዙ ሐሰተኞች መጥተው «እኔ መሲሕ ነኝ» እያሉ ኢየሩሳሌምን በጦ ርነት ለማዳን ስለ ተዋጉ ተቀባይነትን አገኙ። ነገር ግን ሁሉም በየተራ ቸው ስለ ተሸነፉ ሐቀኛ መሲሕ አለመሆናቸው ተገለጸ። ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን ከዚህ ቀጥለን እንዘረዝራለን። ለምሳሌ፦

ሳምራዊ መሲሕ፦

እንደ እውነተኛ መሲሕ ስለ ታመነ ብዙ ተከታዮችን አገኘ። ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ36 ዓ.ም. በሮማውያን ተሸነፈ።

ቴዎዲስ አይሁዳዊ (የሐዋ.ሥራ5፡ 36)፡-

ሥራው ትንሽ ተሳክቶለት ነበር። ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ44 ዓ.ም. ተገደለ።

በን-ስታዳ ግብጻዊ (የሐዋ.ሥራ21፡ 38)፡-

እ.ኤ.አ. በ54 ዓ.ም. ታላቅ ሠራዊቱ በጌተሴማኒ አጠገብ ተሸነፈ።

ሰምያን ባር ኮክባ፡-

በመጀመሪያ በሮማውያን ላይ ድልን ስለተጐናጸፈ ከሌሎች መሲሕ ዎች ነን ከሚሉት በላይ ታማኝነትን አገኘ። አብዛኞቹ እስራኤላውያን ዓይናቸውን ጨፍነው እስከ ሞት ድረስ ተከተሉት። ይህም የሆነው እ.ኤ.አ. በ132 ዓ.ም. ነው።

እንደዚህ ዓይነት ሐሰተኞች መሲሕዎች በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜ ዎች ተነሥተዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ በፖለቲካ ሳይሆን በመንፈስ መ ሲሕዎች ተባሉ። ለምሳሌ፡-

ማነስ ፐርሽያዊ፡-

እኔ የሁሉም ነቢያት ፍጻሜ ነኝ ብሎ እ.ኤ.አ. በ275 ዓ.ም. የተሳሳተ ትምህርቱን ማለትም ማኒከይዝም አስፋፋ።

ዳዊት ኤልፎይ ፐርሽያዊ፡-

እ.ኤ.አ. በ1160 ዓ.ም. መሲሕ ተብሎ በመላው አስያ ታወቀ።

ሻበታይ ሽቢ ስሚርናዊ (ቱርካዊ)፡-

መሲሕ ተብሎ ብዙ ተከታዮችን አግኝቶ ነበር። ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ1616 ዓ.ም. በቱርክ መንግሥት ታሠረ።

ባሁላ (ሚዝራ ሐሰይን ዓሊ) ፐርሽያዊ፡-

እ.ኤ.አ. በ1844 ዓ.ም. ከእርሱ በፊት የነበረውን ነቢይ (ባብ) መደገፍ ጀመረ። እ.ኤ.አ. በ1867 ዓ.ም. የሁሉም ነቢያት መጨረሻ ተብሎ ዓለምን ለማደስ መላኩን ገለጸ፣ አዲስ ሃይማኖትም አስፋፋ፣ ራሱንም እንደ ክርስቶስ አድርጎ ቆጠረ። ጌ.ኢ.ክርስቶስን ቢደግፍ ኖሮ ትልቅ ሥራ በሠራ ነበር፣ ምክንያቱም ትምህርቱ በጣም ድንቅ ነበርና። ነገር ግን ራሱን በክርስቶስ ቦታ ለማስቀመጥና ክርስቶስን ለመተካት ስለ ደፈረ ተሳሳተ። ባሐያውያን የሚባሉት እንግዲህ የመምህራቸውን

ትምህርት በማስፋፋትና የሰው ልጆችን ወንድማማችነት በመፈለግ የ ተመሰገኑ ናቸው። ነገር ግን ጌ.ኢ.ክ. አንድ መድኃኔ ዓለም መሆኑን ስለማያምኑ ይሳሳታሉ።

ሱን ምዩንግ ሙን ኮሪያዊ፡-

«ባፕቲስት» ከሚባሉት ክርስቲያን ፕሮቴስታንቶች ተለይቶ በአሜ ሪካ ተቀምጦ፣ (እንደ እሱ አባባል ክርስቶስ ስላልተሳካለት) በክርስቶስ ፋንታ እሱ በእግዚአብሔር እንደ ተላከ ሆኖ እስከ አሁን እየሰበከ ነው። ተከታዮቹም «ወደ ዓለም የተመለሰ ክርስቶስ ነው» ይሉታል፣ የብዙ ሀገሮች ሕዝቦችንም እያሳሳቱ ናቸው። ይህም ከሌሎች ሐሰተኞች ነቢያት አንዱ ስለሆነ በምንም ዓይነት ልናምነው አይገባም።

ሌሎችም እነዚህን የመሰሉ ሐሰተኞች ነቢያት ቢነሱ እኛ ከሃይማ ኖታችን እንዳንነቃነቅ እንጠንቀቅ። «ብሰው ፊት የሚክደኝን ሁሉ እኔም በሰማይ አባቴ ፊት እክደዋለሁ» (ማቴ.10፡ 33)፣ «የሰማይ መልአክም ቢሆን እኛ ከሰበክንላችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላትያ.1፡ 8)።

ምዕራፍ 16

ስለ እመቤታችን ማርያም

የእውነት ዐምድና መሠረት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን (1ጢሞ.3፡ 15) ከመጽሐፍ ቅዱስና ከትውፊት ቀስማ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚከተለውን ትምህርት ታቀርብልናለች።

1. እመቤታችን ማርያም ወላዲተ አምላክ እንድትሆን ተመርጣ ስለ ነበረች በልጇ ትሩፋት ተጠቅማ ከአዳም ኃጢአት ነፃ ሆና ተፀነሰች። እግዚአብሔር ለእባብ የተናገረው ትንቢት ማለትም «የእርስዋ ዘር የእንተን ራስ ይቀጠቅጣል» (ኦሪ.ዘፍ.3፡ 15) የሚለው ከሁሉ በፊት በማርያም ላይ ተፈጸመ፣ ምክንያቱም በመጀመሪያ የሕይወቷ ደቂቃ እንኳ ሳይቀር በሰይጣን አልተገዛ ችምና። መልአኩ ገብርኤል «አንቺ ጸጋን የተሞላሽ ሰለም ላንቺ ይሁን» (ሉቃ.1፡ 28) በማለት ሁልጊዜ በሕይወቷ መጀ መሪያም ቢሆን ጸጋ የተሞላች መሆንዋን ገለጸ። ለእንዲት

ደቂቃ እንኳ በኃጢአት ተገዝታ ብትሆን ኖሮ ጸጋ የተሞላች ልት ባል ባልቻለችም ነበር። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በደንብ ስለ ተረዳችው (ስለ ተገነዘበችው) ቅዱስ ጳውሎስ «በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ ኃጢአት ሠራ» (ሮሜ.5፡ 12) ያለ ው ቃል እመቤታችን ማርያምን አይመለከትም ብላ፣ በጳጳስ አፍ አድርጋ «እመቤታችን ማርያም ያለ አዳም ኃጢአት መፀነስዋን የ ማያምኑ ሁሉ የክርስቲያን ሃይማኖት ከሐዲዎች መሆናቸውን» ገለጸች ርፒዮስ 9ኛ እ.ኤ.አ. 1854 ዓ.ም ነ።



«ጸጋን የተሞላሽ ሆይ! ሰላም ላንቺ ይሁን» (ሉቃ.1፡ 28)

2. እመቤታችን ማርያም ከሁሉም መላእክትና ቅዱሳን በላይ የተቀደሰ ች ናት። እንደ ቤተ ክርስቲያን አተረጓጐም «ጸጋን የተሞላች» (ሉቃ.1፡ 28) ማለት ከአዳም ኃጢአት ነፃ መሆን ብቻ ሳይሆን ከማ ንኛውም ትንሽ የሰው ኃጢአትም ጭምር በሕይወቷ ዘመን ሁሉ ነፃ ሆነች ማለት ነው። በንጽሕናና በቅድስና በጣም የተሞላች ስለ ሆነች ከአምላክ በታች (ከአምላክ ቀጥሎ) ከቅድስናዋ የሚበልጥ ቅድስና በፍጹም ሊታሰብ አይችልም። ቅድስናዋም በጣም የላቀ

ስለ ሆነ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም በአእምሮው ሊገምተው አይችልም (ጳጳስ ፒዮስ 9ኛ)።

3. እመቤታችን ማርያም በፍጹም ድንግልና ትኖር ነበረች (ሉቃ. 1፡ 34)። ክርስቶስንም በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ፀንሳ ወለደችው (ሉቃ.1፡ 35)። ቅዱስ ዮሴፍ የክርስቶስ አሳዳጊ አባት ነው እንጂ የወለደው አባቱ አይደለም። ማርያም ክርስቶስን ከወለደችውም በኋላ ሕይወቷ ን በሙሉ በፍጹም ድንግልና ኖረች። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት «ማርያም ከመውለዷ በፊት ድንግል፣ በምትወልድበት ጊዜም ድንግል፣ ከወለደች በኋላም ድንግል ናት» በማለት ገልጸዋል።

ለቡ (NB) በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁ7 ጌ.ኢ.ክ. የማርያም የበኩር ልጅ ስለ ተባለ ድንግልናዋን የሚቃወም ምንም ነገር እያመለክ ትም፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከነበረው ታሪክ እንደምና ውቀው የመጀመሪያ ልጅ ከእርሱ በኋላ ሌላ ባይወለድም (ልዩ መብት ስለ ነበረው) በኩር ይባል ነበር። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ምንም እንኳ አንድ የማርያም ልጅ ቢሆ ንም በዚህ ልዩ መብት መሠረት የበኩር ልጅዋ ተብሏል። በወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ወንድሞች የሚባሉት (ማቴ.12፡ 46፣ 13፡ 55፣ ገላትያ.1፡ 9) የማርያም ቀለዮጳ ልጆች መሆናቸ ውን እናውቃለን (ማር.15፡ 40)። በእስራኤል አገር ወንድም ሲባል ማንኛውንም ዘመድ ያመለክት ነበር። ስለዚህ እመቤታ ችን ማርያም ከኢየሱስ በስተቀር ሌሎ ች ልጆች እንዳልወለደ ችና በሕይወቷ ዘመን ሁሉ በድንግልና እንደ ኖረች እንጠራ ጠርም።

4. እመቤታችን ማርያም በእውነት የአምላክ እናት ናት፣ ምክንያቱም እርሷ የወለደችው ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነው፣ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው። (ዮሐ. 1፡ 1)። ከዘላ ለም ጀምሮ የእግዚአብሔር አብ ልጅ የነበረው ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ደግሞ የማርያም ልጅ ሆኖ ተወለደ። እመቤታችን በኢሳይያስ (7፡ 14) የአማኑኤል እናት (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው)፣ በገብርኤል የኢየሱስ እናት (ሉቃ.1፡ 31)፣ በኤልሳቤጥ «የጌታዬ እናት» (ሉቃ.1፡ 43) ተብላለች። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም በሐዋርያት ተመ ርተው ማርያምን የአምላክ እናት ብለው ይመለክሩ ስለ ነበሩ፣ በ ኤፌሶን ጉባኤ ላይ የተሰበሰቡት አቡኖች «እመቤታችን ማርያም በእውነት የአምላክ እናት ናት፣ ይኸንን የማያምን የተወገዘ ይሁን» ብለው አወጁ (ኤፌሶን እ.ኤ.አ. 431 ዓ.ም.)።

5. እመቤታችን ማርያም የክርስቶስ እናት ብቻ ሳትሆን የሁሉም ተከታዮቹም እናት ናት። ምክንያቱም፦

ሀ) «ሊየሱስ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው» (ቆላ.1፡ 18) «እኛም የክርስቶስ አካል ክፍሎች ነን» (ኤፌ.5፡ 30)። የቤተ ክርስቲያንን ራስ የወለደችው አካላቱቹን ም ወልዳለች፣ ስለዚህ ማርያም እናታችንም ናት።

ለ) ክርስቶስ «የበኩር ልጅዋ» ስለ ተባለ (ሉቃ.2፡ 7) እኛ ሌሎች ልጆችዋ ነን።

ሐ) ጌ.ኢ.ክ. ራሱ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ ይህን ትምህርት ገልጾልናል። ምክንያቱም ለማርያም «እነሆ ልጅሽ» (ዮሐ.19፡ 26) በማለት ዮሐንስን አመለከተ። በዮሐንስ ስም ግን ሁሉንም ክርስቲያን ለማርያም ማስረከቡ ነው። በዚህ ምክንያት እመቤታ ችን ማርያም «የቤተ ክርስቲያን እናት፣ ማለትም የክርስቶስ አካላት የሆኑት ሕዝበ-ክርስቲያን እውነተኛ እናት ናት» (ጳጳስ ጳውሎስ 6ኛ በሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ ላይ)።



ቅድስት ድንግል ማርያም ከውድ ልጅዋ ጋር

6. እመቤታችን ማርያም መድኃኔ ዓለምን በመውለድ ብቻ ሳይሆን በ ሕማማቱና በሞቱ በመሳተፍ ድኅንነትን አስገኝተልን። እንደ ቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ «የእርስዋ ዘር የእንተን ራስ ይቀጠቅጣል» (ኦሪ.ዘፍ፡ 3፡ 15) የሚለው ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ማርያምም ከልጅዋ ጋር በጣም ተባብራ የአባብን ራስ እንደምትጨፈልቅልን የሚያመለክት ትንቢት ነው። ይህ ትንቢት በእመቤታችን ማርያም ላይ ፍጻሜውን አገኘ። ምክንያቱም እርስዋ «የክርስቶስ ርኅሩኅ ተባባሪ ሆና በድኅንነታችን ሥራ ውስጥ ተሳትፋለች» (2ኛ የቫቲካን ጉባኤ 1፡ 61)። በተለይም በመስቀሉ ሥር ሆና በሥቃይዋና በጸሎ ትዋ የሕማማቱ ተካፋይ ስለ ሆነች ከልጅዋ ጋር ተባብራ መንግሥተ ሰማይን ከፈተችልን። ቅዱስ አጉስጢኖስ እንደሚለው «በአንዲት ሴት (በሔዋን) ሞት መጣብን፣ በአንዲት ሴት (በማርያም) ግን ሕይወት መጣልን»።

7. እመቤታችን ማርያም ከአዳም ኃጢአት ነፃ ስለ ሆነችና ሥጋዋም የአምላክ ታቦት ስለ ሆነ፣ በመቃብር ውስጥ ሊበላሽ አይገባውምና ምድራዊ ሕይወትዋን ከጨረሰች በኋላ በነፍስና በሥጋ ወደ ሰማይ ወጣች። ይኽንን የሚያስረዳን የሰይጣን ግዛትና የሞት ግዛት አንድ መሆኑና (ሮሜ.5፡ 12) እመቤታችን ማርያም ግን የሰይጣንን ራስ ስለ ጨፈለቀች ከሞት (ከመቃብር) አመለጠች። ይህ ትምህርት በ መጽሐፍ ቅድስ ውስጥ ግለጽ ባይሆንም በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ውስጥ ግልጽ ነው። በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት በብዙ ሕዝብ የታመነ ትምህርት ነበር። ስለዚህም የጴጥሮስን ሥልጣን የወረሱት ጳጳስ ፒዮስ 12ኛ እ.ኤ.አ. በ1950 ዓ.ም. «እመቤታችን ማርያም በነፍስና በሥጋ ወደ ሰማይ ወጥታለች» ብለው በግልጽ ስለ አወጁ ይህ ትምህርት የዓንቀጸ ሃይማኖታችን አካል (ክፍል) ሆኗል።

8. እመቤታችን ማርያም ወደ ሰማይ ከወጣች በኋላ የሰማይና የም ድር ንግሥት ሆና ዘላለማዊ ክብርን ተቀብላለች። በምድር የክርስቶስ ሕማማት ተሳታፊ ስለ ነበረች በሰማይም የመንግሥቱ ተሳታፊ ሆናለች። ክርስቶስ ንጉሥ እንደ ተባለ ሁሉ (ሉቃ.1፡ 33፣ የዮሐ. ራእይ.19፡ 16) ማርያምም ንግሥት ተብላለች (ፒዮስ 12ኛ)። ከፍተኛ ችሎታ ስላላት፣ በቅዱሳንና በሊቃውንት ጠበቃችንና የጸጋ ሁሉ አማላጅ፣ ኧረ እንዲያውም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አገናኝ (መካከለኛ) ተብላለች። ይህም ማለት በቃና ዘገሊላ እንዳደረገችው ሁሉ (ዮሐ.2፡ 3) ከልጅዋ ከክርስቶስ ልትለምንልን ትችላለች፣ ከክ

ርስቶስ ጋር ተባብራም ከዘላለማዊው እግዚአብሔር አብ ትለምንል ናለች፣ ታገኝልናለችም።

9. እመቤታችን ማርያምን እንድንለምናትና እንድናከብራት እግዚአብሔር ይፈልጋል። ይኸንን የሚያስረዳን ትምህርት የሚከተለው ነው።

ሀ. እግዚአብሔር ከሁላችን በፊት በመልአኩ በገብርኤል አፍ አድርጉ «ጸጋን የተሞላሽ ሆይ! ሰላም ላንቺ ይሁን» ብሎ ማርያምን አከበራት፣ በኤልሳቤጥ አፍ አድርጉ ደግሞ «ከሴቶች ሁሉ አንቺ የተባረክሽ ነሽ» አላት። በእመቤታችን ማርያም አፍ አድርጉ በደረሰው ትንቢት ማለትም «ትውልድ ሁሉ የተመሰገንሽ ነሽ ይለኛል» (ሉቃ.1፡ 48) የሚለው በግድ መፈጸም ስላለበት ልናወድሳት ይገባናል።

ለ. ጌኢ.ክ. ማርያምን እንደ እናታችን አድርጉ ስለ ሰጠን በውስጻዊ ፍቅር እንድናከብራት መፈለጉ ግልጽ ነው። እናቱን የማያከብር ማን ነው? ጌኢ.ክ. በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ስለ አከበራትና ስለ አፈቀራት በእርአያው አስተምሮናል።

ሐ. እግዚአብሔር ጸድቃን ስለ ኃጢአተኞችና በደለኞች እንዲ ለምኑት ይፈልጋል። እነ ኢዮብ (42፡ 8)፣ ሙሴ (ኦሪ.ዘዳ.32፡ 13)፣ እስጢፋኖስ (የሐዋ.ሥራ7፡ 60)፣ ኧረ እንዲያውም ክርስቲያኖች በሙሉ ስለ ወንድሞቻቸው እንዲለምኑት ይወዳል (ያዕቆብ 5፡ 16)። በተለይም ደግሞ እመቤታችን ማርያም እንድትለምንልን ይወዳል፣ ጸሎቷንም ይቀበላል፣ ስለዚህ ወደ እመቤታችን መማጠናችን መልካም ነው። ቤተ ክርስቲያንም «ቅድስት ማርያም ሆይ! ለምኚልን» ብለን እንድንጸልይ ታስተምረናለች።

10. እመቤታችን ማርያም ከሁሉም ፍጥረቶች የበለጠችና ከፍ ያለች ስለ ሆነች በታላቅ አክብሮት ልናከብራት ይገባናል። ነገር ግን እርስዋም ፍጥረት ስለ ሆነች ለፈጣሪ ብቻ የሚገባውን የአምልኮ ስግደት ልናቀርብላት አንችልም። የአንዳንድ አካባቢ ሕዝቦች ለእግዚአትነ ማርያም የአምልኮ ስግደት በማቅረባቸው ይሳሳታሉ። አብዛኞቹ ለእመቤታችን ማርያም የሚሰግዱት ክርስቲያኖች ግን የአክብሮት እንጂ የአምልኮ ስግደት አያቀርቡላትም። የአምልኮ ስግደት የሚሰጠው ለአምላክ ብቻ ነው። ስለዚህ ለጌኢ.ክ. የአምልኮ ስግደት ይገ

በዋል፣ ምክንያቱም ምንም እንኳ በሰውነቱ (በስብአዊነቱ) የተወለደ ቢሆንም በመለኮቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል አምልኮ ይገ በዋል። (ፊል2፡ 10)።

ስለ እመቤታችን ማርያም አማላጅነት ማብራሪያ

ፕሮቴስታንቶች «በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታርቀው አንድ ነው፣ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ጢሞ.2፡ 5) የሚለውን ተከትለው፣ ከክርስቶስ በስተቀር ሌላ አስታራቂ፣ ማርያምም ብትሆን አያስፈልገንም ይላሉ፣ ይህን ጥቅስ ያለ ስሕተት ልትተረጉምልን የምትችለው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። እርሷም «ቅ. ጳውሎስ የክርስቶስ ተቃራኒ ሆነው የሚነሱትንና ራሳቸውን በክርስቶስ ቦታ ለመተካት የሚደፍሩትን ነው እንጂ፣ የክርስቶስ ወዳጆች የሆኑትን ቅዱሳን፣ በተለይም ደግሞ ማርያም እናቱን አማላጅና አስታራቂ ከመሆን አላስወገደም፣ ብላ ታስተምረናለች። በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን «ግኖስቲክ» የተባሉ መናፍቃን ተነሥተው «ክርስቶስ «ኤዮንስ» ከሚባሉት መካከለኛ መናፍስት አንዱ ነው» ይሉ ስለ ነበሩ፣ ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን ከንቱ የነበሩትን መካከለኞች አስወገዳቸው።

እንዲሁም ሐሰተኞች መሲሕዎች ተነሥተው ክርስቶስን ለመተካት ከሞከሩ፣ እነዚህ በልዩ ሁኔታ በቅዱስ ጳውሎስ የተወገዱ ናቸው። ምክንያቱም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው ነው፣ አይለወጥም» (ዕብራ13፡ 8)።


እንግዲህ እመቤታችን ማርያም ከአማላጅነትና ከአስታራቂነት አልተ ከለከለችም። በቤተ ክርስቲያን ደግሞ አማላጃችን ተብላለች። ምክንያቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) እግዚአብሔር ልጹን ሊልክልን ስለ ፈለገ ማርያምን መካከለኛ አደረጋት፣ ማለትም ልጁ ከድንግል ማርያም እንዲወለድ አደረገ። ስለ ዚህ ትልቅ ስጦታው የሆነውን ክርስቶስን በማርያም በኩል ሊሰጠን ከ ፈለገ፣ ሌሎቹን ስጦታዎች ሁሉ በማርያም በኩል ሊሰጠን ይወዳል።

ለ) ክርስቶስ በሰማይ ሆኖ ጠበቃችን ነው፣ ምክንያቱም «በእግዚአብ ሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ ስለ እኛ የሚማልድ ነው» (ሮሜ.8፡ 34) እርሱ ግን እናቱ በምድር ሆና አጋዥና ደጋፊው እንድትሆን እንደ ፈለገው ሁሉ በሰማይም ጠበቃችን ሆና እስከ መጨረሻው ድረስ በሰዎች ድኅነት ውስጥ እንድትሳተፍ ይፈልጋል።

ሐ) በሰማይ ቅዱሳን ጠበቃዎቻችን መሆናቸው ግልጽ ነው። ለምሳሌ ያህል አንያስና ኤርምያስ (2መቃ.15፡ 12)። ስለዚህ እመቤታችን ማርያም የበለጠች አማላጃችንና ጠበቃችን መሆንዋን እንረዳ። ይህ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ግልጽ ባይሆንም በቤተ ክርስቲያን ትው ፊት ውስጥ በጣም ግልጽ ነው። በካታኮምብ መቃብሮች ውስጥ የተጻ ፉትን ልመናዎች እናስታውስ።

መ) ምንም እንኳ ክርስቶስ ብቻውን መካከለኛና አስታራቂያችን መሆን ቢችልም፣ ከእርሱ ጋርና ከእርሱ በታች አጋዦች እንዲኖሩት ይወዳል። በምድራዊ ሕይወታችን ውስጥም እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ራሱ ሊያደርግልን ይችል ነበር። ይሁን እንጂ አጋዦች እንዲኖሩት ያስ ፈልጋል። ለምሳሌ፦ በወላጆቻችን አድርጎ ይቀልበናል፣ በአስተማሪዎች አድርጎ ያስተምረናል፣ በሐኪሞች አድርጎ ያክመናል። እንዲሁም በመንፈ ሳዊ ሕይወታችን እግዚአብሔር ብቻውን ሳይሆን በማርያምና በቅዱሳንም አድርጎ ይጠብቀናል፣ ያግዘናል፣ ይንከባከበናልም። ለምሳሌ በዚህ ዓለምም ቢሆን አንድ ደግ ንጉሥ ምንም እንኳ ለሕዝቡ ራሱ ሊያስብላቸው ቢች ልም በአጋዦቹ አድርጎ እርዳታን ይሰጣቸዋል፣ ሕዝቡም በንግሥቲቱ ወይም በወዳጆቹ በኩል አድርገው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ቢለምኑት ንጉሡ በበለጠ ያስብላቸዋል።



«እናቱን የሚያከብር ሃብትን ያከማቻል (ሲራ.ክ.3፡ 4)

እንግዲህ ወደ እመቤታችን ማርያም የምናደርገው መንፈሳዊነት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን ለእኛ ደግሞ ጥቅምን ይጨመራልና በውዴ ታችን ዘወትር እናድርገው። ቅዱሳን እንደሚሉት «ለእናት የሚሰጠው ክብርና ፍቅር ወደ ልጅዋ ያልፋል»። ቅዱስ ፒዮስ 10ኛ «ክርስቶስን ብቻ ለማክበር ማርያምን የሚያስወግዱ ክርስቶስንም አያከብሩትም፣ ምክንያቱም የክርስቶስን ፍላጐት አይፈጽሙትምና» ብሎ ሰበከ። ክርስቶ ስና ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተባብረው እንደሚገኙ ሁሉ፣ በልባችን ውስጥም የክርስቶስ ፍቅር ከማርያም ፍቅር መለየት የለበትም።

ምዕራፍ 17

ስለ መላእክትና ስለ ቅዱሳን አክብሮት

ከእግዚአብሔርና ከእመቤታችን ማርያም በታች መላእክትንና ቅዱ ሳንን ማክበርና መለመን መልካም ነው። ምክንያቱም አስቀድመን እንደ ገለጽነው እነርሱም የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጆች ስለ ሆኑ ሊያማል ዱልን ችሎታ አላቸው (2መቃ.15፡ 12)። ይህን ትምህርት በቤተ ክርስ ቲያን ትውፊት ውስጥ እናገኛለን፣ ሕዝበ-ክርስቲያንም ከመጀመሪያዎቹ ዘመናት ጀምረው ቅዱሳንን ይለምኑ ነበሩ። ይህ ወደ ቅዱሳን የሚደረገው ልመና እስከ ዛሬ ድረስ በጥንታዊ መቃብሮች ላይ ተጽፎ ይታያል። ስለዚህ በትረንቶ ጉባኤ ላይ ተሰብስበው የነበሩት አቡኖች «ከክርስቶስ ጋር የነገሡት ቅዱሳን ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያቀርቡ ወደ እነርሱ መማጠን መልካምና ጠቃሚ ነው» ብለው አወጁ።

መላእክትንና ቅዱሳንን በምናከብርበት ጊዜ እንደሚከተለው ማድረግ ይገባናል። በሥዕላቸው ወይም በመቃብራቸው ፊት እጅ መንሣት፣ ወ ይም መሳለም ወይም ደግሞ ተንበርክኮ ጸሎት ማድረግ ነው። የበለጠው አክብሮት ደግሞ ለክብራቸው ብለን ቅዳሴ ማስቀደስ ወይም መቀደስ ነው። በዮሐንስ ራእይ (19፡ 10) አንድ መልአክ ራሱ ዮሐንስን እንዳስጠ ነቀቀው የአምልኮት ስግደት አይገባቸውም። እንግዲህ ይህንን የአክብሮት ሥራ ለአምላክ እንደሚገባው የአምልኮት ስግደት እንዳንገምተው እንጠ ንቀቅ።



ቅዱስ ዮሴፍ የኢየሱስ ሕፃን መጋቢና ጠባቂ

ቤተክርስቲያን የምትካሄደው በጥንቃቄ ነው፣ ስለዚህ በደንብ መርምራ ያወቀቻቸውንና በፊጸሙት ተአምራት በደንብ የተገለጹትን ቅዱሳን አንጂ በሕዝቡ ልማድ ብቻ እንደ ቅዱሳን የሚታሰቡትን አታከብራቸውም። ቅዱሳንን በማክበራችን እግዚአብሔርን እንረሳውም። እንዲያውም ቅዱሳን በእግዚአብሔር ኃይልና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትሩፋት (ኦርዳታ) ወደ ቅድስና መድረሳቸውን አምነን እግዚአብሔርን በበለጠ እናከብረዋለን።

ስለ ቅዱሳን አስክሬንና ዕቃዎች

የእውነት ዐምድና መሠረት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን እን ደምታከብራቸው ሁሉ አስክሬናቸውንም ታከብራለች። ምክንያቱም አካላ ቸው የክርስቶስ አካላትና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነው ስለሚነሱ በ ሕዝበ ክርስቲያን መካበር ስላባቸው (የትሬንቶ ጉባኤ)። ስለዚህ ጉዳይ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከትውፊት ማስረጃ እናገኛለን ለምሳሌ፦ አንድ የሞተ ሰው ከኤልሳዕ ነቢይ አስክሬን ጋር በተገናኘ ጊዜ ወዲያውኑ በተአምራት ከሞት ተነሥቶ ቆመ (2 ነገሥት13፡ 21)። አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር በቅዱሳን መቃብር ላይ ተአምራት በመፈጸም የቅዱሳን አስክሬን መከበር እንዳለበት ያስረዳናል። የቀድሞ ክርስቲያኖችም የሰማዕታትን ሥጋ ያከብሩ ነበሩ። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ፓሊካርፓስ በሰማዕትነት በተቃጠለ ጊዜ የቀሩት አጥንቶቹን ሰቅመው ከወርቅ በላይ አከበሩት (ገድለ-ሰማዕታት)።

ቅዱሳን አስክሬናቸው ብቻ ሳይሆን ዕቃቸውም ክቡር ነው። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ጳውሎስ ገና በሕይወቱ እያለ በሽተኞች የእርሱን ልብስና መሐረብ ሲነኩ ከበሽታቸው ይፈወሱ ስለ ነበሩ ሕዝበ-ክርስቲያን ልብሱንና መሐረ ቡን ያከብሩት ነበር። (የሐዋ.ሥራ 19፡ 12)። በተሰይም አንድ ቅዱስ ወደ ሰማይ ከተሻገረ በኋላ ልብሶቹን፣ ዕቃዎቹንና ቤቱን ማክበር መልካም ነው። ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች በእምነትና በጸሎት ከነካናቸው አማላጅነታቸውን እናገኛለን።

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንን ዕቃዎችና ቦታዎች እንደዚህ ካከበረች፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዕቃዎችና እርሱ የተጠቀመባቸውን ነገሮች ወይም የሄደባቸውን ቦታዎች በበለጠ ታከብራለች። ለምሳሌ፦ ቤተል ሔም፣ ናዝሬት፣ በኢየሩሳሌም ደግሞ ጽርሐጽዮን፣ ጌተሴማኒ፣ ቀራንዮ ንና መቃብሩን ታከብራለች። እንዲሁም ቀሚሱን፣ መግነጥጡን፣ የእሾክ አክሊሉን፣ በተሰይም ደግሞ የተሰቀለበትን መስቀል ታከብራለች። እርሱ የተሰቀለበት መስቀል በብዙ ሥፍራ እንዲከበር በብዙ ቦታ ተቆራርጦ ወደ ተለያዩ አገሮች ታድሏል። እንግዲህ እነዚህን የተቀደሱ ነገሮች በ ምንሰለምባት፣ በምናከብርበት ጊዜ ግዙፍ ነገርን ለማምለክ ሳይሆን ፍቅርንና ክብርን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ለማቅረብ ፈልገን ነው።

እመቤታችን ማርያም የረገጠቻቸው ቦታዎችም ለምሳሌ፦ በናዝሬት ያለው ቤትዋ፣ የኤልሳቤጥ ቤት፣ በቢታንያ ያለው ቤትዋ የተከበሩ ናቸው። እሬ እንዲያውም እርስዋ በተአምራት የታየችባቸው ቦታዎችም የተከበሩ ናቸው። ብዙ ተአምራት ስለሚፈጸምባቸው ታቦት ተተክሉ ባቸው ደብር ሆነዋል። ደብረ-ሉርድና ደብረ-ፋጥማ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የመስቀልና የሥዕሎች አክብሮት

የመስቀል ሥዕልና ምስል ከስቅላት ጋርም ሆነ (የተሰቀለው የኢየሱስ ምስል ያለበት) ያለ ስቅለት ማክበር ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን የተለመደ ነው። በአሁኑ ጊዜ መስቀል በብዙ ቦታዎች ተከብሮ ይገኛል። በጸሎት ቤት፣ በመንበረ ታቦት ላይ በመናዘዣ ቦታ፣ በመቃብሮች ላይ፣ በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በሆስፒታል፣ በተራራዎች ጫፍ ላይ ሳይቀር ተተክሎና ተሰቅሎ ይገኛል። ብዙ ክርስቲያኖች በአን ገታቸው ላይ ያሥራሉ፣ ኧረ እንዲያውም አንዳንዶቹ በግንባራቸው ላይ ያስነቅሳሉ። አቡኖች በደረታቸው ላይ ያደርጋሉ፣ ካህናት በእጃቸው ይዘው በመዞር ሕዝቡን ያሳልማሉ። ይህ ልማድ የሚደነቅና የሚመሰገን ነው። ምክንያቱም የክርስቶስን ፍቅር ያጠነክርልናል። እንዲሁም የቅዱሳን ሥዕሎች፣ በተለይም የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ሁልጊዜ ተቀባይነት አላቸው።

በ8ኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ የቁስጥንጥንያ ነገሥታት በክርስትና ላይ ከፍተኛ ስደት አስነሡና ብዙ ሥዕሎችን እንደ ጣዖት ቆጥረው አቃጠሏቸው፣ አጠፏቸውም። የሮማው ጳጳስ ግን እነዚህን የሥዕል ጠላቶች አወገዟቸው። ከዚህም በኋላ አቡኖች በ2ኛው የኒቅያ ጉባኤ ላይ ተሰብስበው የጳጳስን አሳብ በመደገፍ «ሥዕሎች በሚከበሩበት ጊዜ የሚከበረው ወረቀቱ ወይም ዕንጨቱ ሳይሆን ራሳቸው ቅዱሳን ስለ ሆኑ የቅዱሳንን ሥዕል ማክበር መልካም ነው» ብለው አወጁ። ሌሎች ካልቪኒስት የሚባሉት መናፍቃን ተነሥተው መስቀልንና ሥዕሎችን ካጠፉ በኋላ ቤተ ክርስቲያን በትፌንቶ ጉባኤ ላይ እንደገና ለሥዕል ተከ ላከለችለት። ስለዚህ ዛሬ ሥዕሎች በሁሉ ቦታ ተዘርግተው ሕዝበ-ክርስ ቲያንን እያነጹ ናቸው።

በሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ሥዕልና ምስል ያለ ምንም ልዩነት ይከ በራል። በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ግን የስቅለት ምስል አይፈቀ ድም፣ የተቀረጸ የቅዱሳን ምስልም የለም። የመከልከሉ ምክንያት ግን አልተገለጸም። ምናልባት ምስሎች ጣዖትን ስለሚመስሉ አስወግደው ሊሆን ይችላል። ሕዝበ-ክርስቲያን ግን ምስልን ከጣዖት ጋር አያደባል ቁም። ስለዚህ ምስሎችን የምናስወግድበት ምክንያት የለንም።

ብዙ ፕሮቴስታንቶች እስከ ዛሬ ድረስ ምስሎችንና ሥዕሎችን ይነ ቅፋሉ። እግዚአብሔር ራሱ ከልክሎታል ብለው «ማንኛውንም ዓይነት ምስል ጣዖት አድርገህ አትሥራ» (ኦሪ.ዘጸ.20፡ 4) የሚለውን ጥቅስ ይ ጠቅሱልናል። ይህ ትእዛዝ የተጻፈው ግን ለእስራኤላውያን ብቻ ነበር፣ ምክንያቱም እስራኤላውያን ምስልና ሥዕልን ባዩ ጊዜ የመስገድ ዝንባሌ

ነበራቸው። በአሁኑ ጊዜ ግን ብዙ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች እንደ ተሻሻሉ ሁሉ ይህም ትእዛዝ መሻሻሉና መቅረቱ በቤተ ክርስቲያን ተገልጿል።

የሥዕሎች፣ በተለይም የመስቀል ጠላቶች ጀሆቫውያን ናቸው። እነዚህ ግን መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተመቻቸው እንጂ በቤተ ክርስቲያን መሪነት ስለማይተረጉሙት ይሳሳታሉ። በተጨማሪም የመስቀልን ታሪክ ምንም ስለማያውቁ፣ ክርስቶስ በአንድ ዕንጨት ላይ ነው እንጂ በተመሳ ቀለ እንጨት ላይ አልተሰቀለም ይላሉ። እኛ ግን የሮማውያንን ታሪክ አልረሳነውም። በሮማውያን ዘመን አንድ ሰው ለስቅላት ከተፈረደ እጆቹ የሚቸነከሩበትን ዕንጨት ራሱ ተሸክሞ ወደሚሰቀልበት ቦታ ይዛድ ነበር። ቋሚው ዕንጨት (ዛፍ) እዚያው ይቆያቸው ስለ ነበረ ሁለቱንም ዕንጨት አመሳቅለው ይቸነክሩት ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ልክ እንዲሁ አድርገው ቸነከሩት። ስለዚህ እኛ ከሁለት ዕንጨት የተሠራ ውን መስቀል ብናከብር ትክክለኞች ነን።

ምዕራፍ 18

ኦሥሩ የእግዚአብሔር ትእዛዛት



ሙሴ በደብረ ሲና ላይ ኦሥሩን የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተቀበለ (ኦሪ.ዘጸአት.31:18)

ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዛት እንድንጠብቅ በጥብቅ ታሳስበናለች። ምክንያቱም ኢየሱስ ሙሴ በደብረ-ሲና የተቀበላቸውን 10 ትእዛዛት ለመሻር አይደለም የመጣው (ማቴ.5፡ 17) እንዲያውም አሻሽሎና እንደ የራሱ ሕግ አድርጎ ፈጸማቸው። ሐዋርያቱንም «እኔ ያዘዝኋችሁን እንዲጠብቁና እንዲፈጽሙ ለሕዝብ ሁሉ አስተምሯቸው» ብሎ ላካቸው። ስለዚህ አሥሩን ትእዛዛት ከነትርጓሜአቸው ማወቅና በተግባር ላይ ማዋል ይገባናል። ትእዛዞቹም ከባድ አይደሉም።

1ኛ) ትእዛዝ፡- «ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ» (ኦሪት ዘዳግም 5፡ 7) የሚለው፣ እግዚአብሔር ፈጣሪያችንን (ሥላሴን) እንድናም ነው፣ እንድናከብረውና ያለ ስንፍናና ያለ መቀዝቀዝ እንድናገለግለው፣ እንዲሁም የሃይማኖትን ትምህርት ተግተን እንድንማር፣ የሃይማኖት ትምህርቶችን ሁሉ ያለ ጥርጥር እንድንቀበል፣ ጸሎትን በእምነት እንድናዘወትር ያዝዘናል። በተጨማሪም ክርስቲያናዊ ሃይማኖት ክሕደት፣ ከአምልኮ ጣዖት፣ ከጥንቆላና ሃይማኖታችንን ከሚጐዱት ነገሮች ሁሉ ይከለክለናል። ነገር ግን የቅዱሳንን ምስልና ሥዕል እንዳናከብር (ዛሬ በአዲስ ኪዳን) አይከለክለንም።

2ኛ) ትእዛዝ፡- «የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ» (ኦሪዘዳ 5፡ 11) የሚለው፣ በጸሎት እንጂ በግድ የለሽነት ወይም በጨዋታ፣ የባሰው ደግሞ በስድብ የእግዚአብሔርን፣ የማርያምንና የቅዱሳንን ስም እንዳንጠራ ይከለክለናል። እንዲሁም በትልቅ ምክንያት ካልሆነ በቀር እንዳንምል፣ በሐሰት ደግሞ በጭራሽ እንዳንምል ይከለክለናል።

3ኛ) ትእዛዝ፡- «ዕለተ ሰንበትን አክብር፣ ቀድሰውም» የሚለው፣ በሰንበትና በበዓላት ቀን ከባድ ሥራ ትተን፣ የመንፈሳዊነት ሥራ እንድንፈጽም ያዝዘናል። ከሁሉም በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደን ሥርዓተ-አምልኮውን በተለይም ቅዳሴውን መሳተፍ ተገቢ ነው። ምክንያቱም በሰንበት ቀን እቤት ውሎ የግል ጸሎት ብቻ ማድረግ በቂ አይደለም።

4ኛ) ትእዛዝ፡- «አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለው፣ ወላጆቻችንን እንድናከብራቸው፣ እንድናፈቅራቸውና እንድንታዘዛቸው፣ እንዲሁም እንዳንበድላቸውና እንዳናሳዝናቸው ያዝዘናል። ይህ ክብርና ተእዝዞ ለወላጆቻችን ብቻ ሳይሆን እንደ ወላጆቻችን ሆነው ለሚያገለግሉንም ይገባቸዋል። ለምሳሌ፡- ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለሚያሳድጉና ለሚንከባከቡ፣ ለአስተማሪዎች፣ ለሥራ መሪዎች፣... ወዘተ። በተለይም ለባለሥልጣኖች፣ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን አለቆች፣ ለማኅበር አለቆች፣ ለመንግ

ሥት ልኡካንም ይህ ክብርና ተአዝዞ ይገባቸዋል። (ሮሜ.13፡ 7)። በንጽሕናችን፣ በሃይማኖታችንና በጥሪያችን ተቃራኒ ለሚያዝዙን ግን ልንታዘዝላቸው አይገባም። በዚህ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ብቻ መታዘዝ ይገባናል (የዋሐ.ሥራ.5፡ 29)

5ኛ) ትእዛዝ፡- «አትግደል» የሚለው፣ ከሁሉም በላይ ሰውን እንዳንገድል ይከለክለናል፣ የሰው ሕይወት ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነውና (ኦሪ.ዘፍ.4፡ 10)። መግደል ብቻም ሳይሆን መማታት፣ መጣላት፣ መቆጣት፣ መሳደብ (ማቴ.5፡ 22) ጥላቻ፣ ቅንዓት... ወዘተ እንዳንፈጽም ይከለክለናል። እንዲሁም ለሰው እንቅፋት እንዳንሆን ይከለክለናል። ምክንያቱም ለሰው ዕንቅፋት መሆን ጉጂ ስለ ሆነ ነፍስን እንደ መግደል ይቆጠራል። በተጨማሪም ሁሉንም ሰው እንደ ራሳችን አድርገን እንድንወድ (ማቴ.22፡ 39)፣ ከበደልናቸው ሰዎች ጋር እንድንታረቅና ጠላቶቻችንን እንድንወድ (ማቴ.5፡ 44) ያዝዘናል።

6ኛ) ትእዛዝ፡- «አታመንዝር» የሚለው፣ የርክሰት ኃጢአትን በተግባርም ሆነ በአሳብ እንዳንፈጽም፣ እንዲሁም የሥጋን ምኞት የሚያነሳሱብንን ነገሮች (አመለካከት፣ ንግግር፣ ተግባር... ወዘተ) እንዳንፈጽም ይከለክለናል (ማቴ.5፡ 28)። ከሌሎች ሰዎች ጋር ከሚደረገው ኃጢአት ብቻ መቆጠብ በቂ አይደለም፣ ብቻህን ሆነህ ከሚደረገው ኃጢአትም መቆጠብ ይገባል። ይህ ነገር ያልገባቸው ሰዎች ከነፍስ-አባታቸው ጋር መማከር አለባቸው።

7ኛ) ትእዛዝ፡- «አትስረቅ» የሚለው፣ የሌሎችን ገንዘብ በስርቆት ወይም በዓመጽ እንዳንወስድ ይከለክለናል። የስርቆት ኃጢአት በፊጸም ነው ጉዳት መጠን ትልቅ ወይም ትንሽ ሆኖ ይቆጠራል። ሌቦች ተጸጽተው ከእግዚአብሔር ይቅርታን ለማግኘት ከፈለጉ፣ የሰረቁትን ገንዘብ ወይም ዕቃ ለባለቤቱ መመለስ አለባቸው።

8ኛ) ትእዛዝ፡- «ብማንም ሰው ላይ በሐሰት አትመስክር» የሚለው ሐሰተኛ ምስክርነትን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሐሰት እንዳንናገር (ማቴ.5፡ 37) እንዲሁም ወንድማችንን የሚጐዳ ሐሜታንና ክፉ ጥርጣሬን እንዳንፈጽም ይከለክለናል።

9ኛ) ትእዛዝ፡- «የሌላውን ሰው ሚስት አትመኝ» ይላል። ይህ ትእዛዝ የተጋቡ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት ከሚስቶቻቸው ጋር እንዲኖሩ እንጂ የሌለውን ሰው ሚስት እንዳይፈልጉና እንዳያገቡ ይከለክላቸዋል።

10ኛ) ትእዛዝ፡- «ያንተ ያልሆነውን ማናቸውንም ንብረት አት መኝ» ይላል። ያንተ ንብረት ያለሆነውን በስርቆት ወይም በዓመጽ ለመ ውሰድ ከተመኘህ፣ ባትሰርቀውም እንኳ እንደ ኃጢአት ይቆጠርብሃል፣ በሥራህና በጥበብህ ኑሮህን ለማሻሻል ከፈለግህ ግን መልካም ሆኖ ይቆ ጠርልሃል።

አስተውል

ስለ 5ኛው ትእዛዝ፡-

1. ሰውን በመልካም ምክንያት መምታት የፍቅር ሥራ ነው እንጂ ኃጢአት አይደለም። ለምሳሌ፡- ወላጆች ልጆቻቸውን አስተማሪዎ ችም ተማሪዎቻቸውን ለማረም ብለው ቢመቷቸው ለበሽተኛ እንደ ሚሰጠው መድኃኒት ይቆጠራል። «ልጅህን የማትቀጣው ከሆነ አትወደውም ማለት ነው» (ምሳሌ 13፡ 24)።

2. «አትግደል» የሚለው ትእዛዝ እንስሳትን እንዳንገድል አይከለክለ ንም። ምክንያቱም እንስሳት የተፈጠሩት ለጥቅማችን ነው። በእንስ ሳት ላይ ጨክኖ ማሰቃየት ግን ተገቢ አይደለም። በእንስሳት ላይ የሚጨክን በሰውም ላይ እንዳይጨክን ያስፈራል። በጥንት ዘመን፣ በግሪክ አገር አንድ ልጅ ወፍ ይዞ ዓይኑን አውጥቶ ስለ ለቀቀ በ መንግሥት ባለሥልጣን የሞት ፍርድ ተፈረደበት።

ስለ 6ኛ ትእዛዝ፡- በብዙ ምክንያቶች ከርክሰት ኃጢአት መራቅ ያስፈልገናል።

1. ይህንን ኃጢአት ብቻውን ወይም ከሌላ ሰው ጋር ሆኖ የሚፈጽም ክፉ ልምዶችን ስለሚለምድ የፍትወተ- ሥጋ ባርያ ይሆናል።

2. ርክሰት ሃይማኖትን እስከ መካድ የሚያደርስ ኃጢአት ነው፣ ስለ ዚህ አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔርን የማያመኑ ሰዎች ወደዚህ ክፉ ልማድ ስለ ወደቁ ናቸው (ቅዱስ አጎስጢኖስ)። ንጹሕ ልብ ያላቸው ግን እግዚአብሔር ያዩታል (ማቴ.5፡ 8)። በንጽሕናቸውም መላእክትን ይመስላሉ።

3. ይህ ኃጢአት ወደ ኩነኔ ያደርሳል፣ በገሃነም እሳት ውስጥ ያሉትም በዚህ ኃጢአት ነው የተኮነኑት፣ በሌላ ኃጢአት ቢኮነኑም ይህን ኃጢአት ሳይፈጽሙ አይቀሩም (ቅዱስ አልፎንሶ)።

4. ክፉ የርክሰት ልማድ ያላቸውን ሰዎች ብዙ ጊዜ የሥጋ በሽታም ያጠቃቸዋል፣ ሕይወታቸውም ተበላሽቶ ይገኛል።

እንግዲህ ይኽንን ፍኖ ትእዛዝ፣ ማለትም ንጽሕናን በሙሉ ኃይላችን እንጠብቀው። «መለኮታዊት ንጽሕና ሆይ! አንቺን የሚያገኝሽና ጸንቶም የሚይዝሽ ብፁዕ ነው። አንቺን ለማግኘት ለጊዜው መድከም አለበት፣ በኋላ ግን ባንቺ ዘንድ ትልቅ የደስታ ምክንያትን ያገኛልና» (ቅ. አትና ቴዎስ)።



በንጽሕና የሚኖር ሰው

ስድስቱ የቤተ ክርስቲያን ትእዛዛት

ቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ሕግ ለመደንገግ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ተቀብላለች። ምክንያቱም ጌታችን ለጴጥሮስ «በጕቼን ጠብቅ» (ዮሐ.21፡ 16) በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑን እንዲያስተዳድር ሥልጣን ሰጥቶታል። ለሁሉም ሐዋርያት ደግሞ «በምድር የምታስሩት

በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድር የምትፈቱትም በሰማይ የተፈታ ይሆ ናል» (ማቴ.18፡ 18)፣ «እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል» (ሉቃ.10፡ 16) አላቸው። ስለዚህ የሐዋርያት ወራሾች የሆኑት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳትና አቡ ኖች ሕግ ሊደነግጉ ይችላሉ፣ ማለትም ጳጳስ ብቻውን ወይም ከጉባኤ ጋ ር ሆኖ ለመላዋ ቤተ ክርስቲያን ሕግ ሊደነግግ ይችላል፣ እያንዳንዱ አቡ ን ደግሞ ለበላውን የሚመለከት ሕግ ወይም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ለመላዋ ቤተ ክርስቲያን በጳጳሳትና በጉባኤዎች የተወሰኑት ስድስቱ ትእዛዛት የሚከተሉት ናቸው።

1. በእሁድና በበዓላት ቀናት ቅዳሴ አስቀድስ፤
2. በዓመት አንድ ጊዜ በግድ ተናዘዝ፤
3. በፋሲካ ወራት ቁረብ፤
4. ቤተ ክርስቲያን ያዘዘችውን ጾም ጹም፤
5. ከአሥር አንድ (ፀሥራት) ለቤተክርስቲያን ስጥ፤
6. ባልተፈቀደ (ከማይገባ) ቀን ጋብቻ (ሠርግ) አታድርግ።

ለቡ፡- በነዚህ 6 ትእዛዛት ላይ ሌሎችም ትእዛዞችና ሥርዓቶች በመጽ ሐፈ ቀኖና (የቤተክርስቲያን ሕግ)፣ እንዲሁም በጳጳሳት ዐዋዲ ደብዳቤ ዎች ውስጥ ተጽፈው ይገኛሉ። እነዚህ በሙሉ ቢያንስ ለዓትመ.አዳም በደረሱ ሰዎች መታወቅ አለባቸው። በቁምስናዎች አስተምሮ በሚሰጥበት ጊዜ ሕዝቡ በጥንቃቄና በትጋት መከታተል አለበት። በገዛ ፈቃዳቸው ነገሩን ለማወቅ ካልፈለጉ ግን በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂዎች ናቸው።

ስለ ኃጢአት ማብራሪያ

የሰውን ልጅ ከሁሉም በላይ የሚጐዳው ኃጢአት ነው። ምክንያቱም ኃጢአት እግዚአብሔርን ይበድላል ነፍሳችንንም ያበላሻል። ከአዳም የወረስነው ኃጢአት የብዙ መከራ ምንጭ ነው፣ እሱ ግን በበደላችን የመጣ አይደለም። በደለኞች የሚያደርገን እኛ ራሳችን የምናደርገው ኃጢአት ነው። ይህ እኛ የምንፈጽመው ኃጢአት የእግዚአብሔርንና የቤተ ክርስቲያንን ሕግ በፍላጐታችን ማፍረስ ማለት ነው።

ኃጢአትን ሁሉ (ትልቁንም ትንሹንም) መጥላት ይገባናል። ምክንያቱ ም ኃጢአት እግዚአብሔር አባታችንን ያሳዝናል። በተለይም ደግሞ ከትልቅ ኃጢአት መራቅ ያስፈልገናል፣ ምክንያቱም ትልቅ ኃጢአት የነፍሳችን ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ይገፍፈናል፣ ወደ ገሃነም እሳትም ያወርደናል። ይህ ኃጢአት «ገዳይ ኃጢአት» ተብሎ ይጠራል።

ኃጢአት ሁሉ አድራጊውን (ፈጻሚውን) ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰቡንም ጭምር ይጐዳል። መልካም የሚያደርጉ ሰዎች በቅዱሳን ሱታፌ ኃይል

ሊለውን ሕዝብ እንደሚጠቅሙ ሁሉ፣ ክፉ የሚያደርጉትም ኃጢአታቸው ያልታወቀ ቢሆንም ሌሎችን ይጐዳሉ፣ የእግዚአብሔርን ቁጣ ይከሰከ ላሉ፣ ጭንቅና መከራንም ያመጣሉ። እንግዲህ በብዙ ምክንያቶች ኃጢአ ትን መጥላትና ማስወገድ አለብን።

ነፍሳችንን የሚገድል ትልቅ ኃጢአት የትኛው መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት እናገኛለን። ለምሳሌ፡ 1ቆሮ.6፡ 9-10፣ ገላ.5፡ 19-21፣ ራእይ.21፡ 8 ተመልከት። እነዚህን ክፉ ነገሮች በነፃ ነታቸውና በፍላጐታቸው የሚፈጽሙና ሳይጸጸቱ የሚሞቱ ሰዎች ለዘ ላለም ይኰነናሉ።

በጣም የሚያስደነግጡን ኃጢአቶች ጌ.ኢ.ክ. እንድናስወግዳቸው በጥብቅ ያስጠነቀቀን ናቸው (ማቴ.12፡ 31) እነርሱም መንፈስ ቅዱስን የመስደብ ኃጢአቶች ናቸው። ማለትም፡-

1. እግዚአብሔር አይምረኝም ብሎ ተስፋ መቁረጥ፤
2. ትልቅ ኃጢአትን ሳትናዘዝ እድናለሁ ብለህ ተስፋ ማድረግ፤
3. እውነተኛ ሃይማኖትን እያወቅህ አለማመን፤
4. በሌሎች ዕድል መቅናት፤
5. ሳትጸጸት በኃጢአት ጸንተህ መኖር፤
6. ንሰሐ ሳትገባ መሞት።

እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት የሚጮኹትን ኃጢአቶች (ኦሪዘፍ.ፋ 10) አጥብቀን ልንጠላቸውና ልንጸየፋቸው ይገባናል። እነሱም የሚከተ ሉት ናቸው።

1. በፍላጐትህ ሰውን መግደል፤
2. የሰዶም ኃጢአት፤
3. ድሆችን መበደል፤
4. የሠራተኖን ደመወዝ በዓመጽ መከልከል።


እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን አምነው ከልባቸው ለሚጸጸቱት ምሕ ረትን ያወርድላቸዋል። ኧረ እንዲያውም ተጸጽቶ ንስሐ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል። (ሉቃ.15፡ 7)። ብዙ ሰዎች ግን ጎሊናቸው ስለ ደነዘዘ ብዙ ክፉ ነገሮችን ከፈጸሙ በኋላ አይጸጸቱም። «ምን አለበት?» እያሉ ኃጢአታቸውን ተንተርሰው ይተኛሉ። ይህ ከፍ ተኛ ጉዳት ነው፣ ምክንያቱም ሰዎች ኃጢአት መሥራታቸውን በጎሊናቸ ው ሳያምኑ ሲጸጸቱና ምሕረት ሲያገኙ አይችሉም። በእውነቱ «የዘመና ችን ትልቁ ክፋት ኃጢአት ሠርቻለሁ የሚል ስሜትን ማጥፋት ነው» (ጳጳስ ፒዮስ 12ኛ)።

ከዚህ የጎሊና መደንዘዝ ለመዳን የእግዚአብሔርንና የቤተ ክርስቲያንን ሕጎች በደንብ እንማር፣ እናስበውም። የእግዚአብሔርን ትምህርት በቃን የምንልበት ደረጃና ጊዜ የለም። በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍላጐት ለማወቅና ለመፈጸም ተግተን መጣጣር አለብን። «እግዚአብሔር ሆይ! ከብዙ ወርቅና ከብዙ ብር ይልቅ ለእኔ እጅግ ዋጋ ያለው አንተ የምትሰጠው ሕግ ነው» (መዝ.119፡ 72)።

የሁሉ ኃጢአት ምንጭ የሆኑትን ክፉ ዝንባሌዎች በሙሉ ኃይላችን ልንቃወማቸውና ልናስወግዳቸው ይገባናል። እነርሱም «ትዕቢት፣ ንፍገት፣ ዝሙት፣ ቁጣ፣ ስግብግብነት፣ ቅናት፣ ስንፍና» ናቸው።

ከትናንሽ ኃጢአቶችም ተጠንቅቀን መራቅ ይገባናል፣ ምክንያቱም «ትናንሽ ጉድለቶችን ቸል የሚል፣ ቀስ በቀስ ወደ ትልቅ ኃጢአት ይወድቃል» (ሲራ.ክ.19፡ 1)። እንዲሁም በሰብአዊ ደካማነታችን ወደ ኃጢአት ከወደቅን ቶሎ ብለን ኃጢአታችንን አምነን መናዘዝ አለብን እንጂ መደበቅና መካድ የለብንም። «ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዘ፣ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይልልናል። ኃጢአት አልሠራንም ብንል፣ እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፣ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ዮሐ.1፡ 9-10)።

ምዕራፍ 19
የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት



የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት እንደ ጸጋ መሰና ሆነው ነፍሳችንን ይመላሉ

እኛ እንድንድን ጌ.ኢ.ክ. ሞቶልናል ማለት ብቻ አይበቃንም፣ የሕማማቱንና የሞቱን ፍሬና ትሩፋት መቀበል ያስፈልገናል። ይህም የሚፈጸመው በምሥጢራት ነው። ብዙ ሰዎች ምሥጢራትን ስለማይቀበሉ፣ ወይም ደግሞ በደንብ ተዘጋጅተው በጥሩ ሁኔታ ስለማይቀበሏቸው፣ የኢየሱስን ሞት ሳይጠቀሙበት ይቀራሉ።

ምሥጢራት ማለት ሰዎች እንዲጸድቁ፣ በሚታይ ሁኔታ የማይታየውን ጸጋ እንዲሰጡ ጌ.ኢ.ክ. የሠራቸው ምልክቶች ናቸው። ምሥጢራት ከኢየሱስ ጋር ያገናኙናል፣ መለኮታዊ ሕይወት እንድንቀበል ያደርጉናል። ምሥጢራትን ያለ ምንም ዕንቅፋት በሥነ-ሥርዓት ከተቀበልናቸው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትሩፋት የሚያጸድቅ ጸጋንና የየራሳቸው የሆነ ምሥጢራዊ ጸጋን ይሰጡናል።

ምሥጢራት ሰባት ናቸው፣ እነሱም፡- ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ መጽሐፈ-ቀንዲል፣ ክህነት፣ መጽሐፈ- ተክሊል ናቸው። ይህ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ባይኖርም፣ በቤተክርስቲያን ትውፊት ሐዋርያት ያስተላለፉልን ትምህርት ስለሆነ የተረጋገጠ ነው። የትሬንቶ ጉባኤ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1545 ዓ.ም. «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምሥጢራት እንደሌሉ፣ ወይም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንዳልተሠሩ፣ ወይም ከሰባት እንደሚያንሱ ወይም እንደሚበልጡ አድርጐ ሰ መናገር ወይም ለማስተማር የሚደፍር የተወገዘ ይሁን» ብሎ አውጇል።

ከምሥጢራት የምንቀበለው አጽዳቂ ወይም ቀዳሽ ጸጋና የመለኮታዊ ሕይወት ሱታፌ ስለሆነ ከሁሉም ነገር በላይ ተግተን መከታተልና መቀበል ይገባናል። ያለ ምሥጢራት ድኅነት የለምና። ጌ.ኢ.ክ. እንዳለው (ማቴ.22፡ 12) የሠርግ ልብስ ያልለበሰ ወደ ሠርግ አዳራሽ መግባት እንደማይችል ሁሉ፣ ይህን ጸጋ የሌለውም ወደ ዘለዓለማዊው አዳራሽ ሊገባ አይችልም። እያንዳንዱ ምሥጢር ለእኛ የሚሰጠን የየራሱ የሆነ ልዩ ጸጋ አለው።

የአኩኖ ቅዱስ ቶማስ እንደሚያስተምረን፣ ምሥጢራት በሥጋዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚገኙትን ሁኔታዎች ይመስላሉ። ማለትም ሰው በሥጋዊ ሕይወት 1) ይወለዳል፣ 2) ያድጋል፣ ይጠነክራልም፣ 3) ይመገባል፣ 4) ከታመመ መድኃኒት ይወስዳል፣ 5) በጠና የታመመ እንደሆነ ልዩ እንክብካቤ ይደረግለታል፣ 6) ይህን እንክብካቤ ወላጆች ያደርጉለታል፣ 7) ከሌሎች መሪዎችም ያገኛል።

እንዲሁም ሰው በመንፈሳዊ ሕይወት 1) በጥምቀት ይወለዳል፣ 2) በሜሮን ያድጋል ይጠነክራልም፣ 3) በቅ.ቁርባን ይመገባል፣ 4) ከጉድለት

በኑዛዜ ይድናል፤ 5) በጠና የታመመ እንደሆነ በመጽሐፈ-ቀንዲል መጽናናትን ያገኛል፤ 6) በምሥጢረ-ክህነት የነፍሱን መሪዎች ያገኛል፤ 7) በምሥጢረ-ተክሊል ደግሞ አዲስ ቤተሰብን ይመሠርታል።

አሁን ደግሞ ስለ እያንዳንዱ ምሥጢር ልዩ ትምህርት አጠር አድርገን እንመለከታለን።

1ኛ ምሥጢረ-ጥምቀት

ጥምቀት ማለት የአዳምን ኃጢአት ደምስሶ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞች፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያና የክርስቲያን ማኅበር አባሎች የሚያደርገን ምሥጢር ነው። ጌኢ.ክ «ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» (ዮሐ.3፡ 5) በማለት ጥምቀት ለድኅነታችን አስፈላጊ መሆኑን ገለጸ። ከዕርገቱ በፊት ደግሞ «ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱና አጥምቋቸው» ብሎ አዘዛቸው (ማቴ.28፡ 19)።

ጥምቀት በሁለት መንገዶች ሊሰጥ (ሊፈጸም) ይችላል፣ ማለት ተጠማቂው በሙሉ ሰውነቱ በውሃ ውስጥ ገብቶ ሳለ ውሃውን እሳዩ ላይ ታፈስለታለህ። ወይም ደግሞ ተጠማቂው ውሃ ውስጥ ሳይገባ በራሱ ላይ ብቻ ውሃ ታፈስለታለህ። ሁለቱም መንገዶች ጥሩ ናቸው። አጥማቂው ግን ራሱ ውሃ ማፍሰስና ቃላቱን መድገም አለበት። አስፈላጊው ቃላት ይህ ነው «እኔ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ» ብሎ መናገር አለበት።

ጥምቀት እንዲሰጣቸው፣ በዕድሜ የደረሱ ሰዎች አምነውና ራሳቸው ጥምቀትን ለምነው የክርስትናን ሕጎች ሁሉ ለመጠበቅ ተስፋ መስጠት አለባቸው። ሕፃናት ግን በወላጆቻቸው ወይም በክርስቲያን ማኅበር ኃላፊነት ነው የሚጠመቁት። ሐዋርያት አንዳንድ ቤተሰቦችን ወደ ክርስትና ሲመልሱ ትልልቆችንና ትናንሾችን ሳይለዩ ያጠምቁ ነበር። (የሐዋ.ሥራ፡ 16፡ 33፣ 1ቆሮ.1፡ 16)። ስለዚህ ሕፃናት አሳዳጊዎች ካሏቸው ቶሎ እንዲጠመቁ ጉባኤዎችና ጳጳሳት ያዝዛሉ። ምክንያቱም በትንሽነታቸው የአዳም ኃጢአት እንዲደመሰስላቸውና የቤተ ክርስቲያን ልጆች መሆንን መጀመር በጣም ትልቅ ጥቅም ነው። ሕፃናት ከተጠመቁ በኋላ ከሞቱ የመንግሥተ-ሰማይ ወራሾች እንደሚሆኑ የተረጋገጠ ነገር ነው። ሳይጠመቁ የሞቱትስ? ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ 2ኛ «የእግዚአብሔርን ምሕረት እንለምንላቸዋለን» ይላሉ። ይህም ማለት ስለ መዳናቸው አላረጋገጡ

ልንም። በአሁኑ ጊዜ ግን ያልተጠመቁት ሕፃናት ወደ ሲኦል ይሄዳሉ የሚል የለም፣ ምክንያቱም አነርሱም በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄዱ እናስባለን። የሆነ ሆኖ አንድ ያልተጠመቀ ሕፃን በሞት አፋፍ ላይ መሆኑን ካየን የማጥመቅ ግዴታ አለብን።



በዲያቆን ፊልጶስ የተጠመቀው መጀመሪያ ኢትዮጵያዊ (የሐዋ.ሥራ፡ 8፡ 38)

አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠምቀው ካህን (ቄስ) ነው። እርሱ ካልተገኘ ግን፣ ስለ ጥምቀት የተማረ ማንም ሰው ሊያጠምቅ ይችላል። የተጠመቁት ህፃናት ካደጉ በኋላ፣ የተቀበሉትን ሚስጥር አውቀው ፍሬ እንዲያፈ

ሩበት መኰትኰት (ማስተማር) ነው እንጂ ሁለተኛ ጊዜ ማጥመቅ አይቻልም። ምክንያቱም ሁለተኛ ጥምቀት በጭራሽ አይታሰብም። ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚሰጠው፤ የራሱ የሆነ ልዩ ማኅተም አለው። ጳጳስ ሲሪችዩስ ኤ.ኤ.አ በ384 ዓ.ም. እንደ ገለጸው ጥምቀት በአርዮሳውያንም ወይም በሌሎች መናፍቃንም ቢሰጥ ሊደገም አይችልም።

በውሃ ጥምቀት ፋንታ፣ የደም ጥምቀት የሚባል ሰማዕትነት ወይም የእሳት ጥምቀት የሚባል የፍላጐት ጥምቀት፣ ለድኅነት በቂ ነው። ሌሎችን ምሥጢራት ለመቀበል ግን መጀመሪያ የውሃ ጥምቀት መቀበል ግዴታ ነው። ክርስቲያን ያልሆኑት ሕዝብ፣ ሕይወታቸውን በመልካም ሁኔታ ከመሩ፣ ያለ ጥምቀት ከእግዚአብሔር ደኅንነትን እንደሚያገኙ እናምናለን። ነገር ግን የእግዚአብሔር የምሕረት መንገድ ብዙ ስለ ሆነ በየትኛው መንገድ መሆኑን አናውቅም።


2ኛ) ምሥጢረ-ሜሮን

ሜሮን ክርስቲያንን አጠንክሮ የክርስቶስ ወታደር የሚያደርግ፣ መንፈስ ቅዱስን አብዝቶ የሚሰጠውና ልዩ ማኅተምን የሚያትምለት ሥሥጢር ነው። ይህ ምሥጢር ለድኅነት በግድ አስፈላጊ አይደለም፣ ኑሱን የማይቀበል ግን መክሰሩ አይቀርም፣ ፍጹም ክርስቲያን ለመሆን መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገዋልና።

ሐዋርያት ያደርጉት እንደ ነበሩ ሁሉ (የሐዋ.ሥራ.8፡ 17) ሜሮን ከጥምቀት በኋላ ይሰጣል። ምሥራቃውያን አንድ ሕፃን ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ሜሮንም ይቀቡታል። ምዕራባዊት ቤተ ክርስቲያን ግን ልጆች ወደ 10 ዓመት አካባቢ ሲሆናቸው ሜሮን እንዲሰጣቸው ወሰነች። ምክንያቱም ልጆች በዚህ ዕድሜያቸው የሜሮንን ትልቅነትና ጥቅም ሊረዱት ይችላሉ።

ሜሮንን የሚሰጥ አቡን ነው። እርሱ በተቀቢዎቹ ላይ እጁን ጭኖ መንፈስ ቅዱስን ይለምንላቸዋል፣ ቀጥሎም በእያንዳንዱ ተቀቢ ግንባር ላይ የተባረከ ቅዱስ ቅባት ይቀባል፣ በሚቀባበትም ጊዜ የሚከተለውን ቃላት ይደግማል፣ «እኔ በመስቀል ምልክት አማትብሃለሁ፣ በድኅነት ቅባት ደግሞ አጸናሃለሁ፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም»።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማስረጃ



የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የክርስቲያን መንፈሳዊ ኃይሎችን ያበለጽጋሉ

በጥምቀትና በሜሮን የተቀበልነው መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ አድሮ በስጦታዎቹ ይመራናል። በሥራው፣ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አድርጉ ይቀድሰናል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በጣም አስፈላጊ ስለ ሆኑ ጠለቅ ብለን እንመልከታቸው።

አቡን በምሥጢረ-ሜሮን የሚለምኑልን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሰባት ናቸው እነሱም፡- ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ምክር፣ ጽናት፣ ዕውቀት፣ መንፈሳዊነትና እግዚአብሔርን መፍራት ናቸው (ኢሳ.11፡ 2)። እነዚህም ክርስቲያናዊ ኃይሎችን (እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ ጥበብ፣ ፍትሕ፣ ጽናትንና በመጠን መኖርን) በቀላሉ እንድንለብስና እንድናዘወትር ያግዙናል። ከእነዚህም ሌላ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ 20 የሚሆኑ ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይዘረዝርልናል። ለምሳሌ፡- በጥበብ መናገር፣ በዕውቀት መናገር፣ እምነት፣ የመፈወስ ስጦታ፣ ተአምራትን የማድረግ

ኃይል፣ ትንቢትን መናገር፣ የመንፈስ ስጦታዎችን የመለየት ችሎታ፣ በአዲስ ቋንቋ የመናገር ችሎታ፣ አዲስ ቋንቋዎችን የመተርጐም ችሎታ (1ቆሮ.12፡ 7-11)፤ አገልግሎት፣ ማስተማር፣ መምከር፣ መለገስ፣ ማስተዳደር፣ ምሕረት ማድረግ (ሮሜ.12፡ 6-8)፣ እንዲሁም ኤፌሶን.4፡ 11-13 ተመልከት። እነዚህ ስጦታዎች የሚታደሉት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለሆነ ሁላችንም ሁሉን ስጦታዎች አጠቃልለን አንቀበላቸውም፣ ነገር ግን እንደ ሥራችን፣ እንደ አገልግሎታችንና እንደ ኃላፊነታችን የሚያስፈልጉን ስጦታዎች በየዓይነቱ ይሰጠናል።


ቅዱስ ጳውሎስ የጠቀሳቸው ስጦታዎች ሁሉም አይደሉም፣ ምክንያቱም ገና ያልተጠቀሱም አሉ። ከሁሉም የበለጠ ስጦታ ፍቅር ነው። (1ቆሮ.12፡ 31)። በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ እስከ 9 የሚደርሱ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ይጠቅስልናል። እነሱም፡- ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ደግነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነትና ራስን መግዛት ናቸው። (ገላትያ.5፡ 22)። በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ሃብት በእውነቱ በጣም ትልቅ ነው። እንደ ጸሎታችንና ምሥጢራትን (ጉዛዜንና ቅ.ቁርባንን) እንደ ማዘውተራችን መጠን መንፈስ ቅዱስ ይቀድሰናል። እኛም በእምነትና በትጋት እንከተለው እንጂ አንቃወመው። ቅዱስ ጳውሎስ «መንፈስ ቅዱስን አታናድዱት» ይለናል። ማለትም በኃጢአት ወይም በክፉ ጠባይ አትበድሉት ማለቱ ነው። እንዲሁም የተቀበልነውን ስጦታ ፍሬ እና ፍራቡት እንጂ የጌታውን ገንዘብ መሬት ቆፍሮ እንደ ቀበረው ሰነፍ አገልጋይ (ማቴ.25፡ 25) አንሁን ማለት ነው።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ትምህርት አለ። «ተሐድሶ» በሚባለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውስጥ ከተሳተፍን ይኸንን በደንብ መማር ብቻ ሳይሆን ጉበዞች የአግዚአብሔርና የኅብረተሰብ አገልጋዮች ልንሆን እንችላለን።

3ኛ ምሥጢረ ቅዱስ ቁርባን

ቅዱስ ቁርባን በኅብስትና በወይን መልክ፣ በእውነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ፣ ደም፣ ነፍስና መለኮትን የያዘ ምሥጢር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንጀራውን ካበረከተ በኋላ ለአይሁድ ይህን ሥጢር አበሠራቸው፣ «ለዓለም ሕይወት እንዲሆን እኔ የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» (ዮሐ.6፡ 51)፣ «ሥጋዬ እውነተኛ መብል፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው።» «ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ ሁሉ በእኔ ይኖራል፣ እኔም በእርሱ እኖራለሁ» አላቸው። (ዮሐ.6፡ 55)

የሠራውም በሕማማቱ ዋዜማ ነው። ማለትም እንጀራውን አንሥቶ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ እንጀራውን ወደ ሥጋው ለወጠው፣ ወይን ያለበትን ጽዋ አንሥቶ ደግሞ «ይህ ደሜ ነው» ብሎ ወይኑን ወደ ደሙ ለወጠው። ሐዋርያት እንዳስተላለፉልን ጌ.ኢ.ክ. በእነዚህ ቃላት ኅብስቱንና ወይኑን ወደ እውነተኛ ሥጋውና ደሙ ለውጧል። «ይህ የሥጋዬ አምሳያ ነው ማለቱ ነው። የሚለው አባባል መናፍቅነት ነው» (የትሬንቶ ጉባኤ)። ጌ.ኢ.ክ. «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» በማለቱ፣ ይህንን የመለወጥ ሥራ እንዲፈጽሙ ለሐዋርያቱና ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት ካህናት በሙሉ ሥልጣን ሰጣቸው።



ጌ.ኢ.ክ. ከሁሉም የበለጠ ስጦታው የሆነውን ቅዱስ ቁርባን ሠራ (ማቴ.26፡ 26)

ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ይህንን ምሥጢር አክብራለች፣ ከመናፍቃን ስሕተትም ጠብቃለች። ብረንጋርዮስ «በቅዱስ ቁርባን የኢየሱስን መንፈስ እንጂ ሥጋውን አንቀበልም» ስላለ፣ ጳጳስ ኒኮላውስ 2ኛ እ.ኤ.አ. በ1059

ዓ.ም. በሮማ ላይ ጉባኤ ጠርቶ «በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ጌ.ኢ.ክ. በእውነተኛ ሥጋው ይገኛል፣ ማለትም ከእመቤታችን ማርያም የተወለደ፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለውና በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ያለው ኢየሱስ ነው በቅዱስ ቁርባን ውስጥ የሚገኘው» የሚለውን ትምህርት እንዲያምን አዘዘው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን ፕሮቴስታንቶች ቅዱስ ቁርባንን ሲክዱ፣ ካቶሊካውያን አቡኖች በትሬንቶ ጉባኤ ላይ ተሰብስበው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መርምረው፣ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው (ዮሐ.16፡ 13) እውነተኛውን ትምህርት እንደሚከተለው አድርገው ገለጹ። ክርስቲያን በሙሉ ይህንን ትምህርት ማመን ግዴታ ቸው ነው።

1. በምሥጢረ ቅዱስ ቁርባን ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ፣ ደም፣ ነፍስና መለኮት አለ። ጌ.ኢ.ክ. በሙሉ፣ በእው ነትና በተጨባጭ ይገኛል እንጂ በአምሳያ ወይም በምልክት ወይም በኃይል አይደለም።

2. በምሥጢራዊ ተአምራት፣ ሙሉ የእንጀራ ህላዌ ወደ ኢ.ክ. ሥጋ፣ ሙሉ የወይን ህላዌ ወደ ደሙ ስለሚለወጥ፣ ከመልኩ በቀር እንጀራና ወይኑ በጭራሽ ይጠፋል።

3. ጌ.ኢ.ክ. ሕያው ስለሆነ፣ ሥጋውና ደሙ አይለያዩምና በእን ጀራ መልክ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ይገኛል፣ መልኩ ከተሰበረም በሁሉም ፍርፋሪ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ይገኛል። እንዲሁም በወይን መልክ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ስለሚገኝ፣ በአንድ መ ልክ ብቻ (በእንጀራ መልክ ወይም በወይን መልክ ብቻ) የሚ ቀርቡት ሙሉ ኢየሱስን ይቀበላሉ።

4. በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ምንም እንኳ የህላዌው ሁኔታ በ ምሥጢራዊ መንገድ ቢሆንም ጌ.ኢ.ክ. በሁሉንተናው ይገኛል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚገባውን አክብሮትና ስግደት ልናቀርብለት ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ በሕብረት ማደብና በ ዑደት ልናከብረው ይገባናል። ይህንን እንደ «አምልኮ ጣዖት» የሚቆጥሩት ሰዎች በስሕተት ላይ ይገኛሉ።

በእውነቱ ምሥጢረ ቁርባን በጣም አስደናቂ ነገር ነው፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ. በሰማይ እያለ፣ እርሱ አንድ ሆኖ ሳለ፣ በምድርም ማለትም በተባረከው የቁርባን ጎብስት ሁሉ በእውነተኛ ሥጋው ይገኛል። ጌ.ኢ.ክ. የነፍሳችን ምግብ መሆን ስለ ፈለገ ነው ይህንን መለኮታዊ ዘዴ የፈጠረ

ው። እኛ እንድንበላው ብሎ የምግብንና የመጠጥን መልክ ወሰደ። ደጋ ግሞም ይጋብዘናል። (ዮሐ.6፡ 53-54)። ስለዚህ እንጠቀምበት።

ቅ.ቁርባንን ለመቀበል የሚያስፈልጉን ነገሮች የሚከተሉት ናቸው

1. ክትልቅ ኃጢአት የነጻን መሆን ይገባናል። ትልቅ ኃጢአት ያለው ሰው መናዘዝ አለበት፣ አለበለዚያ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨም ራል። ጸጸት ብቻውን ምንም እንኳ ፍጹም ቢሆንም በቂ አይደለም። «ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ ሳለ የጌታን ጎብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ፣ በጌታ ሥጋና ደም ባለ ዕዳ ይሆናል» (ለቆሮ.11፡ 27)። ትንሽ ኃጢአት ብቻ ያለው ሰው ወይም ስለ ትልቅ ኃጢአት የሚጠራጠር፣ ተጸጽቶ ሳይናዘዝ ሊቆርብ ይችላል፣ ከተናዘዘ ግን የበለጠ ጸጋ ያገኛል።

2. ቀና አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል፣ ማለትም፣ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ለነፍሳችን ጥቅም ብለን መቁረብ አለብን እንጂ በሥጋዊ ምክንያት ወይም የሰውን ዓይን አፍረን መቁረብ የለብንም፣ በእምነ ትና በመንፈሳዊነት ተዘጋጅተን መቁረብ አለብን። ከቆረብንም በኋላ የምስጋና ጸሎት ማድረስ ይገባናል።

3. ከመቁረባችን በፊት መጾም ይገባናል፣ በአሁኑ ጊዜ ግን የጾም ነገ ር በጣም ቀላል ሆኗል፣ ምክንያቱም [redacted]። ውሃና መ ድኃኒት ግን በማንኛውም ጊዜ [redacted] አይደለም፣ በሽተኞች ደግሞ ከማንኛውም ጾም ነጻ ናቸው።

ቅ.ቁርባንን መቀበል ለድኅነት አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ. «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ የሆነውን (የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም» ብሎ ሰብኳል (ዮሐ.6፡ 53)። ይህ ንግግሩ ለዕድሜ የደረሱትን ሰዎች ያመለክታል። ሕፃናት እንዲቆርቡ ግዴታ ስላልሆነ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ካደጉ በኋላ፣ ቢያንስ 7 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ተዘጋጅተው እንዲቆርቡ ትፈቅድላቸዋለች። ከጀመሩ በኋላ ግን እንደ ሁሉም ምእመናን ዘወትር እንዲቆርቡ ታሳስባቸዋለች።

ዓ.ም. በሮማ ላይ ጉባኤ ጠርቶ «በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ጌ.ኢ.ክ. በእውነተኛ ሥጋው ይገኛል፣ ማለትም ከእመቤታችን ማርያም የተወለደ፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለውና በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ያለው ኢየሱስ ነው በቅዱስ ቁርባን ውስጥ የሚገኘው» የሚለውን ትምህርት እንዲያምን አዘዘው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን ፕሮቴስታንቶች ቅዱስ ቁርባንን ሲክዱ፣ ካቶሊካውያን አቡኖች በትሬንቶ ጉባኤ ላይ ተሰብስበው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መርምረው፣ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው (ዮሐ.16፡ 13) እውነተኛውን ትምህርት እንደሚከተለው አድርገው ገለጹ። ክርስቲያን በሙሉ ይህንን ትምህርት ማመን ግዴታቸው ነው።

1. በምሥጢረ ቅዱስ ቁርባን ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ፣ ደም፣ ነፍስና መለኮት አለ። ጌ.ኢ.ክ. በሙሉ፣ በእውነትና በተጨባጭ ይገኛል እንጂ በአምሳያ ወይም በምልክት ወይም በኃይል አይደለም።

2. በምሥጢራዊ ተአምራት፣ ሙሉ የእንጀራ ህላዌ ወደ ኢ.ክ. ሥጋ፣ ሙሉ የወይን ህላዌ ወደ ደሙ ስለሚለወጥ፣ ከመልኩ በቀር እንጀራና ወይኑ በጭራሽ ይጠፋል።

3. ጌ.ኢ.ክ. ሕያው ስለሆነ፣ ሥጋውና ደሙ አይለያዩምና በእንጀራ መልክ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ይገኛል፣ መልኩ ከተሰበረም በሁሉም ፍርፋሪ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ይገኛል። እንዲሁም በወይን መልክ ውስጥ ሙሉ ኢየሱስ ስለሚገኝ፣ በአንድ መልክ ብቻ (በእንጀራ መልክ ወይም በወይን መልክ ብቻ) የሚቆርቡት ሙሉ ኢየሱስን ይቀበላሉ።

4. በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ምንም እንኳ የህላዌው ሁኔታ በምሥጢራዊ መንገድ ቢሆንም ጌ.ኢ.ክ. በሁለንተናው ይገኛል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚገባውን አክብሮትና ስግደት ልናቀርብለት ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ በሕብረት ማጀብና በዐደት ልናከብረው ይገባናል። ይህንን እንደ «አምልኮ ጣዖት» የሚቆጥሩት ሰዎች በስሕተት ላይ ይገኛሉ።

በእውነቱ ምሥጢረ ቁርባን በጣም አስደናቂ ነገር ነው፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ. በሰማይ እያለ፣ እርሱ አንድ ሆኖ ሳለ፣ በምድርም ማለትም በተባረከው የቁርባን ጎብስት ሁሉ በእውነተኛ ሥጋው ይገኛል። ጌ.ኢ.ክ. የነፍሳችን ምግብ መሆን ስለ ፈለገ ነው ይህንን መለኮታዊ ዘዴ የፈጠረው። እኛ እንድንበላው ብሎ የምግብንና የመጠጥን መልክ ወሰደ። ደጋግሞም ይጋብዘናል። (ዮሐ.6፡ 53-54)። ስለዚህ እንጠቀምበት።

ቅ.ቁርባንን ለመቀበል የሚያስፈልጉን ነገሮች የሚከተሉት ናቸው

1. ክትልቅ ኃጢአት የነጻን መሆን ይገባናል። ትልቅ ኃጢአት ያለው ሰው መናዘዝ አለበት፣ አለበለዚያ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራል። ጸጸት ብቻውን ምንም እንኳ ፍጹም ቢሆንም በቂ አይደለም። «ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ ሳለ የጌታን ጎብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ፣ በጌታ ሥጋና ደም ባለ ዕዳ ይሆናል» (ለቆሮ.11፡ 27)። ትንሽ ኃጢአት ብቻ ያለው ሰው ወይም ስለ ትልቅ ኃጢአት የሚጠራጠር፣ ተጸጽቶ ሳይናዘዝ ሊቆርብ ይችላል፣ ከተናዘዘ ግን የበለጠ ጸጋ ያገኛል።

2. ቀና አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል፣ ማለትም፣ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ለነፍሳችን ጥቅም ብለን መቁረብ አለብን እንጂ በሥጋዊ ምክንያት ወይም የሰውን ዓይን አፍረን መቁረብ የለብንም፣ በእምነትና በመንፈሳዊነት ተዘጋጀተን መቁረብ አለብን። ከቆረብንም በኋላ የምስጋና ጸሎት ማድረስ ይገባናል።

3. ከመቁረባችን በፊት መጾም ይገባናል፣ በአሁኑ ጊዜ ግን የጾም ነገር በጣም ቀላል ሆኗል፣ ምክንያቱም ከእኩለ ሌሊት ጀምረን ሳይ ሆን ለአንድ ሰዓት ብቻ ከምግብ መከልከል ይበቃናል። ውሃና መድኃኒት ግን በማንኛውም ጊዜ ክልክል አይደለም፣ በሽተኞች ደግሞ ከማንኛውም ጾም ነጻ ናቸው።

ቅ.ቁርባንን መቀበል ለድኅነት አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ. «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ የሆነውን (የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም» ብሎ ሰብኳል (ዮሐ.6፡ 53)። ይህ ንግግሩ ለዕድሜ የደረሱትን ሰዎች ያመለክታል። ሕፃናት እንዲቆርቡ ግዴታ ስላልሆነ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ካደጉ በኋላ፣ ቢያንስ 7 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ተዘጋጅተው እንዲቆርቡ ትፈቅድላቸዋለች። ከጀመሩ በኋላ ግን እንደ ሁሉም ምእመናን ዘወትር እንዲቆርቡ ታሳስባቸዋለች።



ቅ.ቁርባንን የሚሠሩልን አቡናትና ካህናት ናቸው

ቅዳሴ በየቀኑ ስላለ ቅዱስ ቁርባን አብዛኛውን ጊዜ በጎብኝት መልክ ብቻ ይታደላል፣ ኢየሱስ በአንዱ ብቻ ሙሉ ነውና። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም ለበሽተኞችና ለእሥረኞች በጎብኝት መልክ ብቻ ይልኩ ላቸው ነበር፣ ለሕፃናት ደግሞ በወይን መልክ ብቻ ያድሏቸው ነበሩ። እኛ ስለ እምነትና ፍቅር እንጂ ስለ አሰጣጡ ሁኔታ መቸገር የለብንም።

ቅዱስ ቁርባንን በመልካም ሁኔታ ዘወትር የሚቀበሉ ሰዎች ብዙ ጥቅም ያገኛሉ፡- የእግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር ይጨመርላቸዋል፣ ትናንሽ ኃጢአታቸው ይደመሰስላቸዋል፣ ትልቅ ኃጢአት ከመፈጸም ይጠበቃሉ፣ መንፈሳዊ መጽናናት ይሰጣቸዋል፣ በዚህ ዓለም እያሉ ከክርስቶስ ጋር ይዋሐዳሉ፤ የዘለዓለማዊ ሕይወትና ትንሣኤ ዋስትና ያገኛሉ (ዮሐ፡ 54)።

ከቆረብን በኋላ በሙሉ ልባችን ጌኢክርስቶስን ለማመስገንና የሚያስ ፈልገንን ጸጋ ለመለመን ምቹ ጊዜ ነው። ምክንያቱም እርሱ በልባችን ውስጥ ስላለ ለሩብ ሰዓት የሚሆን እንደ እምነታችንና ጸሎታችን መጠን

ከለመንነው ጸጋውን ከመስጠት አያቋርጥም። ቅዱሳን እንደሚያስተምሩን የእንድ ክርስቲያን ቅድስና የሚገኘው ቅዱስ ቁርባንን ከተቀበለ በኋላ ከሚያደርገው የሩብ ሰዓት ጸሎት ነው።

መሥዋዕተ-ቅዳሴ

ቅ. ቁርባን ምሥጢር ብቻ ሳይሆን የአዲስ ኪዳን እውነተኛና ነዋሪ መሥዋዕት ነው። በቀራንዮ መሥዋዕት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት በ ሙሉ ተሸሯል። አምልኮ ግን ያለ መሥዋዕት ስለማይታሰብ፣ ጌኢክ. አዲስና ነዋሪ መሥዋዕት ሠራልን። እሱም መሥዋዕተ-ቅዳሴ ነው።

ቅዳሴ ጌኢክ. በዕፀ-መስቀል ላይ የፈጸመውን መሥዋዕት በጎብኝትና በወይን መልክ በካህናት አገልግሎት አንደገና ማቅረብ ማለት ነው። ቅዳሴ ከቀራንዮ መሥዋዕት ይለያል፣ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ጌኢክ ደሙን አፍስሶና እውነተኛ ሞትን ሞቶ ጸጋ አስገኝልን። አሁን ግን ደሙን ሳያፈስ በምሥጢራዊ መንገድ እየተሠዋ በስቅላቱና በሞቱ ያስ ገኘልንን ጸጋ ይሰጠናል።

ቅዳሴ እውነተኛ መሥዋዕት መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እናውቃለን። ሚልክያስ.1፡ 11 «እነሆ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ዳር እስከ ዳር ለእኔ ክብ ር ይሰጣሉ በየትኛውም ስፍራ ለእኔ ዕጣን እያጠኑ ንጹሕ መሥዋዕት ያቀርቡልኛል» የሚለው ትንቢት ቅዳሴን ያመለክታል። (የትሬንቶ ጉባ ኤ)። ዕብራውያን 7፡ 27 «ኢየሱስ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ ይህን ነገር በማያዳግም ሁኔታ ፈጽሞታል» የሚለው፣ የቀራንዮ መሥዋ ዕት በኢየሱስ ሞት አንድ ጊዜና በአንድ ቦታ እንደ ተፈጸመ ይነግረናል። ቅዳሴ ግን ሁልጊዜና በሁሉ ቦታ ስለሚደገም የሚልክያስ ትንቢት በቅ ዳሴ ይፈጸማል።

ከክርስቶስ ቃላትም እንገነዘባለን፣ ምክንያቱም «ይህ ለእናንተ የሚ ሰጥ ሥጋዬ ነው» (ሉቃስ.22፡ 19፣ 1ቆሮ.11፡ 24)፣ «ይህ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው» (ማቴ.26፡ 28፣ ማር.14፡ 24) ያለው ቃል በመጨረሻው የእራት ጊዜ ያቀረበውን መሥዋ ዕት ያመለክታል። ይህም መሥዋዕት ከቅዳሴያችን የተለየ አይደለም።

ስለ መሥዋዕተ ቅዳሴ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ብቻ የሚገኘው ትምህርትና ምስክርነት እንኳን በጣም ብዙ ስለሆነ፣ እ.ኤ.አ. በ1545 ዓ.ም. በትሬንቶ ጉባኤ ላይ የተሰበሰቡት አቡኖች መርምረው፣ ቅዳሴ እውነተኛ መሥዋዕት መሆኑን የማያምን መናፍቅ

መሆኑን ገለጹ። እንዲሁም ጌ.ኢ.ክ. «ይህን ስታደርጉ ለመታሰቢያዬ አድርጉት» በማለቱ ሐዋርያቱን ካህናት እንደሾማቸውና ለእነሱና ለካህ ናት በሙሉ ቅዳሴ እንዲቀድሱ ሥልጣን እንደሰጣቸው አረጋገጡልን።

መሥዋዕት በሁለት ነገሮች ማለትም በመስጠትና በማረድ የቆመ ነው። በቅዳሴ የመጀመሪያው በትክክል ይፈጸማል፣ ምክንያቱም ጌ.ኢ.ክ፣ በካህናት አፍ አድርጎ ራሱን ይሰጣል፣ ሁለተኛው ግን በቅዳሴ ደም ስለ ማይፈስ በአምሳያ ይፈጸማል፣ ማለትም የኅብስትና የወይን መልክ ተለያይቶ ስለሚገኝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት ያመለክትልናል፤ በዚህ ምክንያት የጌ.ኢ.ክ መሥዋዕት ምሥጢራዊ ይባላል፣ ግን እውነተኛ መሥዋዕት ነው። ከቀራንዮ መሥዋዕት የሚለየው በአደራረጉ ብቻ ነው፣ ምክንያቱም ሠዊና ተሠዊ ዘወትር አንድ ክርስቶስ ነው (የትሬንቶ ጉባኤ)።

ቅዳሴን የሚሰተፉት ልክ በመስቀል ሥር ሆነው የቀራንዮን መሥ ዋዕት እንደሚሰተፉት ናቸው። ጌ.ኢ.ክ. በቀራንዮ እንዳደረገው ሁሉ፣ ቅዳሴን በአራት ምክንያቶች ማለትም፦

1) እግዚአብሔርን በሚገባ እንድናከብረው፣ 2) እንድናመሰግነው፣ 3) እንድንክሰውና ርኅራኄውን እንድናገኝ፣ 4) የሚያስፈልገንን ጸጋ ለመለመን ብለን እናቀርባለን።

በቅዳሴ ላይ በምንሰተፍበት ጊዜ የካህኑን ጸሎት መከታተል መልካም ነው፣ ብዙ ፍሬ ለማግኘት ግን ከጌ.ኢ.ክ ጋር ልብ ለልብ መገናኘት፣ ማለትም፣ እርሱ በመስቀል ላይ እያለ የተሰማውን መንፈሳዊ አሳብ መልበስ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቅዱስ ቅንዓት፣ የካሣ ፍላጐት፣ ምስጋና፣ ተአዝዞ፣ ተጋድሎ፣.... ወዘተ. ማዘውተር አለብን። የቅዳሴ ትልቁ ሱታፌ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ነው። የቅዳሴ ዋና ምሥጢር የኅብስትና የወይን መለወጥ ስለሆነ በዚያን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆይተው ከልባቸው የክርስቶስን መሥዋዕት የሚያቀርቡ በቅዳሴ ላይ ተሳታፊዎች ናቸው። ከተለወጠ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡ ግን ቅዳሴ አላስቀደሱም።

በየእሁዱ ቅዳሴ እንድንሳተፍ ትልቁ የቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ነው። ይህንን ትእዛዝ ለመፈጸም ሙሉ ቅዳሴ መስማት ተገቢ ነው። ስለዚህ ቅዳሴ ከሚጀመርበት ጊዜ ጀምረን የካህኑን ጸሎት መሳተፍ፣ የእግዚአብሔርን ቃልና ስብከት ሰምተን ማስተንተን፣ ካህኑ እስኪሸኘን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ቆይተን ጸሎት ማድረግ አለብን። ግማሽ ቅዳሴ

ውን ብቻ የሚሳተፉ የእግዚአብሔርን ፍላጐት አይፈጽሙም፣ በመልካም አርአያቸው ሕዝቡን ስለማያንጹ ጉብዝ ክርስቲያኖች አይደሉም። ቅዳሴ ከሁሉም ጸሎት፣ ከሁሉም ሥራ፣ ከሁሉም ተጋድሎ፣ ከሰማዕትነትም በላይ እግዚአብሔርን ያስከብራል፣ ምክንያቱም በቅዳሴ የእግዚአብሔርን ልጅ ሰማዕትነት ስለምናቀርብ ጥቅሙ ከመጠን በላይ ትልቅ ነው። «ካህን ሲቀድስ ከእርሱ ጋር ቅዳሴውን የሚሳተፍም ለእግዚአብሔር ክብርን ይሰጣል፣ መላእክትን ያስደስታል፣ ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል፣ ያሉትን ይረዳል፣ ሰሞቱትም ዕረፍትን ይሰጣል፣ ለራሱም የሁሉም መልካም ነገር ተሳታፊ ይሆናል» (ክርስቶስን ስለመምሰል 4ኛ መጽሐፍ 5፡ 3)።

4ኛ ምሥጢረ ንስሐ

ንስሐ ከጥምቀት በኋላ ያደረግነውን ኃጢአት እንዲደመስስልን ጌ.ኢ.ክ. የመሠረተው ምሥጢር ነው። ጌ.ኢ.ክ. ከሞት በተነሣበት ቀን ለ ሐዋርያቱ «እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸ ዋል። እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ይቅር አይባልላቸ ውም» (ዮሐ.20፡ 23) በማለት ለሐዋርያቱና ለሁሉም ካህናት ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ሰጣቸው። ይህ ሥልጣን በፍርድ መልክ እን ዲፈጸም ስለ ፈለገ ኃጢአታቸው ይቅር የሚባልላቸው ለሚናዘዙት ብቻ ነው። ምክንያቱም ካህን ኃጢአትን በኑዛዜ ሳያውቅ ሊፈታና ሊያ ሥር አይችልም፣ የኑዛ (የቀኖና) ሥራም ሊሰጥ አይችልም።

ሐዋርያት የጸፉት ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆንም፣ በስብከታቸው ለነፍሳት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ምሥጢረ-ንስሐንም ጭምር ገልጸ ዋል። ይሁን እንጂ እንደ ማንኛውም የጎበረተሰብ ጉዳዮች የምሥጢረ ንስሐ አፈጻጸም ሥርዓትም ቀስ በቀስ ወደ ሕዝበ ክርስቲያን ልማድ ገባ። በመጀመሪያ የንስሐ አደራረግ በስብሰባና በሕብረት ነበር፣ ቆይቶም በግላዊ ሁኔታ መፈጸም ተለመደ። አንዳንድ ምስክሮችም እነሆ፦

ዲዳኬ፡ (ኤ.ኤ.አ. በ95ዓ.ም. አካባቢ) «መሥዋዕታችሁ (ቅዳሴ) ን ጹሕ እንዲሆን፣ በጌታ ቀን (እሁድ) ኃጢአታችሁን ከተናዘ ዛችሁ በኋላ እንጀራ ቆርሳችሁ (ቆርባችሁ) አመስግኑ»።

በርናባስ፡ (ኤ.ኤ.አ. በ95ዓ.ም. አካባቢ) «ኃጢአታችሁን በማጎበር መካከል ተናዘዙ፣ በቆሻሻ ልብ ወደ ጸሎት (ቁርባን) አት ቅረቡ»።

ቆጵሪያኖስ፡ (ኤ.ኤ. በ258ዓ.ም. አካባቢ ሞተ) «አያንዳንዱ ጊዜ አያ ለው ኃጢአቱን ይናዘዝ፣ በካህን የሚያገኘው የኃጢአት ይቅርታ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አለው»

አሪጀንስ፡ (ኤ.ኤ. በ252 ዓ.ም. አካባቢ ሞተ) «ለእግዚአብሔር ካህ ን በመናዘዝ የኃጢአት ይቅርታ ይገኛል... ኃጢአታችሁን ለነፍስ አባታችሁ ተናዘዙ፣ ለማጎበር እንድትገልጹት ለ ነፍስ አባታችሁ መልካም ሆኖ ከታየው ፈጽሙት»።

በነዚህ ቃላትና በሌሎችም አበው ምስክርነት በዚያን ጊዜ ሁለት ዓይነት የኑዛዜ አደራረግ እንደ ነበረ እናውቃለን። ብቻህን ሆነህ ለነፍስ-አባት መናዘዝ የተለመደ ነበር፣ ይህ ብቻ ነበር ምሥጢረ- ንስሐ የነበረ ው። ለክርስቲያን ማጎበር የሚደረገው ኑዛዜ ግን የትሕትና ወይም የ ካሣ ሥራ ነው እንጂ እንደ ምሥጢረ-ንስሐ አልተቆጠረም። እንዲያውም በኛ ክፍለ-ዘመን ይህ ልማድ በጭራሽ ስለ ተከለከለ ለነፍስ አባት የሚደረገው ኑዛዜ ብቻ ቀረ።

ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ዓይነት ኃጢአት አንድም ሳይቀር ይቅር የማለት (የመፍታት) ሥልጣን እንደ ነበራት የታወቀ ነበር። በመጀመሪያ አካባቢ ግን ጠንካራ ስለ ነበረች ሦስት [redacted] አትፈታቸውም ነበር። ይህንን ማ ደረጓ ግን የኃጢአት ጥላቻ ልታሳድርባቸው ፈልጋ ነው እንጂ ኃጢአት የመፍታት ሥልጣን ስላልነበራት አይደለም። መናፍቃን፣ በተለይም ናቫሲያን ቤተ ክርስቲያን ይህን ሥልጣን የላትም ብለው ስላስተማሩ ኤ.ኤ. በ251 ዓ.ም. በሮማ በተደረገው ጉባኤ ተወገዙና በካህናት የሚ ደረገው ኑዛዜ የተለመደ ሆነ። ቅዱስ አንስጢኖስ ይሰብከው የነበረው፣ ማለትም «ለካህን መናዘዝ አለብን እንጂ አንድ ሰው እንኳ እኔ በእግዚ አብሔር ፊት መጸጸት ብቻ ይበቀኛል አይበል» የሚለው በዚያን ዘመን በመላዋ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያገኘ ትምህርት ነበር።



የተጸጸተው ልጅ (ሉቃ.15፡ 17) ምሥጢረ- ንስሐን ያስታውሰናል

በ13ኛው ክፍለ-ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለ ልጆቿ መንፈሳዊነት በማሰብ፣ ኑዛዜን የሚመለከት ትእዛዝ ጨመረች። ምክንያቱም ኤ.ኤ. በ1215 ዓ.ም. በ4ኛው የላቴራን ጉባኤ ላይ ለሙሉ አእምሮ የደረሱ ክር ስቲያን ሁሉ በዓመት አንድ ጊዜ ለነፍስ- አባታቸው መናዘዝ እንደሚገ ባቸው አወጀች። በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ ከሉተር በኋላ ፕሮቴስታንቶች ተነሥተው ምሥጢረ-ንስሐን ስለ አስወገዱ፣ ኤ.ኤ. በ1545 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያን በትሬንቶ ጉባኤ አድርጋ፣ እንደገና የሐዋርያትን ትምህ ርት መርምራና አረጋግጣ የሚከተለውን ትምህርት ገለጸች።


1. ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ከጌ.ኢ.ክ. ስለ ተቀበለች ማንኛውንም ኃጢአት በጣም ትልቅ ቢሆንም መፍታት ትችላለች። በዮሐንስ ወንጌል20፡ 23 የተነገረውን ቃል በሌላ አሳብ የሚተረጉም የተወገዘ ይሁን።

ቆጵሪያኖስ: (ኤ.ኤ.አ. በ258ዓ.ም. አካባቢ ሞተ) «እያንዳንዱ ጊዜ እያ ለው ኃጢአቱን ይናዘዝ፣ በካህን የሚያገኘው የኃጢአት ይቅርታ በእግዚአብሔር ተቀባይነት አለው»

ኦሪጀንስ: (ኤ.ኤ.አ. በ252 ዓ.ም. አካባቢ ሞተ) «ለእግዚአብሔር ካህ ን በመናዘዝ የኃጢአት ይቅርታ ይገኛል... ኃጢአታችሁን ለነፍስ አባታችሁ ተናዘዙ፣ ለማኅበር እንድትገልጹት ለ ነፍስ አባታችሁ መልካም ሆኖ ከታየው ፈጽሙት»::

በነዚህ ቃላትና በሌሎችም አበው ምስክርነት በዚያን ጊዜ ሁለት ዓይነት የኑዛዜ አደራረግ እንደ ነበረ እናውቃለን:: ብቻህን ሆነህ ለነፍስ-አባት መናዘዝ የተለመደ ነበር፣ ይህ ብቻ ነበር ምሥጢረ- ንስሐ የነበረ ው:: ለክርስቲያን ማኅበር የሚደረገው ኑዛዜ ግን የትሕትና ወይም የ ካሣ ሥራ ነው እንጂ እንደ ምሥጢረ-ንስሐ አልተቆጠረም:: እንዲያውም በ4ኛ ክፍለ-ዘመን ይህ ልማድ በጭራሽ ስለ ተከለከለ ለነፍስ አባት የሚደረገው ኑዛዜ ብቻ ቀረ::

ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ዓይነት ኃጢአት አንድም ሳይቀር ይቅር የማለት (የመፍታት) ሥልጣን እንደ ነበራት የታወቀ ነበር:: በመጀመሪያ አካባቢ ግን ጠንካራ ስለ ነበረች ሦስት ትላልቅ ኃጢአቶችን፣ ማለትም ክሕደት፣ ግድያና ዝሙትን በቀላሉ አትፈታቸውም ነበር:: ይህንን ማ ድረጓ ግን የኃጢአት ጥላቻ ልታሳድርባቸው ፈልጋ ነው እንጂ ከኃጢአት የመፍታት ሥልጣን ስላልነበራት አይደለም:: መናፍቃን፣ በተለይም ኖቫሲያን ቤተ ክርስቲያን ይህን ሥልጣን የላትም ብለው ስላስተማሩ እ.ኤ.አ. በ251 ዓ.ም. በሮማ በተደረገው ጉባኤ ተወገዙና በካህናት የሚ ደረገው ኑዛዜ የተለመደ ሆነ:: ቅዱስ አጎስጢኖስ ይሰብክው የነበረው፣ ማለትም «ለካህን መናዘዝ አለብን እንጂ አንድ ሰው እንኳ እኔ በእግዚ አብሔር ፊት መጸጸት ብቻ ይበቀኛል አይበል» የሚለው በዚያን ዘመን በመላዋ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያገኘ ትምህርት ነበር::



የተጸጸተው ልጅ (ሉቃ.15: 17) ምሥጢረ- ንስሐን ያስታውሰናል

በ13ኛው ክፍለ-ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለ ልጆቿ መንፈሳዊነት በማሰብ፣ ኑዛዜን የሚመለከት ትእዛዝ ጨመረች:: ምክንያቱም ኤ.ኤ.አ. በ1215 ዓ.ም. በ4ኛው የላቴራን ጉባኤ ላይ ለሙሉ አእምሮ የደረሱ ክር ስቲያን ሁሉ በዓመት አንድ ጊዜ ለነፍስ- አባታቸው መናዘዝ እንደሚገ ባቸው አወጀች:: በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ ከሉተር በኋላ ፕሮቴስታንቶች ተነሥተው ምሥጢረ-ንስሐን ስለ አስወገዱ፣ ኤ.ኤ.አ. በ1545 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያን በትሬንቶ ጉባኤ አድርጋ፣ እንደገና የሐዋርያትን ትምህ ርት መርምራና አረጋግጣ የሚከተለውን ትምህርት ገለጸች::

1. ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ከጌ.ኢ.ክ. ስለ ተቀበለች ማንኛውንም ኃጢአት በጣም ትልቅ ቢሆንም መፍታት ትችላላች:: በዮሐንስ ወንጌል20: 23 የተነገረውን ቃል በሌላ አሳብ የሚተረጉም የተወገዘ ይሁን::

2. በፍርድ ሥራ የሚሰጠው የካህን ፍትሐት እውነተኛ የኃጢአት ይቅርታ ነው እንጂ ተራ መግለጫ አይደለም።

3. በኑዛዜ ትልልቅ ኃጢአቶችን በሙሉ፣ በአሳብ የተደረገውንም፣ ቁጥሩንና ዓይነቱን ገልጠን መናገር የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ብቻ አይደለም።

4. ትልቅ ኃጢአት ያላቸው ሰዎች እንዲናዘዙ የእግዚአብሔር ፍላጐት ነው። በተለይም ከመቁረብ በፊት መናዘዝ አስፈላጊ ነው። (1ቆሮ.11፡ 28)። ትናንሽ ኃጢአት ያሳቸው ግን ቢናዘዙ መልካም ነው። ካልሆነም አይገደዱም።

ይህ ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንቶ ይገኛል፣ በጳጳሳትና በቅዱሳን ምክር ኑዛዜ እየተስፋፋ ሄዷል። ጳጳስ ፒዮስ 12ኛ እ.ኤ.አ. በ1945 ዓ.ም. «ዛሬ በሕዝበክርስቲያን የተለመደውና የሚዘወተረው ኑዛዜ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነውና እንደግፈው እንጂ አንንቀፈው» ብለው ሰበኩ። ጳውሎስ 6ኛ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም. ስለ ኑዛዜ በሰጡት አስተምሮ ላይ ይኸንኑ ምክር ደገሙልን።

መልካም ኑዛዜ ለማድረግ 5 ነገሮች ያስፈልጋሉ፣ ማለት ኃጢአታችን ን ማሰብ፣ በኃጢአታችን መጸጸት፣ ቁርጥ ፈቃድ ማድረግ፣ ኃጢአታችን ን ለነፍስ አባታችን መግለጽና እርሱ የሰጠንን ቀኖና (ካሣ) መፈጸም።

ከሁሉም በጣም የሚያሳስበን በኃጢአታችን መጸጸት ነው፣ ምክንያ ቱም ኃጢአታችንን ካልጠላን የእግዚአብሔር ምሕረት አይገባንም። ጸጸታችን መልዕልተ-ባሕርያዊ እንዲሆን ያስፈልጋል፣ ማለት ኃዘናችን በመንፈሳዊ ምክንያት እንጂ በሥጋዊ ምክንያት መሆን የለበትም። እንዲሁም ኃዘናችን አጠቃላይ መሆን አለበት፣ ማለትም ስለ ትልልቅ ኃጢአቶቻችን በሙሉ (አንድም ሳናስቀር) ማዘን አለብን። የበለጠው ሐዘን ግን ቅጣትን ፈርተህ የምታደርገው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍቅ ር ተነሣሥተህ የምታደርገው ፍጹም ሐዘን ነው። ይህ ፍጹም ሐዘን ያለውና የመናዘዝ ፍላጐት (ምኞት) ያለው ሰው፣ ገና ሳይናዘዝ ኃጢአቱ ይደመሰስለታል። ነገር ግን ከኑዛዜ መቅረት አይገባንም፣ ምክንያቱም ትልቅ ኃጢአትን በሙሉ ለካህን እንድንገልጽ የጌ.ኢ.ክ. ፍላጐት ነው።

እንግዲህ ይህንን የትሕትና ሥራ ወደን እንፈጽምና አዲስ ኃይል፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ሌላም ብዙ ጥቅም እናገኛለን። «ኑዛዜ ሰብአዊ ደኅንነታች ንን ለማደገፍ ጌ.ኢ.ክ. ያስገኘልን ከሁሉም የበለጠና ጠቃሚ መድኃኒት ነው» (ጳጳስ ቅዱስ ፒዮስ 10ኛ)።

የፍጹም ሐዘን ሥራ ምሳሌ እነሆ፡- «እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! በኃጢአቴ ምክንያት ለመከራና ለገሃነም እሳት የተገባሁ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን፣ በተለይም አንተን ቸር ፈጣሪዬንና አባቴን ስለ በደልኩህና ደጉ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒቴን ስለ ሰቀልሁት በፍጹም ልቤ አዝናለሁ፣ የሁሉ ኃጢአቶቼንም ይቅርታ አለምንሃለሁ።»

[redacted]

ሥሬተ-ኃጢአት፣ በንስሐ ቦታ ልንክሰው የሚገባንን ጊዜያዊ ቅጣት ይቅርታ የምናገኝበት ነው። ኃጢአት በኑዛዜ ከተደመሰሰልን በኋላ ካሣ መክፈል አለብን። ካሣውም ከኑዛዜ በኋላ የምንፈጽመው ቀኖና ነው። ግን አብዛኛውን ጊዜ ይህ ብቻ በቂ ስላልሆነ በሌላ መንገድ በዚህ ዓለም ወይም በንስሐ ቦታ መካስ አለብን። ቤተ ክርስቲያንም «መንፈሳዊ መዝገብ» ከሚባለው የኢየሱስ፣ የማርያምና የቅዱሳን ትሩፍት እየቀዳች ሥሬተ-ኃጢአትን ካደለችን የቀረው ዕዳችን ይቅር ይባልልናል። ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት ከሐዋርያት ስለተቀበለችና በጉባኤዎችም ስለ አረጋገጠች፣ ይህንን የማያምኑ ሰዎች ከሐቀኛው መንገድ ርቀው ይገኛሉ (የትሬንቶ ጉባኤ)።

[redacted]

ጐደሎ ሥሬተ-ኃጢአት ቤተ ክርስቲያን የሰጠችንን ጸሎት ወይም ቀስተ ጸሎት በቀን ብዙ ጊዜ በመድገም ሙሉ ሊሆን ይችላል። ሙሉ ሥሬተ-ኃጢአት ግን ቤተ ክርስቲያን የወሰነችልንን 4 ነገሮች በቀን አን ድ ጊዜ ከፈጸምን እናገኛለን። 4ቱ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ልዩ የመንፈሳዊነት ሥራ፣ እንደ ፍኖተ-መስቀል ወይም መቁ ጸሪያ ወይም ሌላ ጸሎት ለግማሽ ሰዓት በቅዱስ ቁርባን ፊት ሆኖ ማድረግ፣
ለ. በዕለቱ ወይም አስቀድሞ ኑዛዜ ማድረግ፣
ሐ. መቁረብ፣
መ. በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አሳብ የተወሰነ ጸሎት ማድረግ።

በጣም የታወቀው የሙሉ ሥሬተ-ኃጢአት መንገድ ደግሞ የኢዮቤል ዓመት ነው። ልዩ በሆነው የኢዮቤል ዓመት ወደ ተወሰነችልን ቤተ ክ ርስቲያን ሄደን ከላይ የጠቀስናቸውን 4 ነገሮች ከፈጸምን በየቀኑ ሙሉ ሥሬተ-ኃጢአት እናገኛለን። [redacted] ሳት ልንጠቀምበት እንችላለን።

2. በፍርድ ሥራ የሚሰጠው የካህን ፍትሐት እውነተኛ የኃጢአት ይቅርታ ነው እንጂ ተራ መግለጫ አይደለም።

3. በኑዛዜ ትልልቅ ኃጢአቶችን በሙሉ፣ በአሳብ የተደረገውንም፣ ቁጥሩንና ዓይነቱን ገልጠን መናገር የእግዚአብሔር ቅዱዝ ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ብቻ አይደለም።

4. ትልቅ ኃጢአት ያላቸው ሰዎች እንዲናዘዙ የእግዚአብሔር ፍላጐት ነው። በተለይም ከመቁረብ በፊት መናዘዝ አስፈላጊ ነው። (1ቆሮ.11፡ 28)። ትናንሽ ኃጢአት ያላቸው ግን ቢናዘዙ መልካም ነው። ካልሆነም አይገደዱም።

ይህ ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ ጸንቶ ይገኛል፣ በጳጳሳትና በቅዱሳን ምክር ኑዛዜ እየተስፋፋ ሄዷል። ጳጳስ ፒዮስ 12ኛ እ.ኤ.አ. በ1945 ዓ.ም. «ዛሬ በሕዝበ-ክርስቲያን የተለመደውና የሚዘወተረው ኑዛዜ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነውና እንደግፈው እንጂ አንንቀፈው» ብለው ሰበኩ። ጳውሎስ 6ኛ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም. ስለ ኑዛዜ በሰጡት አስተምሮ ላይ ይኽንኑ ምክር ደገሙልን።

መልካም ኑዛዜ ለማድረግ 5 ነገሮች ያስፈልጋሉ፣ ማለት ኃጢአታችን ን ማሰብ፣ በኃጢአታችን መጸጸት፣ ቁርጥ ፈቃድ ማድረግ፣ ኃጢአታችን ን ለነፍስ አባታችን መግለጽና እርሱ የሰጠንን ቀኖና (ካሣ) መፈጸም።

ከሁሉም በጣም የሚያሳስበን በኃጢአታችን መጸጸት ነው፣ ምክንያቱም ኃጢአታችንን ካልጠላን የእግዚአብሔር ምሕረት አይገባንም። ጸጸታችን መልዕልተ-ባሕርያዊ እንዲሆን ያስፈልጋል፣ ማለት ኃዘናችን በመንፈሳዊ ምክንያት እንጂ በሥጋዊ ምክንያት መሆን የለበትም። እንዲሁም ኃዘናችን አጠቃላይ መሆን አለበት፣ ማለትም ስለ ትልልቅ ኃጢአቶቻችን በሙሉ (አንድም ሳናስቀር) ማዘን አለብን። የበለጠው ሐዘን ግን ቅጣትን ፈርተህ የምታደርገው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍቅ ር ተነሣሥተህ የምታደርገው ፍጹም ሐዘን ነው። ይህ ፍጹም ሐዘን ያለውና የመናዘዝ ፍላጐት (ምኞት) ያለው ሰው፣ ገና ሳይናዘዝ ኃጢአቱ ይደመሰስለታል። ነገር ግን ከኑዛዜ መቅረት አይገባንም፣ ምክንያቱም ትልቅ ኃጢአትን በሙሉ ለካህን እንድንገልጽ የጌ.ኢ.ክ. ፍላጐት ነው።

እንግዲህ ይህንን የትሕትና ሥራ ወደን እንፈጽምና አዲስ ኃይል፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ሌላም ብዙ ጥቅም እናገኛለን። «ኑዛዜ ሰብአዊ ደካማነታች ንን ለማደገፍ ጌ.ኢ.ክ. ያስገኘልን ከሁሉም የበለጠና ጠቃሚ መድኃኒት ነው» (ጳጳስ ቅዱስ ፒዮስ 10ኛ)።

የፍጹም ሐዘን ሥራ ምሳሌ እነሆ፡- «እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! በኃጢአቴ ምክንያት ለመከራና ለገሃነም እሳት የተገባሁ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን፣ በተለይም አንተን ቸር ፈጣሪዬንና አባቴን ስለ በደልኩህና ደጉ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒቴን ስለ ሰቀልሁት በፍጹም ልቤ አዝናለሁ፣ የሁሉ ኃጢአቶቼንም ይቅርታ እለምንሃለሁ።»

ሥርዓተ-ኃጢአት

ሥርዓተ-ኃጢአት፣ በንስሐ ቦታ ልንክሰው የሚገባንን ጊዜያዊ ቅጣት ይቅርታ የምናገኝበት ነው። ኃጢአት በኑዛዜ ከተደመሰሰልን በኋላ ካሣ መክፈል አለብን። ካሣውም ከኑዛዜ በኋላ የምንፈጽመው ቀኖና ነው። ግን አብዛኛውን ጊዜ ይህ ብቻ በቂ ስላልሆነ በሌላ መንገድ በዚህ ዓለም ወይም በንስሐ ቦታ መካስ አለብን። ቤተ ክርስቲያንም «መንፈሳዊ መዝገብ» ከሚባለው የኢየሱስ፣ የማርያምና የቅዱሳን ትሩፍት እየቀዳች ሥርዓተ-ኃጢአትን ካደለችን የቀረው ዕዳችን ይቅር ይባልልናል። ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት ከሐዋርያት ስለተቀበለችና በጉባኤዎችም ስለ አረጋገጠች፣ ይህንን የማያምኑ ሰዎች ከሐቀኛው መንገድ ርቀው ይገኛሉ (የትሬንቶ ጉባኤ)።

ሥርዓተ-ኃጢአት ሁለት ዓይነት ነው፣ ማለትም ጐደሎና ሙሉ። ጐደሎ ሥርዓተ-ኃጢአት ቤተ ክርስቲያን የሰጠችንን ጸሎት ወይም ቀስተ ጸሎት በቀን ብዙ ጊዜ በመድገም ሙሉ ሊሆን ይችላል። ሙሉ ሥርዓተ-ኃጢአት ግን ቤተ ክርስቲያን የወሰነችልንን 4 ነገሮች በቀን አን ድ ጊዜ ከፈጸምን እናገኛለን። 4ቱ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ልዩ የመንፈሳዊነት ሥራ፣ እንደ ፍኖተ-መስቀል ወይም መቁ ጸሪያ ወይም ሌላ ጸሎት ለግማሽ ሰዓት በቅዱስ ቁርባን ፊት ሆኖ ማድረግ፤

ለ. በዕለቱ ወይም አስቀድሞ ኑዛዜ ማድረግ፤

ሐ. መቁረብ፤

መ. በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አሳብ የተወሰነ ጸሎት ማድረግ።

በጣም የታወቀው የሙሉ ሥርዓተ-ኃጢአት መንገድ ደግሞ የኢዮቤል ዓመት ነው። ልዩ በሆነው የኢዮቤል ዓመት ወደ ተወሰነችልን ቤተ ክ ርስቲያን ሄደን ከላይ የጠቀስናቸውን 4 ነገሮች ከፈጸምን በየቀኑ ሙሉ ሥርዓተ-ኃጢአት እናገኛለን። ይህንን ዕድል ለራሳችንና ለንስሐ ቦታ ነፍ ሳት ልንጠቀምበት እንችላለን።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ምሕረትንና የአናታችን የቤተ ክርስቲያንን ልግስና አመስግነን በእምነት እንጠቀምበት።

5ኛ መጽሐፈ-ቀንዲል (ለበሽተኞች የሚደረግ ቅባት)

መጽሐፈቀንዲል በጠና ሕመም ወይም በእርጅና ለሞት የቀረቡትን የሚያጽናና ምሥጢር ነው። ምንም እንኳ በያዕቆብ ቢገለጽም (ያዕ.5፡ 14-15) በጌ.ኢ.ክ. እንደ ተመሠረተ እርግጥ ነው (የትሬንቶ ጉባኤ)። ይህ ምሥጢር ልዩ ጸጋን ይሰጣል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን፣ ማለትም እምነት፣ እርጋታ፣ ኃይል፣ ጽናት፣ የመሳሰሉትን ያድላል። የቀረ ኃጢአትንም ይደመስሳል። ለነፍስ የሚጠቅም ከሆነ ደግሞ ለሥጋ ጤንነትን ስለሚሰጥ ለታመሙት ሰዎች በጣም ጠቃሚ ነው።

ይህንን ምሥጢር ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው ካህናት ብቻ ናቸው (የትሬንቶ ጉባኤ)። ቅዱስ ያዕቆብ ሽማግሌዎች ሲል ሳለ ካህናት ማለቱ ነው እንጂ ማንም ተራ ሰው አለማለቱን ያረጋግጣል። ካህን ቤተ ክርስቲያን የወሰነችውን ጸሎት እደየገመ በቅዱስ ዘይት የበሽተኛውን ግምባርና እጆች ይቀባቸዋል። በመጨረሻም በሽተኛውንና እዚያ የሚገኙትን ምእመናን ሁሉ ይባርካል።

6ኛ ምሥጢረ-ክህነት

ምሥጢረ-ክህነት ሰውን የተቀባ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚያደርግ፣ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት ለማደል ሥልጣን የሚሰጥና፣ የማይጠፋ ማኅተምን የሚያትምበት ምሥጢር ነው። ምሥጢረ ክህነት የጵጵስናንና የዲቁና ማዕረጎችንም ያጠቃልላል።

ጌ.ኢክ. ምሥጢረ-ቁርባንን ከሠራ በኋላ «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» (ሉቃ.22፡ 19) በማለት ለሐዋርያቱና ለተከታዮቻቸው ቅዱስ ቁርባንን የመሥራት ሥልጣን ሰጣቸው። በትንሣኤው ቀን ደግሞ (ዮሐ.20፡ 22) ኃጢአትን የሚፈቱበትና የሚያስሩበት ሥልጣን ሰጣቸውና የአዲስ ኪዳን ካህናት አደረጋቸው። ሐዋርያትን የመረጣቸውና የሾማቸው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ.15፡ 16)። እነሱም ይህን ሥልጣን ለባልደረቦቻቸውና ለወራሾቻቸው እንዲያስተላልፉ ፈለገ። ይህንን ለማድረግ ያስተማራቸው ሥርዓት ደግሞ ጸሎትና አንብሮ-እድ (እጅን መጫን) ነበር። ይህ ሥርዓት በሐዋርያት ዘመን የተለመደ ነበር። ለምሳሌ፡- በዚህ ሥርዓት የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት ተሾሙ (የሐዋ. ሥራ፡ 6፡ 7)፣ ጳውሎስና በርናባስ በዚህ ዓይነት ሥርዓት ተልእኳቸውን ተቀበሉ (የሐዋ. ሥራ.13፡ 2)፣ ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ ዓይነት ሥርዓት ለጢሞቴዎስ ማዕረገ ክህነትን ስለ አካፈለው (2ጢሞ.1፡ 6)፣ ጢሞቴዎስም በዚሁ ሥርዓት ማዕረገ ክህነትን ለሌሎች ሊያካፍል ይችል ነበር (1ጢሞ.5፡ 22)።

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደ ሥራቸው መጠን ልዩ ማዕረግ ስለሚቀበሉ፣ ማዕረጋቸው 3 ደረጃ አለው፣ ማለትም ጵጵስና፣ ክህነትና ዲቁና ነው። ይህ የተለያየ ደረጃ ከመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ጀምሮ የተለመደ መሆኑን ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት እናውቃለን። ለምሳሌ፡- እ.ኤ.አ. በ107 ዓ.ም. የሞተው የቅዱስ ኢግናጵዮስ ደብዳቤዎች ይመሰክሩ ልናል።

እንግዲህ ጌ.ኢ.ክ. ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስተዳድሯት፣ ከሕዝበ-ክርስቲያን መካከል ተመርጠው፣ ልዩ ማዕረግ ተቀብለው ካህናት እንዲሆኑ ፈለገ። እነሱ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት በትውልድ የሚተላለፍ ሳይሆን በልዩ የእግዚአብሔር ጥሪ በቤተክርስቲያን ይሾማሉ፣ ይቀባሉም። ይህንን ሹመትና ቅባት ሊሰጡ የሚችሉ ደግሞ አቡናት ብቻ ናቸው። እነሱም ይህን ሥልጣን የተቀበሉት ከሐዋርያት ነው። ምክንያቱም ባለፉት ዘመናት የሐዋርያት ተከታዮች ለወርሾቻቸው ያስተላለፉላቸው ሥልጣን ዛሬ እስካሉት አቡናት ድረስ ደርሷል።



አቡን ማዕረገ-ክህነት ሲሰጡ

ፕሮቴስታንቶች ግን በሉተር ተመርተው የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት፡፡ ስለካዱና ማዕረገ-ክህነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኝ ሊረዱ ስላልቻሉ ክህነትን አስወገዱ፡፡ ይህንን በማድረጋቸው የበለጠውን የክርስትና ሃብት አጠፉ (ክሰሩ)፣ ምክንያቱም ከምሥጢረ-ጥምቀት በስ ተቀር ሌላ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የላቸውም፡፡ ካህናት ስለሌላቸው ሊቀድሱና ሊቆርቡ አይችሉምና ትልቅ ኪሳራ ደርሶባቸዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በትሬንቶ ጉባኤ መጽሐፍ ቅዱስንና ትውፊትን መርምራ ስለ ምሥጢረ-ክህነት የሚከተለውን ትምህርት ገለጸች፡፡


ሀ. «በአዲስ ኪዳን እውነተኛ ክህነት አለ፣ ክህነቱን የሚቀበሉት ጎብስትንና ወይንን የመለወጥና መስዋዕት የማቅረብ፣ እንዲሁም ኃጢአትን የማሠርና የመፍታት ሥልጣን አላቸው እንጂ ሥራቸው ተራ የስብከት ተልእኮ ብቻ አይደለም፡፡ ይህንን የ ማያምን የተወገዘ ይሁን»፡፡

ለ. «በቤተ ክርስቲያን ያለው ክህነት በእውነት በጌ.ኢ.ክ. የተመሠረተ ምሥጢር ነው፣ በሰው የተፈጠረ ተራ ሥርዓት ነው የሚል ካለ የተወገዘ ይሁን»፡፡

ሐ. «አቡናት ማዕረጋቸውን ለማካፈል ብለው «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» በሚሉበት ጊዜ በእውነት መንፈስ ቅዱስን ይሰጣሉ፣ ለተቀባዮቹም የማይደመሰስ ማኅተም ስለሚያትሙላቸው ለሁልጊዜ የተቀቡ ናቸው»፡፡

ጳጳሳትም፣ በተለይም ፒዮስ 12ኛ ስለ ክህነት ማዕረግና ሥልጣን በሰፊው አስተምረዋል፡፡ ስለዚህ የማትሳሳት ቤተ ክርስቲያን ስለ ክህነት ከአረጋገጠችልን፣ እኛም እንጠቀምበት፣ አምላክንም እናመስግነው፣ በ ተለይም በቅዳሴ አድርገን ለእግዚአብሔር ወሰን የሌለው አክብሮት እናቅርብለት፡፡

በሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ካህናት የሚሆኑት በድንግልና መኖር አለባቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ግን ማንንም ሰው በድንግልና እንድኖር አታስገድድም፡፡ ነገር ግን በራሳቸው ፈቃድ በድንግልና ለመኖር መሐላ ያደረጉትን ተማሪዎች ክህነት ታሰብሳቸዋለች (ትቀባቸዋለች)፡፡ ድንግልናውን የማይጠብቅ ሰው ወደ ክህነት ደረጃ ለመድረስ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ለመፈጸም ነፃ አይደለም፡፡



አቡናት ማዕረገ-ጵጵስናን ሲሰጡ

7ኛ ምሥጢረ-መጽሐፈ ተክሊል (ቃል-ኪዳን)

መጽሐፈ-ተክሊል፣ ባልና ሚስት በቤተ ክርስቲያን ቡራኬ ጀምረው ለሙሉ የሕይወት ዘመናቸው በመልካም ሁኔታ በፍቅርና በስምምነት አብሮ የሚኖሩበትንና ልጆቻቸውን በመልካም ሁኔታ የሚያሳድጉበትን ጸጋ የሚሰጥ፣ በጌ.ኢ.ክ. የተመሠረተ ምሥጢር ነው። «ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል፣ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ» (ኦሪ. ዘፍ.2፡ 24) የሚለው ቃል፣ ይህ ኪዳን እንደ ተፈጥሮአዊ ውል በባነት ውስጥ እንደ ተመሠረተ ያመለክታል። ጌ.ኢ.ክ. ይህንን ኪዳን ቀድሶ ወደ ምሥጢር ለወጠው፣ ይህንን መቼ እንዳደረገ ግን አናውቅም (ምና ልባት በቃና ዘገሊላ ይሆናል)። የሆነ ሆኖ፣ ቃል-ኪዳን የተመሠረተው በእርግጥ በጌ.ኢ.ክ. ነው። የትሬንቶ ጉባኤ እንደ አወጀው፣ ቃል-ኪዳን በሰው ሳይሆን በጌ.ኢ.ክ. እንደ ተመሠረተና ከ7ቱ ምሥጢራት አንዱ መሆኑን ማመን አለብን።

ቅዱስ ጳውሎስም «ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፣ ይህንንም የምለው ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርጌ ነው» (ኤፌሶን.5፡ 32) በማለት የሙሽራውና የሙሽሪቷ ኅብረት የክርስቶስንና ሙሽሪቱ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ስለሚመስል ቅዱስ ምሥጢር መሆኑን ያስረዳናል።

ክርስቲያናዊ ቃል-ኪዳን እንደሚከተለው መሆን አለበት፡-

ሀ. ቃል-ኪዳን አንድ ነው፣ ማለት አንድ ወንድ አንድ ሴት ብቻ ማግባት ይችላል። ይህ ሕግ ከመጀመሪያ ጀምሮ የነበረ ነው፣ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ከሚስቱም ጋር ይተባበራል» ይላል እንጂ «ከሴቶች ጋር ይተባበራል» የሚል አናገኝም (ጳጳስ ኢኖቸንዚዮስ 3ኛ)። በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ወንድ ብዙ ሴቶችን ማግባት የተለመደ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን በትዕግሥት ይጠብቃቸው ነበር (ሮሜ.3፡ 25)፣ ጌ.ኢ.ክ. ግን የእግዚአብሔርን ሕጎች ወደ መጀመሪያው መሠረት መለሳ ቸው።

ለ. ቃል-ኪዳን አይፈታም። ጌ.ኢ.ክ «እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው» (ማር.10፡ 9) በማለት መፋታትን በጭራሽ ከለከለ። «በዝሙት ምክንያት ከልሆነ በቀር ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ምክንያት ይሆንባታል። የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል» (ማቴ.5፡ 32፣ 19፡ 6) የ ሚለው ቃል ያጠራጥረን ይሆናል፣ ማለት ጌ.ኢ.ክ. በዝሙት



በቤተ ክርስቲያን ቡራኬ ቃል-ኪዳን የሚያስሩ ሙሽሮች

ምክንያት ቃል-ኪዳን እንዲፈታ የፈቀደ ይመስላል፣ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ግን በሐዋርያት ትውፊት ታግዛ፣ ባለት ስጦታ ተጠቅማ (ስለ ሃይማኖትና ስለ ሞራል ስታስተምር አትሳሳትም ና) ይህንን የወንጌል ቃል እንዲህ ብላ ተረጉመችልን፡- «ለዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር፣ ማለት ያለ ቃል-ኪዳን ያገባ ካልሆነ በቀር አንድም ሰው ሚስቱን ሊፈታ አይችልም ማለቱ ነውና ዝሙት የቃል-ኪዳንን ማሠሪያ እንደማይፈታ የተረጋገጠ ነው» የትሬንቶ ጉባኤ ደግሞ «ቤተ ክርስቲያን የቃል-ኪዳን ማሠሪያ በዝሙት አይፈታም ብላ በማስተማርዋ ትሳሳታለች የሚል የ ተወገዘ ይሁን» ብሎ አወጀ። አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች ግን የቤተ ክርስቲያን መሪነት ስለሚጐድላቸው ይህንን የወንጌል ቃል አይረዱትምና ከትዳር ጓደኞች ከሁለት አንዱ ዝሙት ከፈጸመ አንደኛው ሊፈታውና ሊሸኘው ይችላል ይላሉ። ይህ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጐት ተቃራኒ ነው።

ቅዳውሎስም እንዲህ ይለናል፡- «ሚስት ባልዋ በሕይወት እስካለ ድረስ በጋብቻ ሕግ የታሰረች ናት» (1ቆሮ.7፡ 39)። ስለዚህ በእውነተኛ ፍላጐት የታሠረ ቃል-ኪዳን በምንም ምክንያት፣ በችግር፣ ባለ መስማማት፣ በበሽታ፣ በመናፍቅነት፣ በዝሙት፣... ወ.ዘ.ተ. ሊፈታ አይችልም። በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን የፈታ ሌላ ሊያገባ አይችልም። (ማቴ.5፡ 32፣ 1ቆሮ.7፡ 10)። በድንገት ወይም በስምምነት የተለያዩ ባለትዳሮች፣ ለየብቻቸው እንዲኖሩ እንጂ ሌላ እንዲያገቡ አይፈቀድላቸውም። ቅዳውሎስ ገና ክርስቲያን ሳይሆኑ ቃል-ኪዳን አሥረው ወደ ክርስትና ለሚገቡት ብቻ አንድ የመፋታት ምክንያት አገኘላቸው፣ ማለትም ከትዳር ጓደኛሞቹ አንዱ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ሊገባ ከፈለገና አንዱ ወገን የተቃወመው እንደሆነ ሊፈታው ይችላል። በሰላም ከተቀበለው ግን እነሱም ቢሆኑ ሊፋቱ አይችሉም (1ቆሮ.7፡ 12-15)።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ቃል-ኪዳንን የመፍታት ሥልጣን የላትም። እውነተኛ ቃል-ኪዳን ከተፈጸመ በኋላ ሁለቱም «አንድ ሥጋ ስለሚሆኑ» ቤተ ክርስቲያን ልትፈታው ሥልጣን የላትም። ያልተፈጸመውን ቃል-ኪዳን ግን (ሁለቱ በግብረ-ሥጋ ሳይገናኙ) በበቂ ምክንያት ልትፈታው ትችላለች፣ ማለትም ሁለቱ ቃል-ኪዳን ከአሠሩ በኋላ በግብረ ሥጋ ከመገናኘታቸው በፊት ለመለያየት ከለመኑ የቤተ ክርስቲያንን ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። ይአንዳንድ ችግር ምክንያት ማሠሪያ የሌላቸው የሚመስላቸው ባለትዳሮች ቤተ ክርስቲያን ጉዳያቸውን ትመረምርና ማሠሪያ እንደሌላቸው የሚያስረዳ ምክንያት ከተገኘ ሊለያዩ እንደሚችሉ መግለጫ ታወጣለች እንጂ ፈቃድ አትሰጥም።

ሐ. ቃል-ኪዳን የሚመራው በቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው። መጽሐፈ-ተክሊል ከሰባቱ ምሥጢራት አንዱ ስለ ሆነና ቤተ ክርስቲያን የ ባለትዳሮች ኃላፊነት ስለ አለባት የቃል-ኪዳኑን ሁኔታ የምትወስነው ቤተ ክርስቲያን ናት። የቃል-ኪዳን ዕንቅፋት የሚሆኑትን ምክንያ ቶች የማቅረብና ብያኔ የመስጠት ሥልጣን አላት። «በምድር የም ታስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል» (ማቴ.18፡ 18) የሚለውን እና ስታውስ። ስለዚህ ቃል-ኪዳን የሚያስሩ ለዎች ሕጎቹን መጠበቅ አለባቸው።

የቃል-ኪዳን ሥርዓት የሚፈጸመው በጉባኤዎች በተወሰነው መ ሠረት ነው፣ ማለት ሙሽሮቹ ተዘጋጅተውና ከማንኛውም ዕንቅፋት ነፃ ሆነው በቆሞስና በሁለት ምስክሮች ፊት ቆመው ፍላጐታቸውን

ይገልጻሉ። ያለ ካህንና ያለ ምስክሮች ከተጋቡ ግን ኃጢአት ይሆን ባቸዋል እንጂ እንደ ቃል-ኪዳን አይቆጠርላቸውም። በቆሞስና በ ምስክሮች ፊት ሁለቱም «እሺ» ካሉ በኋላ ይህ ምሥጢር ይፈ ጸማል። ይህንን የሚያረጋግጡት እጅ ለእጅ በመያያዝና ቀለበቶችን በመለዋወጥ ነው። ምንም እንኳ ቃል-ኪዳን የሚያደርጉት ራሳቸው ሁለቱ ሙሽሮች ቢሆኑም ቆሞስ የቤተ ክርስቲያን ተወካይ ሆኖ እንዲሳተፍ አስፈላጊ ነው። ያለ ካህን የሚታሰር ቃል-ኪዳን ብቁ ስላልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድም ተቀባይነት የለውም። በሞት አደጋ ጊዜ ግን በምስክሮች ፊት ብቻ እንዲታሰር ይፈቀዳል።

ቃል-ኪዳን የሚያስሩት በሙሉ ሕይወታቸው ለቤተ ክርስቲያን ሊታዘዙ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትቃወመውን ጽንሰ የሚከለክል ነገ ር እንዳይጠቀሙ (ጳጳስ ጳውሎስ ፩ኛ)፣ ልጆቻቸውን በመልካም ሁኔታ እንዲያሳድጉ፣ እርስበርሳቸው መፋቀርና በስምምነታቸውና በመንፈሳዊነታቸው ለሌሎች አርአያ መሆን ይገባቸዋል። እያንዳንዱ ቤተሰብ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ነው (2ኛ የቫቲካን ጉባኤ)፣ ስለዚህ እግዚአብሔር በመካከላቸው አለ (ማቴ.18፡ 20)፣ የናዝሬቷ ቅድስት ቤተሰብ አርአያ ትሁንላቸው።

ምዕራፍ 20


የሰው ፍጻሜዎች

«በምታደርገው ሥራ ሁሉ ፍጻሜህን አስብ፣ ለዘለዓለሙም አትበድልምና» (ሲራክ.7፡ 36) የሚለውን አስታውሰን፣ ከዚህ ቀጥሎን የሰው ፈጻሜዎችን፣ ማለትም ስለ ሞት፣ ስለ ፍርድ፣ ስለ መንግሥተ-ሰማይ ና ስለ ገሃነመ-እሳት፣ እንዲሁም በዓለም መጨረሻ ጊዜ የሚከናወኑትን ሁኔታዎች እንመለከታለን።

ሞት

ሞት የነፍስና የሥጋ መለያየት ነው። ከሞት የሚያመልጥ አንድም ሰው የለም፣ «በኃጢአት ምክንያት ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ» (ሮሜ.5፡ 12)፣ ስለዚህ ሄኖክና ኤልያስም ከዚህ ዓለም ሲለዩ እኛ በማናውቀው መንገድ ሞተው እንደሚሆኑ ግዴታ ነው።

ሞት የዘለዓለማዊ ሕይወት በር መክፈቻ ስለሆነ ሊያስፈራን አይገባም። ሳንሞት እግዚአብሔርን ልናገኘው አንችልም። ምክንያቱም «እንደ መኖሪያችን በሆነው ሥጋችን እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን መኖራችንን አናውቃለን» (2ቆሮ.5፡ 6)። ከሞት ይልቅ ፍርድ ያስፈራናል፣ ምክንያቱም ደሞዛችንን ወይም ቅጣታችንን የምናገኘው በፍርድ ነው። ስለዚህ ሁል ጊዜ በንጽሕና፣ በእምነትና በመልካም ተግባር ተዘጋጅተን እንቆይ። ምክንያቱም «የሰው ልጅ ባላሰባችሁበት ሰዓት በድንገት ይመጣል፣ ስለዚህ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ» ተብለናል (ሉቃ.12፡ 40)።



የጻድቃንና የኃጥአን ሞት

ግላዊ ፍርድ

ፍርድ የሚፈጸመው ከሞት በኋላ ነው፣ ማለት ሰው ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ነፍሱ መልካም ዋጋዋን ወይም ቅጣትዋን ትቀበላለች። ይህ የመጀመሪያ ፍርድ ወይም ግላዊ ፍርድ ይባላል። «ለሰው አንድ ጊዜ መሞት የተገባ ነው፣ ከሞት በኋላም ፍርድ ይጠብቃዋል» (ዕብራ.9፡

27)፣ «እያንዳንዱ ሰው በሥጋው ላደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደየሥራው ብድራቱን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን» (2ቆሮ.5፡ 10)። «ከሥጋችን ተለይተን ከጌታ ጋር ለመኖር እንመኛለን» (2ቆሮ.5፡ 8) በማለት ቅዱሱስ ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወዲያውኑ በሰማይ ከአምላክ ጋር መኖር እንዳለባት ያስብ ነበር።

ጌ.ኢ.ክ. ምንም እንኳ ስለ የጋራ ፍርድ ብዙ ጊዜ ቢናገርም፣ ስለ ግላዊ ፍርድም ሳይገልጽ አላለፈም። ይህንንም ከቃላቱና ከምሳሌዎቹ እንረዳለን። ለምሳሌ፡- ሃብታሙ ሰውየና አልአዛር (ሉቃ.16፡ 24) ከሞቱ በኋላ ወዲያውኑ ፍርዳቸውን ተቀብለዋል። እንዲሁም ያ ክፉና ጨካኝ አገልጋይ (ማቴ.24፡ 50)፣ በኢየሱስ ቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴም ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ዘላለማዊ ዋጋውን አገኘ (ሉቃ.23፡ 43)። ይህ ትምህርት በሐዋርያት ትውፊት ውስጥም ይገኛል፣ ምክንያቱም በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት አበውና ሰማዕታት ሲሞቱ ቀጥ ብለው ወደ ሰማይ እንደሚሄዱ አይጠራጠሩም ነበር።

የጋራ ፍርድ የሚፈጸመው በዓለም መጨረሻ ነው፣ ዘላለማዊው ዕጣችን ግን (ሽልማት ወይም ቅጣት) ድሮ በመጀመሪያው ግላዊ ፍርድ ይወሰንልናል። ብዙ የፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች እንዲሁም ግሪካው ያን ግላዊ ፍርድን አያምኑም። እንደነሱ አስተያየት፣ ነፍሳት እስከ ሙታን ትንሣኤ ድረስ በሲኦል ወይም በሌላ ቦታ ሆነው ያለ ፍርድ ይጠባበቃሉ። እኛ ግን ይህን አስተሳሰባቸውን ልንቀበል አንችልም፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ስለዚህ ጉዳይ የምታስተምረው ትምህርት የተረጋገጠ ነው።


2ኛ የልዮን ጉባኤ እ.ኤ.አ. በ1274 ዓ.ም.፣ የፊረንጻ ጉባኤ እ.ኤ.አ. በ1439 ዓ.ም. እንዲሁም ጳጳስ በነዲክቶስ 12ኛ እ.ኤ.አ. 1336 ዓ.ም. እንደገለጹት፣ ሰው ሁሉ ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ሽልማቱን ወይም ቅጣቱን ይቀበላል። ይኸውም እንደሚከተለው ነው።

ሀ. በጣም ንጹሕ የሆነ ሰው ከሞተ በኋላ፣ ምንም እንኳ ያለ ሥጋ ው ቢሆንም ወዲያውኑ መንግሥተ-ሰማይ ገብቶ በነፍሱ ዘለዓለማዊ ብፅዕነትን ያገኛል።

ለ. [redacted]ው ወይም ደግሞ የኃጢአት ካሣ (ቀኖና) ያልፈጸመ ከሞተ በኋላ ነፍሱ [redacted]፡ ካሣ ዋን ከፈጸመች በኋላ ወደ ሰማይ ታልፋለች።

ሐ. ትልቅ ኃጢአት ሠርቶ እስከ መጨረሻው ሳይጸጸት የሞተ ሰው ለዘለዓለም ይኮነናል።

ሞት የዘለዓለማዊ ሕይወት በር መክፈቻ ስለሆነ ሊያስፈራን አይገባም። ሳንሞት እግዚአብሔርን ልናገኘው አንችልም። ምክንያቱም «እንደ መኖሪያችን በሆነው ሥጋችን እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን መኖራችንን አናውቃለን» (2ቆሮ.5፡ 6)። ከሞት ይልቅ ፍርድ ያስፈራናል፣ ምክንያቱም ደሞዛችንን ወይም ቅጣታችንን የምናገኘው በፍርድ ነው። ስለዚህ ሁል ጊዜ በንጽሕና፣ በእምነትና በመልካም ተግባር ተዘጋጅተን እንቆይ። ምክንያቱም «የሰው ልጅ ባላሰባችሁበት ሰዓት በድንገት ይመጣል፣ ስለዚህ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ» ተብለናል (ሉቃ.12፡ 40)።



የጻድቃንና የኃጥአን ሞት

ግላዊ ፍርድ

ፍርድ የሚፈጸመው ከሞት በኋላ ነው፣ ማለት ሰው ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ነፍሱ መልካም ዋጋዋን ወይም ቅጣትዋን ትቀበላለች። ይህ የመጀመሪያ ፍርድ ወይም ግላዊ ፍርድ ይባላል። «ለሰው አንድ ጊዜ መሞት የተገባ ነው፣ ከሞት በኋላም ፍርድ ይጠብቃዋል» (ዕብራ.9፡

27)፣ «እያንዳንዱ ሰው በሥጋው ላደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደየ ሥራው ብድራቱን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን» (2ቆሮ.5፡ 10)። «ከሥጋችን ተለይተን ከጌታ ጋር ለመኖር እንመኛለን» (2ቆሮ.5፡ 8) በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወዲያውኑ በሰማይ ከአምላክ ጋር መኖር እንዳለባት ያስብ ነበር።

ጌ.ኢ.ክ. ምንም እንኳ ስለ የጋራ ፍርድ ብዙ ጊዜ ቢናገርም፣ ስለ ግላዊ ፍርድም ሳይገልጽ አላለፈም። ይህንንም ከቃላቱና ከምሳሌዎቹ እንረዳለን። ለምሳሌ፡- ሃብታሙ ሰውየና አልአዛር (ሉቃ.16፡ 24) ከሞቱ በኋላ ወዲያውኑ ፍርዳቸውን ተቀብለዋል። እንዲሁም ያ ክፉና ጨካኝ አገልጋይ (ማቴ.24፡ 50)፣ በኢየሱስ ቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴም ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ዘላለማዊ ዋጋውን አገኘ (ሉቃ.23፡ 43)። ይህ ትምህርት በሐዋርያት ትውፊት ውስጥም ይገኛል፣ ምክንያቱም በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት አበውና ሰማዕታት ሲሞቱ ቀጥ ብለው ወደ ሰማይ እንደሚሄዱ አይጠራጠሩም ነበር።

የጋራ ፍርድ የሚፈጸመው በዓለም መጨረሻ ነው፣ ዘላለማዊው ዕጣችን ግን (ሽልማት ወይም ቅጣት) ድሮ በመጀመሪያው ግላዊ ፍርድ ይወሰንልናል። ብዙ የፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች እንዲሁም ግሪካው ያን ግላዊ ፍርድን አያምኑም። እንደነሱ አስተያየት፣ ነፍሳት እስከ ሙታን ትንሣኤ ድረስ በሲኦል ወይም በሌላ ቦታ ሆነው ያለ ፍርድ ይጠባበቃሉ። እኛ ግን ይህን አስተሳሰባቸውን ልንቀበል አንችልም፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ስለዚህ ጉዳይ የምታስተምረው ትምህርት የተረጋገጠ ነው።

2ኛ የልዮን ጉባኤ እ.ኤ.አ. በ1274 ዓ.ም.፣ የፊረንጸ ጉባኤ እ.ኤ.አ. በ1439 ዓ.ም. እንዲሁም ጳጳስ በነዲክቶስ 12ኛ እ.ኤ.አ. 1336 ዓ.ም. እንደገለጹት፣ ሰው ሁሉ ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ሽልማቱን ወይም ቅጣቱን ይቀበላል። ይኸውም እንደሚከተለው ነው።

ሀ. በጣም ንጹሕ የሆነ ሰው ከሞተ በኋላ፣ ምንም እንኳ ያለ ሥጋ ው ቢሆንም ወዲያውኑ መንግሥተ-ሰማይ ገብቶ በነፍሱ ዘለዓለማዊ ብፅዕናትን ያገኛል።

ለ. ትናንሽ ኃጢአት ያለው ወይም ደግሞ የኃጢአት ካሣ (ቀኖና) ያልፈጸመ ከሞተ በኋላ ነፍሱ ወደ ንስሐ ቦታ ትሄዳለች። ካሣ ዋን ከፈጸመች በኋላ ወደ ሰማይ ታልፋለች።

ሐ. ትልቅ ኃጢአት ሠርቶ እስከ መጨረሻው ሳይጸጸት የሞተ ሰው ለዘለዓለም ይኮነናል።


መንግሥተ-ሰማይ

መንግሥተ-ሰማይ፣ እግዚአብሔር ፊት ለፊት የሚታይበትና በፍቅር በተቃጠለ ልብ የሚወደድበት ሁኔታ ነው። ቦታ ልንለው አንችልም፣ እግዚአብሔር በቦታ፣ አይወሰንምና (በሁሉም ቦታ ይገኛል)።

መንግሥተ-ሰማይ በብሉይ ኪዳን ታውቆ ነበር (ጥበብ 4፡ 16፣ ዳን ኤል.12፡ 2)፣ በአዲስ ኪዳን በልዩ ሁኔታ ይነገርለታል። ስለ መንግሥተ ሰማይ እጅግ ብዙ ጥቅሶች አሉ። ጌኢ.ክ. መንግሥተ-ሰማይን ሊከፍትልን ስለ መጣ ስለ መንግሥተ-ሰማይ ብዙ ጊዜ ረጅም ንግግሮች አድርጓል። ለምሳሌ፡- «በመንፈስ ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ፣ መንግሥተ-ሰማይ የእነርሱ ስለሆነች ደስ ይበላቸው» (ማቴ.5፡ 3)፣ «ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ» (ማቴ.13፡ 43)፣ «በሰማይ ሃብት ታገኛ ለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ» (ማቴ.19፡ 21)፣ ... ወ.ዘ.ተ.። ብዙ ጊዜ «የዘ ላለም ሕይወት» ይለዋል (ማቴ.19፡ 17፣ ዮሐ.3፡ 36፣ 6፡ 55... ወ.ዘ.ተ.)፣ አንዳንድ ጊዜም እንደ የሠርግ ግብዣ አስመስሎ ይናገራል (ማቴ.22፡ 2፣ 25፡ 10፣ ማቴ.8፡ 11፣ ወ.ዘ.ተ.)። አንድ ጊዜ እንዲያውም «ምድር» ብሎ ጠርቶታል፣ «የዋሆች ምድርን ይወርሳሉ» (ማቴ.5፡ 5) በማለት በተስፋ ምድር የተመሰለችውን ሰማያዊት የደስታ አገራችንን አመለከተ።

ከዚህ በፊት ወደ መንግሥተ-ሰማይ የገቡት እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። «ከዚህ በኋላ እነሆ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል እጅግ ብዙ ሰዎች አየሁ፣ እነርሱ ከሕዝብና ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ የተው ጣጡ ነበሩ፣ ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት (በሰማይ) ቆመው ነበር» (የዮሐ.ራእይ.7፡ 9)።

መንግሥተ-ሰማይ መኖሩን የዓለም ክርስቲየኖች በሙሉ ያመናሉ። ጀሆሻውያን ብቻ አይስማሙበትም። እነርሱ፣ አብዛኛው ሰው ለምድር እንጂ ለሰማይ አልተፈጠረም በማለት መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ፍላጐታቸው ስለሚተረጉሙት ይሳሳታሉ። እኛ ግን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስንና የሐዋርያቱን ትምህርት ተከትለን «እግዚአብሔር ሰውን ከሰው አያበላልጥም፣ አያደላምም» (የሐዋ.ሥራ.10፡ 34) የሚለውን አውቀን፣ ሁላችንም፣ አንድም ሳይቀር መንግሥተ-ሰማይን እንጠባበ ቃለን። «እኛ ገና የምትመጣውን ከተማ እንጠባበቃለን እንጂ ጸንታ የምትኖር ከተማ በዚህ ምድር የለችንም» (ዕብራ.13፡ 14)።



ከኃጢአት ነፃ የሆነች ነፍስ ከሥጋ በተለየች ጊዜ ወደ ሰማይ ትወጣለች

በመንግሥተ-ሰማይ እግዚአብሔርን፣ ማለትም ሥላሴን ማየት፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በክቡር ሰውነቱ፣ እንዲሁም እመቤታችን ማርያምን፣ መላእክትንና ቅዱሳን ዘመዶቻችንን ማግኘት እኛ ልናስበው ከምንችለው በላይ የሆነ ውብ፣ አስደሳችና አስደናቂ ነገር ስለሆነ በቃላት ልንገልጸው አንችልም። ቅዱስ ጳውሎስ የመንግሥተ-ሰማይን ፍንጭ በራእይ አይቶ በወረደ ጊዜ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- «የሰው ዓይን ያላየውን፣ የሰው ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰው ልብ ያላስበውን እግዚአብሔር ለሚወ ዱት አዘጋጅቷል» (1ቆሮ.2፡ 9)።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ሁላችንንም ወደዚሁ ዓላማ ያድርሰን። አሜን።

[redacted]

ንስሐ ቦታ በዚህ ዓለም [redacted]ነ ያልፈጸሙት ሰዎች የሚከሱበት ሁኔታ ነው። የመንግሥተ-ሰማይ በረንዳ ልንሰው እንችላለን። ምክንያቱም በንስሐ-ቦታ የሚገኙት ነፍሳት የመዳን ተስፋ ያላቸው ናቸው። የበረታው ሥቃያቸው እግዚአብሔርን አለማየታቸው ነው፣ ሌላ ሥቃይም አይታጣም፣ ግን አልተገለጸም። ብዙ ሊቃውንት እነ ጳጳስ ጎርጎርዮስ፣ ቅዱስ አጎስጢኖስ ቅዱስ ቶማስ በንስሐ ቦታ የሚገኙት ነፍሳት በእሳትም እንደሚሰቃዩ ያስተምራሉ። አንዳንድ ነፍሳት ከንስሐ-ቦታ ታይተው በምሥጢራዊ እሳት ይሠቃዩ እንደነበሩና ብዙ ጊዜ እዚያ እንደሚቆዩ ገልጸዋል። ንስሐ-ቦታ በብሉይ ኪዳንም ታውቆ ነበር፣ ምክንያቱም ይሁዳ ለሞቱበት ወታደሮች ካሣ ለመክፈል መሥዋዕት አሳረገ (2 መቃብያን 12፡ 43)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ንስሐ ቦታ ጥቂት ብቻ ነው የጠቀሰው። ለምሳሌ፡- ማቴ.12፡ 32 «በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» በማለት አንዳንድ ኃጢአት በሚመጣው ዓለም ይቅር እንደሚባል ገለጸ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ እውነት ስለሆነ፣ ይህንን ማመን አለ ብን (ጳጳስ ጎርጎርዮስ 1ኛ)። ማቴ.5፡ 25 ምንም እንኳ ስለ ሰዎች መታ ረቅ ቢናገርም፣ አንዳንዶች እንደሚተረጉሙት ኢየሱስ ምሳሌ አድርጎ የኃጢአታችንን ዕዳ ሁሉ በመንገድ ላይ እያለን እንድንከፍል ይመክረናል፣ አለበለዚያ ወደ እስር ቤቱ (ንስሐ-ቦታ) መግባታችን አይቀርም (አሪጀንስ)። ቅዱስ ጳውሎስ «በፍርድ ቀን መጥፎ ሥራ የሚገኝበት ሰው (ትልቅ ኃጢአት ባይሆንም) ይቀጣል። ድኅንነት (ሽልማት) ደግሞ በእሳት ውስጥ ካለፉ በኋላ ነው» (1ቆሮ.3፡ 15) በማለት ንስሐ-ቦታ መጥቀሱን የፊረንጸ ጉባኤ ይመሰክራል።

የሆነ ሆኖ የንስሐ-ቦታ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት በደንብ ይገለጻል። በሐዋርያት የተማሩት የመጀመሪያ ያመቹ ክርስቲያኖች የሞቱትን ሰዎች ካሣ ለመክፈል ጸሎት ያደርጉላቸው ነበር፣ ድሆችን ይመጸውታሉ፣ በተለይም ደግሞ መሥዋዕተ-ቅዳሴ ያሳ ርጉላቸው ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ መረዳት ከጥንት ጀምሮ እንደ ተለመደ ብዙዎች አበው፣ እነ ቆጵርያኖስ፣ ተርቱልያኖስ፣ ቄርሎስ ይመሰክራሉ። ካታኮምብ በሚባለው የሮማ ጥንታዊ መቃብሮች ውስጥ፣ የመጀመሪያ ዎቹ ክርስቲያኖች ለሞቱት ወገኖቻቸው «ከክርስቶስና ከቅዱሳን ጋር ዕረፍት፣ ብርሃንና ሰላም» ይለምኑላቸው እንደነበሩ የሚያስረዳ ጽሕፈት

እስከ ዛሬ ድረስ ይታያል። ወደ ሰማዕታትም ይለምኑላቸው ነበሩ፣ በተ ለይም ወደ ጴጥሮስና ጳውሎስ ያሳርጉ የነበሩት ልመናዎች እስከ ዛሬ ድረስ በግድግዳው ላይ ተቀርጸው ይታያሉ። ይህም እነዚያ ሰማዕታት ለሞቱት ምእመናን እንደ ጠበቃ ይቆጠሩ እንደነበሩ ያስረዳናል። እንዲ ሁም ወደ መንግሥተ-ሰማይ ለመግባት ፍጹም የሆነ ንጽሕና እንደሚያስ ፈልጋቸው ተረድተው ስለነበሩ፣ ለሐዋርያትና ለሰማዕታት ካልሆነ በቀር ለሞቱት ሁሉ ምሕረት ይለምኑላቸው ነበሩ። ይህን ማድረጋቸው የንስሐ-ቦታ ዕዳቸውን ሊከፍሉላቸው እንደፈለጉ ያስረዳል። ስለ ሙታን ቅዳሴ ማሳረግ (ማስቀደስ ወይም መቀደስ) በዓለም ሙሉ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ስለሆነ የበለጠ የንስሐ-ቦታ ማስረጃ ነው።

ንስሐ-ቦታ መኖሩን የማያምኑ፣ እነ አልቢጀንስስ፣ ግሪካውያን፣ በ መጨረሻም ፕሮቴስታንቶች ስለ ተነሡ፣ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህ ርት መርምራ በ2ኛ የልዮን ጉባኤ፣ በፊረንጸ ጉባኤና በተለይም በትሬንቶ ጉባኤ ስለ ንስሐ-ቦታ የተረጋገጠ ትምህርት ሰጠችን። እንዲሁም በቅዳሴ፣ በጸሎትና በሌላም መልካም ሥራ ለንስሐ-ቦታ ነፍሳት ካሳ መክፈል እን ደምንችል አረጋገጠችልን። 2ኛ የቫቲካን ጉባኤ፣ የንስሐ-ቦታ ሰምችን አስታውሶ፣ ባለፉት ጉባኤዎች የተገለጸው ትምህርት ይርጋ በማለት ለንስሐ-ቦታ ነፍሳት ካሣ እንድንከፍል ያበረታታናል (1፡ 49-50)። ጳጳስ ጳውሎስ 6ኛ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1968 ዓ.ም. በደገሙት ረጅም ጸሎተ-ሃይ ማኖት የንስሐ-ቦታ ነፍሳትን ሁለት ጊዜ ይጠቅሱዋቸዋል። እንግዲህ መጠራጠሩን ትተን ለሞቱት ወንድሞቻችን በትጋት እንጸልይላቸው። «በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል» (ማቴ.7፡ 2)።

ገሃነመ እሳት

ገሃነመ እሳት እግዚአብሔር ከቶ የማይታይበትና የማይፈቀርበት ሥቃይ የተሞላ ሁኔታ ነው። ከዚህ የከፋ ነገር ልናስብ አንችልም። የ ጥፋት ጥፋት ነው። ምክንያቱም የተኰነኑት ሰዎች ለዘለዓለም ከእግዚ አብሔር ተለይተው ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ውበት፣ ሃብት፣ ምቾትና ፍቅር እኛ ልናስበው ከምንችለው በላይ የሚያስመኝና የሚማርክ ስለሆነ፣ ይህንን ዕድል ማጥፋት በዓለም ላይ ሊያጋጥሙን ከሚችሉት ሥቃዮች ሁሉ የባሰ ነው። የሚያሳብድ ነገር ነው። መድኃኒት የለውምና።

ገሃነመ እሳት በብሉይ-ኪዳን ዘመንም ታውቆ ነበር፤ (ዮዲት 16፡ 17፣ ዳንኤል 12፡ 2)። በአዲስ ኪዳን ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያት ትምህርት በበለጠ ሁኔታ ተገለጸ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

ንስሐ ቦታ

ንስሐ ቦታ በዚህ ዓለም የኃጢአታቸውን ካሣ በደንብ ያልፈጸሙት ሰዎች የሚክሱበት ሁኔታ ነው። የመንግሥተ-ሰማይ በረንዳ ልንለው እንችላለን። ምክንያቱም በንስሐ-ቦታ የሚገኙት ነፍሳት የመዳን ተስፋ ያላቸው ናቸው። የበረታው ሥቃያቸው እግዚአብሔርን አለማየታቸው ነው፣ ሌላ ሥቃይም አይታጣም፣ ግን አልተገለጸም። ብዙ ሊቃውንት እነ ጳጳስ ጎርጎርዮስ፣ ቅዱስ አጎስጢኖስ ቅዱስ ቶማስ በንስሐ ቦታ የሚገኙት ነፍሳት በእሳትም እንደሚሰቃዩ ያስተምራሉ። አንዳንድ ነፍሳት ከንስሐ-ቦታ ታይተው በምሥጢራዊ እሳት ይሠቃዩ እንደነበሩና ብዙ ጊዜ እዚያ እንደሚቆዩ ገልጸዋል። ንስሐ-ቦታ በብሉይ ኪዳንም ታውቆ ነበር፣ ምክንያቱም ይሁዳ ለሞቱበት ወታደሮች ካሣ ለመክፈል መሥዋዕት አሳረገ (2 መቃብያን 12፡ 43)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ንስሐ ቦታ ጥቂት ብቻ ነው የጠቀሰው። ለምሳሌ፡- ማቴ.12፡ 32 «በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» በማለት አንዳንድ ኃጢአት በሚመጣው ዓለም ይቅር እንደሚባል ገለጸ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ እውነት ስለሆነ፣ ይህንን ማመን አለብን (ጳጳስ ጎርጎርዮስ 1ኛ)። ማቴ.5፡ 25 ምንም እንኳ ስለ ሰዎች መታረቅ ቢናገርም፣ አንዳንዶች እንደሚተረጉሙት ኢየሱስ ምሳሌ አድርጎ የኃጢአታችንን ዕዳ ሁሉ በመንገድ ላይ እያለን እንድንከፍል ይመክረናል፣ አለበለዚያ ወደ እስር ቤቱ (ንስሐ-ቦታ) መግባታችን አይቀርም (ኦሪጀንስ)። ቅዱስ ጳውሎስ «በፍርድ ቀን መጥፎ ሥራ የሚገኝበት ሰው (ትልቅ ኃጢአት ባይሆንም) ይቀጣል። ድኅንነት (ሽልማት) ደግሞ በእሳት ውስጥ ካለፉ በኋላ ነው» (1ቆሮ.3፡ 15) በማለት ንስሐ-ቦታ መጥቀሱን የፊረንጸ ጉባኤ ይመሰክራል።

የሆነ ሆኖ የንስሐ-ቦታ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት በደንብ ይገለጻል። በሐዋርያት የተማሩት የመጀመሪያ ያመቹ ክርስቲያኖች የሞቱትን ሰዎች ካሣ ለመክፈል ጸሎት ያደርጉላቸው ነበር፣ ድሆችን ይመጸውታሉ፣ በተለይም ደግሞ መሥዋዕተ-ቅዳሴ ያሳርጉላቸው ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ መረዳዳት ከጥንት ጀምሮ እንደ ተለመደ ብዙዎች አበው፣ እነ ቆጵርያኖስ፣ ተርቱልያኖስ፣ ቄርሎስ ይመሰክራሉ። ካታኮምብ በሚባለው የሮማ ጥንታዊ መቃብሮች ውስጥ፣ የመጀመሪያ ያመቹ ክርስቲያኖች ለሞቱት ወገኖቻቸው «ከክርስቶስና ከቅዱሳን ጋር ዕረፍት፣ ብርሃንና ሰላም» ይለምኑላቸው እንደነበሩ የሚያስረዳ ጽሕፈት

እስከ ዛሬ ድረስ ይታያል። ወደ ሰማዕታትም ይለምኑላቸው ነበሩ፣ በተለይም ወደ ጴጥሮስና ጳውሎስ ያሳርጉ የነበሩት ልመናዎች እስከ ዛሬ ድረስ በግድግዳው ላይ ተቀርጸው ይታያሉ። ይህም እነዚያ ሰማዕታት ለሞቱት ምእመናን እንደ ጠበቃ ይቆጠሩ እንደነበሩ ያስረዳናል። እንዲሁም ወደ መንግሥተ-ሰማይ ለመግባት ፍጹም የሆነ ንጽሕና እንደሚያስፈልጋቸው ተረድተው ስለነበሩ፣ ለሐዋርያትና ለሰማዕታት ካልሆነ በቀር ለሞቱት ሁሉ ምሕረት ይለምኑላቸው ነበሩ። ይህን ማድረጋቸው የንስሐ-ቦታ ዕዳቸውን ሊክፍሉላቸው እንደፈለጉ ያስረዳል። ስለ ሙታን ቅዳሴ ማሳረግ (ማስቀደስ ወይም መቀደስ) በዓለም ሙሉ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ስለሆነ የበለጠ የንስሐ-ቦታ ማስረጃ ነው።

ንስሐ-ቦታ መኖሩን የማያምኑ፣ እነ አልቢጀንስስ፣ ግሪካውያን፣ በመጨረሻም ፕሮቴስታንቶች ስለ ተነሡ፣ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት መርምራ በ2ኛ የልዮን ጉባኤ፣ በፊረንጸ ጉባኤና በተለይም በትሬንቶ ጉባኤ ስለ ንስሐ-ቦታ የተረጋገጠ ትምህርት ሰጠችን። እንዲሁም በቅዳሴ፣ በጸሎትና በሌላም መልካም ሥራ ለንስሐ-ቦታ ነፍሳት ካሳ መክፈል እንደምንችል አረጋገጠችልን። 2ኛ የቫቲካን ጉባኤ፣ የንስሐ-ቦታ ሰዎችን አስታውሶ፣ ባለፉት ጉባኤዎች የተገለጸው ትምህርት ይርጋ በማለት ለንስሐ-ቦታ ነፍሳት ካሣ እንድንከፍል ያበረታታናል (1፡ 49-50)። ጳጳስ ጳውሎስ 6ኛ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1968 ዓ.ም. በደገሙት ረጅም ጸሎተ-ሃይማኖት የንስሐ-ቦታ ነፍሳትን ሁለት ጊዜ ይጠቅሱዋቸዋል። እንግዲህ መጠራጠሩን ትተን ለሞቱት ወንድሞቻችን በትጋት እንጸልይላቸው። «በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል» (ማቴ.7፡ 2)።

ገሃነመ እሳት

ገሃነመ እሳት እግዚአብሔር ከቶ የማይታይበትና የማይፈቀርበት ሥቃይ የተሞላ ሁኔታ ነው። ከዚህ የከፋ ነገር ልናስብ አንችልም። የጥፋት ጥፋት ነው። ምክንያቱም የተኰነኑት ሰዎች ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ተለይተው ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ውበት፣ ሃብት፣ ምቾትና ፍቅር እኛ ልናስበው ከምንችለው በላይ የሚያስመኝና የሚማርክ ስለሆነ፣ ይህንን ዕድል ማጥፋት በዓለም ላይ ሊያጋጥሙን ከሚችሉት ሥቃዮች ሁሉ የባሰ ነው። የሚያሳብድ ነገር ነው። መድኃኒት የለውምና።

ገሃነመ እሳት በብሉይ-ኪዳን ዘመንም ታውቆ ነበር! (ዮዲት 16፡ 17፣ ዳንኤል 12፡ 2)። በአዲስ ኪዳን ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያት ትምህርት በበለጠ ሁኔታ ተገለጸ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

«ገሃነመ-እሳት» (ማቴ.5፡ 22፣ 10፡ 28)፣ «የዘላለም እሳት» (ማቴ.18፡ 8፣ 25፡ 41)፣ «የዘላለም ቅጣት» (ማቴ.25፡ 46)፣ «የማይጠፋ እሳት» (ማቴ.3፡ 12) ይለዋል። እንዲሁም «ገሃነም ትሉ የማይሞትበት፣ እሳቱ የማይጠፋበት ሥፍራ ነው» (ማር.9፡ 46)፣ «ጨለማ፣ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ያለበት ቦታ» (ማቴ.22፡ 13) ይለዋል። ሐዋርያትም ነሃነመ-እሳት መኖሩን ገልጸዋል። «እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችን ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን በእሳት ነበልባል ይበቀላቸዋል» (2ተሰሎ.1፡ 8)፣ «ሌሊትና ቀን ለዘላለም ይሠቃያሉ» (ራእይ 20፡ 10)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገሃነመ-እሳት መኖሩን የሚነግሩን ጥቅሶች ቢያንስ 14 ይሆናሉ። በእውነቱ የተረጋገጠ ግልጽ ነገር ነው። ነገር ግን ብዙዎች ነሃነመ-እሳት የለም ለማለት ይደፍራሉ። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በትጋት አይከታተሉትም ማለት ነው። ድሮ በጥንት ዘመን አሪጀንስ የተባለ ካህን «በርኅራኄ ምክንያት የተኰነኑት ሰዎች በዓለም መጨረሻ ጊዜ ይድናሉ» የሚል ትምህርት አስፋፍቶ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ግን ይህንን አስተያየት እንደ መናፍቅነት አወገዘችው። ከዚያ በኋላም ብዙዎች ገሃነመ-እሳትን እንደ ንሰሐቦታ፣ ማለት እንደ ጊዜያዊ ሥቃይ አሰቡት። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ግን፣ በተለይም ቅዱስ አጎስጢኖስ፣ ጳጳስ ቅዱስ ጎርጎርዮስ 1ኛ... ወ.ዘ.ተ. ገሃነመ-እሳት ዘላለማዊ መሆኑን አስረዷ ቸው። «ገሃነመ-እሳት ዘላለማዊ ባይሆን ኖሮ መንግሥተ-ሰማይም ዘላለ ማዊ ባልሆነም ነበር፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የሁለቱንም ዘላለማዊ ነት በትክክል ቃል ገልጾታል» ብለው ረቱዋቸው።

ሕዝበ-ክርስቲያን እንዳይጠራጠሩ፣ ቤተ ክርስቲያን ገሃነመ-እሳት መኖሩና ዘላለማዊ መሆኑ የሃይማኖት ትምህርት (አንቀጸ-ሃይማኖት) ነው ብላ ገለጸችው። 4ኛ የላቴራን ጉባኤና የፊረንጅ ጉባኤ፣ እንዲሁም ጳጳስ በነዲክቶስ 12ኛ ይህንን ትምህርት አረጋግጠዋል። ዛሬም የገሃነመ-እሳትን መኖር የማያምኑ ገና አይታጡም፣ በተለይም ጀሆቫውያን፣ ኃጢአተኞች እንደሚጠፉ፣ ማለትም ህላዌያቸው እንዳልነበረ ይሆናል ብለው ስለሚያስተምሩ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት በሙሉ ይክዳሉ። ይህ ደግሞ የከፋ ዕውርነት ነው። የእግዚአብሔርንም ጥበብ ይቃወማሉ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈጣሪ አንጂ አጥፊ አይደለም። እንግዲህ ገሃነመ-እሳት መኖሩን ካለማመናችን የተነሣ እንዳንኰነን እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር ሁላችንንም ለመንግሥተ-ሰማይ ነው የፈጠረን። «የእግዚ አብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ነው» (1ጢሞ.2፡ 4)፣ «እግዚአብ ሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው፣ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም።» (ዮሐ.3፡ 17)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

የሞተልን እኛ እንድንድን ነውና እምነት ካለን አንፍራ፣ ፈቃዱን ግን መፈጸም አለብን። ታማኞች እንድንሆን ደግሞ ጸሎትና ምሥጢራትን እናዘውትር። ሰራሳችን ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎች ሕዝቦች ድኅንነትም እንለምን።

ለተኰነኑ ሰዎች ርኅራኄ ሊኖረን ይገባል፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ የተሰማው ርኅራኄ በጣም ከፍተኛ ስለነበረ ሰዎች እንዳይኰነኑ ብሎ በሚዘገንን ሁኔታ ሞተ። አሁንም ኃጢአተኞችን በ ሙሉ በሕይወታቸው እያሉ ይጠራቸዋል፣ ወዲያውኑ ሲመለሱ በምሕ ረቱ ራርቶላቸው ያቅፋቸዋል (ሉቃ.15፡ 20)። ይህም ማለት ጌታ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ሰው ሁሉ እንዲድን ይፈልጋል፣ የድኅነት ጸጋም ይሰጣ ቸዋል። ነገር ግን ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት አለበት።

ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም የማይቸገሩ፣ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻም አውቀው የሚበድሉት፣ በፍጹም መጸጸት የማይፈለጉ፣ ሳይቀጡ እንደማይቀሩ የተረጋገጠ ነገር ነው። ምክንያቱም «በእግዚአብ ሔር ላይ መቀለድ አይቻልምና» (ገላ.6፡ 7)። በክፋታቸው ሰይጣንን የሚመስሉት ለሰይጣንና ለተከታዮቹ የተዘጋጀውን ቅጣት ይቀበላሉ (ማቴ.25፡ 41)። ይህንን ቅጣት በራሳቸው ላይ የሚያወርዱት እነርሱ ራሳቸው ናቸው፣ ምክንያቱም ፍርዳቸውን ከተቀበሉ በኋላ ከእግዚአብ ሔር የሚለዩት እነርሱ ራሳቸው ናቸው እንጂ እግዚአብሔር እስኪያባርራ ቸው ድረስ አይጠብቁም። ነሃነመ-እሳት፣ ከእግዚአብሔር መለየትና ከቶ እግዚአብሔርን እንደገና አለማየት ነው እንጂ ቦታ አይደለም። የተኰነኑት ሰዎች በመንፈስ ደረቆች ስለሆኑ አይጸጸቱም። መናፍስት ስለሆኑ ለዘላለም ፍላጐታቸውን አይቀይሩም። የፍቅር ሥራ ቢያደርጉ መንግሥተ-ሰማይን ባገኙ ነበር፣ ነገር ግን ይህ ለውጥ አይሆንላቸውም። እነርሱ እግዚአብ ሔርን ሊያፈቅሩ አይችሉም። «ልባቸው እንደ ተጨመቀ ፍሬ ስለሆነ ለ ዘወትር ደርቋል» (ቅ.ዮሐንስ ቪያነ)። ገሃነመ-እሳት ማለት ፍቅርን ማጣት ማለት ነው። መንግሥተ-ሰማይ አስደሳች ፍቅር ስለሆነ ጊዜ እያለን እግዚአብሔር አምላካችንን እንውደድ። ፍቅሩን እየጨመርን እንሂድ፣ ፍቅሩም ለዘላለም ያስደስተናል። አሜን።

የሕጻናት ሲኦል

ስለ የሕፃናት ሲኦል የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የለንም። ስለዚህ ሳይጠመቁና የአዳም ኃጢአት ሳይደመሰስላቸው የሚሞቱት ሕፃናት

ወዴት እንደሚሄዱ አናውቅም። የፊረንጻ ጉባኤ እንደሚለው «የአዳም ኃጢአት ሳይደመሰስለት ማንም መንግሥተ-ሰማይን ሊወርስ ስለማይችል» ያልተጠመቁት ሕፃናት ወደ መንግሥተ-ሰማይ የመግባት መብት የላቸውም። ነገር ግን የራሳቸው ኃጢአት ስለሌላቸው ምንም ሥቃይ አይገባቸውም። በዚህ ምክንያት ብዙ ሊቃውንት ያልተጠመቁት ሕፃናት እግዚአብሔር ወደማይታይበትና ሥቃይ ወደሌለበት ሲኦል እንደሚሄዱ ያስቡ ነበር። እንደ አስተያየታቸው ከሆነ ይህ ሲኦል ዘለዓለማዊ ነው። (በብሉይ ኪዳን ጻድቃን ይጠበቁበት የነበረው ሲኦል ግን ድሮ አልቋል)።

ዛሬ ግን ብዙ ሊቃውንት ያልተጠመቁት ሕፃናት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትሩፋትና (አርዳታና) በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ሲሞቱ የአዳም ኃጢአት ስለሚደመሰስላቸው ወደ መንግሥተ-ሰማይ ይገባሉ ብለው ያስባሉ። እንደነዚህ ሊቃውንት አስተያየት ከሆነ ዘለዓለማዊ ሲኦል የለም። ይህ ግን የተረጋገጠ ትምህርት አይደለም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ስለዚህ ጉዳይ የተናገረችው ነገር የለምና። ስለዚህ ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ 2ኛ እንዳሉት «ሳይጠመቁ ለሞቱት ሕፃናት የእግዚአብሔርን ምሕረት እንለምንላቸዋለን»፣ በተቻለን መጠን ደግሞ ሳይሞቱ እናጥም ቃቸው።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለ2ኛ ጊዜ ወደዚህ ምድር ይመጣል፣ ወዲያውኑ የመጨረሻ ሁኔታዎች ማለትም፣ (የሙታን ትንሣኤ፣ የጋራ ፍርድ፣ የዓለም መጨረሻ) ይፈጸማሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት እንዳለበት ደጋግሞ ገልጾታል። «የሰው ልጅ በኃይልና በታላቅ ክብር በደመና ላይ ሆኖ ይመጣል» (ማቴ.24፡ 30)፣ ኢየሱስ በቀያፋ (በሊቀ ካህናቱ) ፊትም ይህንኑ ትንቢት ተናገረ (ማቴ.26፡ 64)፣ እርሱ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ሁለት መላእክት በዚሁ ዓይነት ተመልሶ እንደሚመጣ ለደቀመዛሙርቱ አስታወቁዋቸው (የሐዋ.ሥራ 1፡ 11)፣ ቅዱስ ጳውሎስም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ላይ እንደሚፈርድ ገልጾ ሰበከ (2ጢሞ.4፡ 1)። ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ «ክርስቶስ በሕይወት ባሉትና በሞቱት ላይ ሊፈርድ ተዘጋጅቷል» ይላል (1ጴጥ.4፡ 5)። «ዓለም ሁሉ እስኪታደስ ድረስ ኢየሱስ በሰማይ ይቆያል» (የሐዋ.ሥራ 3፡ 21)፣ ይህም ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ በሰማይ ይቆያል፣ ያኔ ግን ይመጣል ማለት ነው። የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት በችግርና በጭንቅ አይደለም፣ ሊሠቃይና ሊዋረድ

አይደለም የሚመጣው፣ በታላቅ ኃይልና ግርማ ነው እንጂ (ማቴ.24፡ 30)። ሐቅን ለመግለጽ፣ በሐሜትና በስድብ የጠፋውን የራሱንና የጻድቃንን ክብር ለመመለስ ነው የሚመጣው። ስለዚህ «ማራና-ታ-ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!» ብለን መጸለይ መልካም ነው (የዮሐ.ራእይ 22፡ 20)።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣትና የዓለም መጨረሻ በአንድ ጊዜ ይሆናል (ማቴ.24፡ 3)፣ ይህ መቼ እንደሚሆን ከእግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቅም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ሁልጊዜ ተዘጋጅተን እንድንቆይ ስለፈለገ ለሐዋርያቱ «ጊዜውን እኔም አላውቅም» አላቸው። ይህ አነጋገሩ «አሁን ልገልጽላችሁ አልችልም (አልፈልግም)» ማለቱ ነበር፣ ምክንያቱም እርሱ አምላክ ስለሆነ ሁሉን ነገር ያውቃል። ምንም እንኳ የዓለም መጨረሻ መቼ መሆኑን ባናውቅም፣ የመምጣቱ ምልክቶች ተነግረውናል፣ ማለትም፡- ከመምጣቱ በፊት አንዳንድ ነገሮች መፈጸም አለባቸው። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

1 - ማቴ.24፡ 14 «ወንጌል ለዓለም ሕዝብ በሙሉ ሳይሰበክ የዓለም መጨረሻ አይመጣም»። ይህ ስብከት ገና አልተፈጸመም፣ ምክንያቱም በብዙ አገሮች ትንሽ ወሬው ተሰምቷል እንጂ ወንጌል ገና በግልጽ አልተሰበከም።

2 - ሮሜ 11፡ 25 «የተጠሩት አረማውያን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እስኪመጡ ድረስ እስራኤላውያን በእምቢተኝነት ይቆያሉ»። ይህም ማለት የዓለም ሕዝብ ሁሉ ወደ ክርስትና ሲገባ እስራኤላውያንም ይመለሳሉ። እስከ አሁን ድረስ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ወደ ክርስትና አልገቡም፣ እስራኤላውያንም በክርስቶስ ማመን አልጀመሩም።

3 - 2ተሰሎንቄ 2፡ 3-4 «አስቀድሞ የመጪረሻው ክሕደት ሳይሆንና ገሃነም የሚገባው የዐመፅ ሰው የሆነው ሳይገለጥ፣ ያ ቀን አይመጣም»፣ እነዚህ ሁለት መከራዎች አልተፈጸሙም። ምክንያቱም ምንም እንኳ በዓለም ውስጥ ክህደት ቢኖርም ቅዱስ ጳውሎስ የተነበየው በጣም የከፋውን ነገር ነው።

4 - ማቴ.24፡ 29 «ፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃንዋን አታሳይም፣ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፣ የሰማያት ኃይሎችም ይናወጣሉ» የሚለውን ትንቢት ቃል በቃሉ ከተቀበልነው በርግጥ ገና አልተፈጸመም፣ በምሳሌ ተናግሮ እንደሆነም፣ ማለትም የታላላቅ ሰዎችን ክሕደት ማለቱ እንደሆነም እኩም ቢሆን ገና አልተፈጸመም።

5 - ኢሳይያስ 11፡ 6 «ተኵላና በግ በአንድነት ተባብረው በሰላም ይኖራሉ፣ ነብርም ከፍየል ግልገሎች ጋር አብሮ ይመሰጋል» የሚለው ትንቢት የሰው ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ወደ ማሕበራዊ ወንድማማችነት መድረስ እንዳለባቸው ያስረዳናል። ነገር ግን ይህ ሙሉ በሙሉ አይሆንም፣ ምክንያቱም እንክርዳዱ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ አብሮ ይቆያል (ማቴ.13፡ 40)። አብዛኛው ዓለም ሰላምንና ወንድማማችነትን ማግኘት አለበት። ከዓለም መጨረሻ በፊት ወደ እዚህ የክርስትና አላማ መድረስ ግዴታ ነው። ምክንያቱም ትንቢት ሁሉ እንዲፈጸም ግዴታ ነውና (ማቴ.5፡ 18)። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ዓለም እንደ ተሻሻለና ገና በመሻሻል ላይ እንዳለም ግልጽ ነው። የሰዎች ወንድማማችነታዊ ፍቅር ግን ዛሬም ገና በቂ አይደለም።

ስለዚህ እነዚህ ትንቢቶች ሁሉ ስላልተፈጸሙ የዓለም መጨረሻ ገና ሩቅ ነው ለማለት እንችላለን። ገና ብዙ ሺ ዓመታትም ቀርቶ ሊሆን ይችላል። «የዓለም መጨረሻ አሁን ደርሷል» እያሉ የሚጠባበቁት ጀሆቫውያን ምንኛ አሳሳቾች ናቸው!

የሆነ ሆኖ ለእያንዳንዱ ሰው ግላዊ የዓለም መጨረሻ ቅርብ ነው። ምክንያቱም ዓይኖቼ በሞት ከተዘጉ ፀሐይ ትጪልምብኛለች፣ ሥጋዬ ወደ መቃብር ከተወሰደ በኋላ ለእኔ የዓለም መጨረሻ ነው። እኔ ብቻዬን ፍርዴን ከተቀበልሁ የሚሰጠኝ ዕጣ ልክ በጋራ ፍርድ ጊዜ እንደሚሰጠን ዓይነት ነው። ስለዚህ ስለ ዓለም መጨረሻ ከመጨነቅ በቅርብ ጊዜ ስለሚመጣው ሞቴ በትጋት ማሰብ አለብኝ።

የሙታን ትንሣኤ

የሙታን ትንሣኤ የሃይማኖታችን ትልቁ ትምህርት ነው። ስለ ሙታን ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ ያስረዳናል። ለምሳሌ፡- «ከወገኖቻችን መካከል የሞቱት ተነሥተው እንደገና በሕይወት ይኖራሉ፣ በድናቸውም እንደገና ሕይወት ያገኛል። ወደ መቃብር የወረዱ ሁሉ ተነሥተው በደስታ እልል ይላሉ። የጠል ነጠብጣብ ለምድር ሕይወትን እንደሚሰጥ፣ እግዚአብሔር ከሞቱ ብዙ ጊዜ የሆናቸውን ተነሥተው በሕይወት እንዲኖሩ ያደርጋል» (ኢሳ.26፡ 19)። «አስቀድመው ከሞቱት ሰዎች ብዙዎቹ ተነሥተው እንደገና በሕይወት ይኖራሉ፤ ከእነርሱም አኩሌቶቹ የዘላለም ሕይወት አግኝተው ሲደሰቱ፣ አኩሌቶቹ ለዘላለም በሐፍረትና በጉስቁልና ይሠቃያሉ» (ዳንኤል 12፡ 2)። «በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው

በሕይወት ይኖራሉ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል» (ዮሐ.5፡ 28-29)። «ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ» (ዮሐ.6፡ 40)። «በክርስቶስ ምክንያት ሰው ሁሉ ሕይወትን ያገኛል። ይህም የሚሆነው በየተራ ነው፤ ክርስቶስ ከሞት የመነሣት የመጀመሪያ ምሳሌ ነው፤ በኋላም ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ከሞት ይነሣሉ» (1ቆሮ.15፡ 22-23)።

በቤተ ክርስቲያን ትውፊትም ብዙ ምስክር አለ፣ ለምሳሌ፡- የሐዋርያት ጸሎተ-ሃይማኖት፣ ዲዳኪ፣ አተናጎራስ፣ ተርቱልያኖስ፣ የአትናቴዎስ ጸሎተ-ሃይማኖት። እንዲሁም ብዙ ጉባኤዎችና ጳጳሳት ሰዎች ሁሉ በምድራዊ ሕይወታቸው ጊዜ ለብሰውት የነበሩትን ሥጋ ለብሰው እንደ ሚነሡ አስተምረዋል። በተለይም 4ኛ የላቴራን ጉባኤ ይህንን ነገር ስላ ረጋገጠው በግድ ማመን አለብን።

እንግዲህ ከሞት በኋላ ሥጋችን በመቃብር ውስጥ ይበሰብሳል፣ ይሁን እንጂ ትል ብዙ ጊዜ በመሬት ውስጥ ከተደበቀ በኋላ ወደ ውብ ብራቢሮ እንደሚለወጥ ሁሉ፣ ሥጋችንም በዓለም መጨረሻ አዲስ ሕይወትንና ውበትን ያገኛል። የጻድቃን ሥጋ እንደ መላእክት ይሆናል፣ ማለትም የማይሞት፣ ብሩህ ጤናማ፣ ቀላልና ረቂቅ ይሆናል (1ቆሮ.15፡ 43-44፣ 53፣ ማቴ.13፡ 43፣ 22፡ 30)።



«በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል» (ዮሐ.5፡ 28)

የሚነሣው ሥጋችን አሁን ለብሰን ያለነው ሥጋ ነው፣ ማለትም ሰውነታችንን የሚያቆምና ከሌሎች የሚለየን መልክና ዓይነት አይጠፋም። ይሁን እንጂ አሁን የለበስነው ዓይነት ግዙፍ ሥጋ አይደለም የሚነሣው። ምክንያቱም «ሥጋዊ አካል ሆኖ የተዘራው፣ መንፈሳዊ አካል ሆኖ ይነሣል» (1ቆሮ.15፡ 44)፣ «ሁላችንም እንለወጣለን» (1ቆሮ.15፡ 51)፣ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተዋረደውን ሰውነታችንን በመለወጥ የእርሱን ክቡር ሰውነት እንዲመስል ያደርገዋል» (ፊልጵ.3፡ 20-21)። ሥጋችን ስለሚለወጥ ነው መንግሥተ ሰማይን የሚወርሰው፣ ምክንያቱም «ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱምና» (1ቆሮ.15፡ 50)።

የሙታን ትንሣኤ እኛ ልንረዳው የማንችል ምሥጢር ነው። ምክንያቱም ምንም እንኳ በትንሣኤ እንደ መላእክት ብንሆንም (ማቴ.22፡ 30) እውነተኛ ሥጋ ነው የምንለብሰው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በተነሣ ጊዜ እውነተኛ ሥጋውን ነው የለበሰው። እኛም በዚሁ ዓይነት ሰውነት ይኖረናል (ፊልጵ.3፡ 21)። ይህ ትምህርት ለጊዜው ከዓቅማችን በላይ ስለሆነ አሁን ልንረዳው አንችልም።


የኛ ትንሣኤ ከአልአዛር ትንሣኤ የተለየ ይሆናል፣ ምክንያቱም እርሱ በግዙፍና በሚች ሥጋ ነው የተነሣው፣ እኛ ግን በመንፈሳዊና በማይሞት ሥጋ ነው የምንነሣው። በትንሣኤ የምናገኘው አዲስ ሁኔታ ከመጀመሪያው የአዳም አኗኗርም ይለያል፣ ምክንያቱም አዳም ግዙፍ ሥጋ ነበረው። በትንሣኤያችን ጊዜ ነፍስ ከሥጋ ላይ ፍጹም የበላይነትን ስለምታገኝ ሰውነታችን ወደ ፍጻሜ ይደርሳል። እንግዲህ ይህን ነገር ትንሣኤ ከ ተፈጸመ በኋላ እንረዳዋለን።

የተከሰኑት ሰዎች ሥጋም ፍርዱን ለመቀበል ይነሣል፣ በዚህ ዓለም ነፍስና ሥጋ ኃጢአት ለመሥራት እንደተባበሩ ሁሉ በወዲያኛው ዓለምም በሕብረት ይፈረድባቸዋል።

የጋራ ፍርድ

ከሞት በኋላ ግላዊ ፍርድና (ኩነኔና) ሽልማት ይፈጸማል፣ ይህ ግን በቂ ፍርድ አይደለም፣ ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ክብር እንዲሁም ለሐቅ ክብር የጋራ ፍርድ አስፈላጊ ነው። በዚህ ዓለም ዓመጸኞች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዋረዱት፣ ስሙንም አጠፉ፣ ቅዱሳንንም አሙዋቸው፣ ጠሉዋቸው፣ አሳደዱዋቸውም። ይህ ውርደት ሊጠፋና ሐቅ ሊገለጽ ይገ

ባል፣ የጻድቃን ንጽሕና ሊካሥና የዓመጸኞች ሐሰት ተገልጾ ሊቀጣ ይገባል። በዚህ ዓለም በሰው ያልታወቀ ነገር ሁሉ በዚያን ጊዜ ይገለጻል።



የጋራ ፍርድ (ማቴ.25፡ 31)፣ «አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ» (የዮሐ.ራእይ 1፡ 7)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጋራ ፍርዱን የሚፈጽመው (የሚያካሂደው) መቼ ነው? ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም ሲመጣና ወዲያውኑ ሙታን ሲነሡ፣ በዚያን ጊዜ የጋራ ፍርድ ይፈጸማል። «የሰው ልጅ (ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) በመላእክቱ ሁሉ ታጅቦ በክብር ሲመጣ በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል፤ ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ» (ማቴ.25፡ 31)። መለኮታዊው ፍርድ፣ ሰዎች በፍርድ ቤት እንደሚናገሩት ዓይነት ለሆን ግዴታ አይደለም፣ ምክንያቱም ወደ ሁሉም ቦታ የሚተላለፍ ኃይለኛ ብርሃን የሰዎችን ሁሉ ነፍስ ያበራል። ተሠውሮ የሚቀር አንድም ነገር የለም (1ቆሮ.4፡ 5)። ተደብቆ የነበረው በደልና ኃጢአት ሁሉ ይገለጻል። በድብቅ የተሠራው መልካም ነገርም ይታያልና ሐቅ ወደ አደባባይ

ትወጣለች። በመጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀኙ በኩል ያሉትን (ጻድቃን) «እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ! ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ የተዘጋጀ ላችሁን መንግሥት ውረሱ» ይላቸዋል (ማቴ.25፡ 34)። ከዚህ በኋላ በግራው በኩል ላሉት (ኃጢአን) «እናንተ የተረገማችሁ! ከእኔ ወዲያ ራቁ! ለሰይጣንና ለተከታዮቹ መላእክት ወደተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ» ይላቸዋል። (ማቴ.25፡ 41)። ስለዚህ እነዚህ ወደ ዘላለም ቅጣት ሲሄዱ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴ.25፡ 46)። ሁላችንም ለመንግሥተ-ሰማይ የተፈጠርን ስለሆንን ወደዚህ የብፅዕ ነት ዓላማችን ለመድረስ እንታገል። በእምነትና በመልካም ሥራም እን ትጋ። በተለይም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ፍርድ የጠቀሳቸ ውን የምሕረት ሥራዎች (ማቴ.25፡ 35-36) አስታውሰን በተግባር ላይ እናውለው።

ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ማብራሪያ

ስለ መጨረሻው የዓለም ፍርድ አንድ አስፈላጊ ነገር በደንብ እናስተ ውል። ፈራጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። ዓለምን የሚፈርድ ሌላ አይደለም። ይህንን በታላቅ ጥንቃቄ መመልከት አለብን። ምክንያቱም ዛሬ በዓለም ውስጥ ካሉት የሃይማኖት ስሕተቶች ውስጥ የበሃይ ትም ሀርት አንዱ ነው። እነርሱ ክርስቶስ አልፎአል፣ በእርሱ ፈንታ ባሑላ መጥቶአል፣ በማለት በክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት የምንጠባበቀው የ ዓለም ፍርድ በባሑላ እንደተፈጸመ ሊያስረዱን ይፈልጋሉ። ትምህርታ ቸው ስሕተት መሆኑ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትና ንትም ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው፣ አይለወጥም» (ዕብራ.13፡ 8) የ ሚለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም አያልፍም ማለት ነው። እርሱ የሚፈጽመው ፍርድ በታላቅ ኃይልና ግርማ፣ በክብርም ታጅቦ ይሆናል (ማቴ.24፡ 30፣ 25፡ 31)። ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ተሰብስበው እንደሚታይ መብረቅ ያዩታል (ማቴ.24፡ 27)። ክርስቶስ ከሰማይ የሚመ ለሰው በዓለም መጨረሻና በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ብቻ ነው (ማቴ.24፡ 31)። ከዚያ በፊት ግን አይመጣም (የሐዋ.ሥራ 3፡ 21)። ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ በሕይወታችን ዘመን የሠራነውን ሁሉ ልናቀርብለት እንገደዳለን።

ባሑላ ግን በድኽነትና በስደት የሕይወት ዘመኑን ጨረሰ እንጂ ከሰማይ ወርዶ አያውቅም። የፈራጅ ግርማ ለብሶ አያውቅም፣ ከጥቂት ሰዎች በቀር ያየውም የለም። እርሱ ግንም ተራ ሰው ስለሆነ ለሕዝብ

ሽልማት ወይም የዘላለም ቅጣት ሊያድል አይችልም። ባሑላ በኖረበት ጊዜ ሙታን አልተነሡም፣ የዓለም መጨረሻ አልተፈጸመም። ስለዚህ ባሑላ በክርስቶስ ፋንታ አልመጣም። በምሳሌ ነው የተጻፈው የሚሉን እንደሆነም ይሰሳታሉ። ምክንያቱም ኢየሱስና ሐዋርያት ይህንን ትም ሀርት ቃል በቃሉ እንድናምን ነው ያስተማሩን። ማለት ሙታን በእውነት እንደሚነሡ፣ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን፣ እርሱ በዓለም መጨረሻ ለ እያንዳንዱ የሰው ልጆች እንደየሥራቸው እንደሚሰጣቸው (መዝ.62፡ 12፣ ራእይ 21 23)። የጋራ (የመጨረሻ ፍርድ) ከተፈጸመ በኋላ የሰው ልጆች ሁሉ ምድራዊ ሕይወታቸውን ጨርሰው ጻድቃን ወደ መንግሥተ-ሰማይ ሲሄዱ ኃጢአን ደግሞ ወደ ገሃነመ-እሳት እንደሚሄዱ በግልጽ አስተምሮናል (ማቴ.25፡ 46)።

«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ይመጣል» (ማር.8፡ 38)፣ ማለት «ክርስ ቶስ በአባቱ ክብር ፊት ይመጣል» ማለት ነው። በሃዮች ግን ይህንን ቃል ለእነርሱ በሚመቻቸውና ደስ እንዳላቸው ተርጉመው «የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ይመጣል ማለት ክርስቶስ አምላክ በተባለው ባሑላ ተተክቶ ይመጣል ማለት ነው» ኢየሱ የእግዚአብሔርን ቃል ይለውጣሉ። እነዚህን በጭራሽ መቃወም አለብን። በተጨማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ጊዜ የሚመጣው ሊፈርድባቸውና ሊፈርድላቸው ነው እንጂ የሰው ልጆችን ሊያስተምር አይመጣም፣ ምክንያቱም ለድኅነት የሚያስፈ ልገንን ሁሉ በመጀመሪያ መምጣቱ አስተምሮናል። ባሑላ ግን ብዙ ትምህርቶችን ስለጻፈ እርሱ በዓለም ላይ ሊፈርድ የሚመጣ ክርስቶስ አይደለም። ስለዚህ እንዳናምነው እንጠንቀቅ።

የዓለም መጨረሻ

የሰው ልጅ ምድራዊ ሕይወት ካለቀ በኋላ፣ ማለት የጋራ ፍርድ ከተፈጸመ በኋላ፣ ይህ አሁን የምንኖርበት መሬት ምን ይሆናል? አሁን የምናደንቀው ግሩም የሰማይ ጠፈር እንዴት ይሆናል? ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንገነዘበው ይህ ዓለም አላፊ ነው «ሰማይና ምድር ያልፋሉ» (ማቴ.24፡ 35፣ ራእይ 21፡ 1)። ዓለም ያልፋል ማለት ይለወጣል ማለት ነው እንጂ ይጠፋል ማለት አይደለም። ይህንንም ከሚከተሉት ጥቅሶች እንረዳለን፦ «ሰማይና ምድር ያረጃሉ፣ እንደ ልብስ መጐናጸፊያ ትለውጣ ቸዋለህ፣ እነርሱም ይለወጣሉ» (መዝ.102፡ 26)። ይህ ለውጥ በየትኛው መንገድ (በምን ሁኔታ) እንደሚፈጸም አናውቅም። ቅዱስ ጴጥሮስ ሰማ ይና ምድር እንደሚቃጠሉ ትንቢት ተናግሮአል (2ጴጥ.3፡ 10)፣ ቅዱስ

ጳውሎስ ደግሞ ምድራችን እንደምትሻሻል ትንቢት ተናግሮአል። «ፍጥረት ራሱ (ምድራችን) ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥቶ ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር የነፃነትና የክብር ተካፋይ ይሆናል» (ሮሜ 8፡ 21)። የዚህን ምሥጢራዊ ትንቢት ትርጓሜ አናውቅም። ቅዱስ ቶማስ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ (ዶክተር) አስተያየቱን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦ «ምድራችን ስለሚለወጥ እንደ ተነሣው ሥጋችን እርሱም ውብ ይሆናል»። እንዲህ ከሆነ አዲሱ ምድራችን በውበቱ እኛንና ሰማያውያንን ሁሉ ያስደስተናል። ከድሮ በላይ አምላክን እንድናወድስ ያግዘናል (መዝ.100፡ 1)።

ነገር ግን የታደሰው ምድር መኖሪያችን አይሆንም፣ ምክንያቱም ከትንሣኤ በኋላ መርገጫ አያስፈልገንም፣ ግዙፍ ሥጋ የለንምና (1ቆሮ.15፡ 44) እንደ መላእክት እንሆናለን (ማቴ.22፡ 30)። ስለዚህ ጀሆቫውያን በ ምድር ላይ ኢየሱ የሚጠባበቁት ሥጋዊ ብፅዕና ከንቱ ሕልም ነው። የሚድኑት የሰው ልጆች ሁሉ ሰማያውያን ይሆናሉ፣ በዚያን ጊዜ «የሁሉ አምላክ በሁሉ ቦታ ይሆናል» (1ቆሮ.15፡ 28)፣ ጸድቃን በእርሱ ስለሚደሰቱ ሰማይና ምድርን አይለዩም፣ የቦታዎች ርቀት አልቆአልና።

በሙታን ትንሣኤና በዓለም መጨረሻ መካከል የተለያየ ጊዜ የለም፣ ምክንያቱም በጋራ ፍርድ ሁሉም ይታደሳልና (የሐዋ.ሥራ 3፡ 21)፣ ብፁዓን ወደ መንግሥተ-ሰማይ ይገባሉ፣ «ከእንግዲህ ወዲህ አይዘገይም!» (ራእይ 10፡ 6)። ስለዚህ አድቨንቲስት «ከሙታን ትንሣኤ በኋላ ሺህ ዓመት በምድር እንነግሣለን» የሚሉት ቦታ የለውም። ቅዱስ ዮሐንስ በ ራእይ 20፡ 4 የሚናገረውን በምሳሌ እንጂ ቃል በቃሉ ልንቀበለው አይገ ባም። ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ዓይነቱን አሳብ ተቀብላ አታውቅም፣ ኧረ እንዲያውም በመጀመሪያዎቹ ዘመናት ይህንን አሳብ ስለተቃወመች ነው የዮሐንስ ራእይን ዘግይታ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የመዘገበችው። ባለፈው ቅርብ ጊዜ (እ.ኤ.አ. በ1944 ዓ.ም.) አንዳንድ ሰዎች በምድር ሺህ ዓመት ስለመንገሥ፣ የቀድሞዎቹን አስተያየት ስለ አመጡ፣ የቅ ድስት መንበር ኮሚሽን በጥብቅ አወገዘው።

እንግዲህ ከትንሣኤ በኋላ መንግሥተ-ሰማይ የዘላለም አገራችን ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ «ሰማያዊት ከተማ» (ዕብ.11፡ 16) በማለት፣ እንዲሁም «የምትመጣው ከተማ» (ዕብ.13፡ 14)፣ «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር... አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» (ራእይ 21፡ 1-2) በማለት ሰማይን አመለከተ። ቅዱስ ጴጥሮስም «እኛ ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን» (2ጴጥ.3፡ 13) በማለት አዲስ ዓለምን፣ ማለት መንግሥተ-ሰማይን ያመለክታል፣ ምክን

ያቱም ጽድቅ የሚነግሠው በሰማይ ብቻ ነው፣ በዚህ ዓለም እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ስንዴና እንክርዳድ አብሮ ያድጋሉ፣ በመጨረሻው ቀን ብቻ የኃጢአት ምክንያትና ክፉ አድራጊዎች ከእግዚአብሔር መንግሥት ይባረራሉ (ማቴ.13፡ 41)። ቅዱስ ጴጥሮስ የሚታደሰውን ምድር ማለቱም ሊሆን ይችላል፣ ግን ከዓለም መጨረሻ በኋላ ሁሉም ነገር የሰማያውያን ስለሚሆን በሰማይና በምድር መካከል ልዩነት አይኖርም። እግዚአብሔር ወሰን ስለሌለው በሁሉ ቦታ ይታያል፣ በሁሉ ቦታ ሰማያዊ ደስታ ይሆ ናል።

ከሞታችን በኋላ የሚጠብቀን ጽድቅ ከትንሣኤ በኋላ ስለሚጨመር ልን እግዚአብሔር በፍቅሩና በምሕረቱ ያዘጋጀልን ዕድል በጣም ከፍተኛ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና በእመቤታችን ማርያም እርዳታ ወደዚህ የቅድስና ደረጃ ለመድረስ እንበርታ። «የመለኮታዊ ባሕርይው ተካፋዮች እንሆናለን» (2ጴጥ.1፡ 4)፣ «ክርስቶስን እንመስላለን» (1ዮሐ.3፡ 2)። ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን። አሜን።



ተጨማሪ

ምዕራፍ 1

የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ታሪክ

መቅድም

አንዳንድ ጊዜ ብዙ ተማሪዎች በሕዝበ-ክርስቲያን መካከል ልዩነት መኖሩን አይተው፣ በቅሬታ ይህ ልዩነት ለምን ይኖራል? መቼ ተጀመረ? የክርስቲያን ማሕበር አንድ ነው ወይስ ብዙዎች ናቸው? እያሉ ይጠይቃሉ። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሁሉ በፊት ያለፉት ዘመናትን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ እንመለከታለን። ይህ ዕውቀት ቢያንስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ሁሉ ስለ ሁሉም ክርስቲያኖች አንድነት ጸሎት እንድናደርግ ያግዘናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ይህን ታሪክ በሦስት ክፍሎች ከፍለን እንመለከታለን።

1ኛ የመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመኖች ሁኔታ

በሐዋርያት ዘመን የክርስቶስ ተከታዮች «ክርስቲያን» ተብለው ተጠሩ (የሐዋ.ሥራ 11፡ 26)። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ «ካቶሊካውያን» ተባሉ። ምክንያቱም በግሪክ ቋንቋ «ካቶሊክስ» ማለት ዓለም-አቀፋዊ ማለት ነው። የክርስቲያን ሃይማኖት ደግሞ ለሁሉም ሰው ያለ ልዩነት የተመሠረተ ነው። የብሉይ-ኪዳን ሃይማኖት የአንድ ሕዝብ ሃይማኖት ብቻ ነበር። ከዚህ ለመለየት የአዲስ ኪዳን ሃይማኖት ካቶሊክ ተባለ። የክርስቲያን ማኅበር ደግሞ «ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን» ተብላ ተጠራች። ይህ ትምህርት በአበው ጽሑፎች የተለመደ ሆኖ ይኖራል። ለምሳሌ፦ ቅ.ኢግናጽዮስ (ኢ.ኤ.አ. 107 ዓ.ም. የሞተው)፣ ቅ.ፖሊካርፓስ (ኢ.ኤ.አ. በ156 ዓ.ም. የሞተው)፣ ቅ.ኢረነዎስ (ኢ.ኤ.አ. 161 ዓ.ም. የሞተው)፣ ... ወዘተ. ስለ ክርስቲያን ማኅበር ሲጽፉ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ብለው ይጠሩዋት ነበር።

ይህች የክርስቲያን ማሕበር ለረጅም ጊዜ አንድ ነበረች፣ ምክንያቱም ሌላ ማኅበር አልነበረምና። መናፍቃን፣ ማለትም እነ ከሪንቶስ፣ ማኒስ፣

ሰበልዮስ፣ ... ወዘተ. የተባሉት ተነሥተው ከቤተ ክርስቲያን ተለዩ። ነገር ግን ሌላ ማኅበር ሊያቋቁሙ አልቻሉም።

በ4ኛው ክፍለ-ዘመን አርዮስ የተባለ ካህን ተነስቶ በእስክንድርያ ትልቅ ስሕተት አስፋፋ፣ ማለትም «ኢየሱስ የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው እንጂ አምላክ አይደለም» ብሎ አስተማረ። ወዲያውኑ ኢ.ኤ.አ. በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ ተደርጉ «ወልደ አምላክ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ ባሕርይ ነው» የሚል የሃይማኖት ትምህርት ተገለጸ። አርዮስ ደግሞ ተወገዘ። ተከታዮቹም ምንም እንኳን ለረጅም ጊዜ ቢቆዩም ቀስ በቀስ ጠፉ።

በ5ኛው ክፍለ-ዘመን፣ ንስጥሮስ የተባለ የቁስጥንጥንያ አቡን ከተክክለኛው ሃይማኖት ወጣ፣ ማለትም «በክርስቶስ ሁለት አካላት አሉ» ማለትም «የአምላክ ልጅ ሌላ፣ የማርያም ልጅ ደግሞ ሌላ ነውና ማርያም የተራ ሰው እናት ናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም» ብሎ ሰበከ። ይህንን ለመቃወም ኢ.ኤ.አ. በ431 ዓ.ም. የኤፌሶን ጉባኤ ተሰበሰበና «የእግዚአብሔር አብ ልጅና የማርያም ልጅ አንድ ነው፣ በክርስቶስ የሚገኘው የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ በአንድ አካል ስለሚገኝ ክርስቶስ አንድ ነው። የወለደችው ድንግል ማርያምም የአምላክ እናት ናት» የሚለውን ትምህርት ገለጸ። ንስጥሮስም ተወገዘ፣ የቀሩት ተከታዮቹም ጥቂት ስለነበሩ የክርስቲያን ማሕበር (ቤተ ክርስቲያን) አንድነቷን አላጠፋችም።

እንደገና በ5ኛው ክፍለ-ዘመን ሌላ መናፍቅነት ተነሥቶ የሚያሳዝን ትልቅ ጉዳት በቤተ ክርስቲያን ላይ አደረሰ። ነገሩ እንዲህ ነው፦ በቁስጥንጥንያ አውጣኪ የተባለ የገዳም አበምኔት «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ ነው ያለው፣ ምክንያቱም መለኮቱና ሰውነቱ ሲዋሐዱ ሰብአዊ ባሕርይ ስለጠፋ መለኮታዊ ባሕርይ ብቻ አለው» ብሎ አስተማረ። እንደ እርሱ አስተሳሰብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋ አምሳያ፣ ማለትም የማይሠቃይ ሥጋ ነበረው እንጂ እንደ እኛ ሰው አልነበረም። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኛ ሰው ባይሆን ኖሮ ሊሞትልን ባልቻለም ነበር። አውጣኪ ይህንን ስሕተቱን በብዙ አገሮች እስከ ግብጽ ድረስ ስለ አዳረሰ፣ ኢ.ኤ.አ. በ451 ዓ.ም. 630 አቡናት በኬልቂዶን ጉባኤ ተሰብስበውና በርእሰ ሊቃነ-ጳጳሳት በቅዱስ ልዮን ልኡካን ተመርተው እውነተኛውን የክርስቲያን ሃይማኖት ትምህርት እንደሚከተለው አድርገው ገለጹት። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው፣ በመለኮቱ ከአግዚ

አብሔር ጋር አንድ ባሕርይ ነው፣ በሰውነቱ ደግሞ ማለትም በነፍስና በሥጋ በሁሉም ከኃጢአት በቀር ልክ እንደ እኛ ሰው ነው። ከዘለዓለም ጀምሮ ከአግዚአብሔር አብ የተወለደ የአምላክ ልጅ፣ ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ደግሞ ከእመቤታችን ማርያም ሥጋ ለብሶ ተወለደ፣ የሁለቱም አንድ ልጃቸው ነው። ሁለቱ ባሕርይው (የመለኮቱና የሰውነቱ) ሳይቀላቀሉና ሳይደባለቁ፣ ሳይለያዩና ሳይለወጡ በአንድ አካል በሕብረት ይገኛሉ። አንድ ክርስቶስ እንጂ በሁለት አካላት የተከፈለ ክርስቶስ አይደለም።

የአውጣኪ ትምህርት በኬልቄዶን ጉባኤ ተወገዘ፣ የንስጥሮስም በድጋሚ ተወገዘ። አቡነ ዲዮስቆሮስ የእስክንድርያው (የግብጹ) ፓትርያርክ የኬልቄዶንን ጉባኤ ስለተቃወሙ ጉባኤው አወገዛቸው። ይህ ውግዘት የመንበረ እስክንድርያ ሰበካ ሕዝበ-ክርስቲያንን በጣም አሳዘናቸው። በሐዘኑ ምክንያት ሕዝቡ በሁለት ተከፈለ፣ ግማሹ የኬልቄዶን ጉባኤ ደጋፊ ሲሆኑ ግማሹ ደግሞ የጉባኤው ተቃዋሚ ሆኑ። የኬልቄዶን ጉባኤ ተቃዋሚ የሆኑት «ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን» ተብለው እ.ኤ.አ. በ457 ዓ.ም. ልዩ ፓትርያርክ ሾሙ፣ እስከ 642 ዓ.ም. ድረስ ሁለት ፓትርያርክ ጎን ለጎን ሆነው በእስክንድርያ መንበረ-ማርቆስ ይቀመጡ ነበር።

ነገሩን በደንብ ካስተዋልነው ቤተ ክርስቲያንን ለሁለት የሚጎመዳት ምክንያት አልነበረም። ከመስማማት ጉድለት የተነሣ ነው ወደ መለያየት የተደረሰው። ምክንያቱም የኬልቄዶን ጉባኤም ሆነ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንስጥሮስን ስሕተት ለማጥፋት ይፈልጉ ነበር፣ ክርስቶስ አንድ አካል መሆኑንም ያምኑ ነበር።

በግብጽ የአውጣኪ ትምህርት በሁሉም ድጋፍ አግኝቶ ነበር፣ መለያየት ግን ወዲያውኑ አልተከሠተም። የተዋሕዶ ክርስቲያን «አካል»ን ከ«ባሕርይ» ጋር አደባልቀው «በክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ እናምናለን» በማለት «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው» ከሚሉት የኬልቄዶን ውሳኔ ደጋፊዎች ጋር መስማማት ስለ አቃታቸው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስቶስ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ከመስማማት ጉድለት የተነሣ አንድነቷን አጣች።


ከግብጽ ቀጥሎ የተዋሕዶ ሃይማኖት ወደ ሌሎች የእስያ ሀገሮችም፣ ማለትም ወደ ሶርያ፣ ቱርክና አርሜንያ ገባ። በሶርያ የተዋሕዶን ሃይማኖት በደንብ የደገፈውና ያስፋፋው አቡነ ያዕቆብ ባርዳስ የተባለ ስለ ሆነ፣ የተዋሕዶ ክርስቲያኖችም «ያዕቆባውያን» ተባሉ። በግሪክ አገር

ግን ሕዝበ-ክርስቲያኑ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ ስለተቀበሉ ከመንበረ-ጴጥሮስ (ከሮማ) አልተለዩም።

በኢትዮጵያስ? በዚያን ጊዜ በቦታ ርቀት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝበ-ክርስቲያን ከሌሎች ሕዝበ-ክርስቲያን ጋር ሳይገናኙ ይኖሩ ነበር። በዚህም ምክንያት የኬልቄዶን ጉባኤ ወሬና በምድረ-ግብጽ የተደረገው የመለያየት ወሬ በጣም ዘግይቶ ደረሳቸው። አዲስ ሊቀ-ጳጳስ ባስፈለጋቸው ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታት እንደ ልማዳቸው ደብዳቤና ገጸ-በረከትን አስይዘው ልኡካኖቻቸውን ወደ ግብጽ ንጉሥ መላክ ቀጠሉ። የግብጽ ንጉሥ ደግሞ የኬልቄዶን ውሳኔ ደጋፊ ስለነበረ ልኡካኖቹን ተቀብሎ የኬልቄዶን ሃይማኖት ደጋፊ የሆነውን ፓትርያርክ አዲስ ሊቀ-ጳጳስ ያሰጣቸው ነበር።

እ.ኤ.አ. በ642 ዓ.ም. ካሊፋ ዓምር አልዓሶ ክርስቲያን የነበረውን የ ግብጽ መንግሥት አሸንፎ ከሠራዊቱ ጋር በዚያን ጊዜ የግብጽ ዋና ከተ ማ ወደ ነበረው ወደ እስክንድርያ ገባ። ይህ ሰው የኬልቄዶን ሃይማኖት ተከታይ የነበረውን ፓትርያርክ አቡነ ቂሮስን ከሥልጣን አውርዶ ተቃራኒው የነበረውን ፓትርያርክ አቡነ ብንያምን ተቀበለ። ከዚህ ዓመት ጀምረው ነው የኢትዮጵያ ሊቃነ-ጳጳሳት ከተዋሕዶ ፓትርያርክ መላክ የጀመሩት። ይህ መለዋወጥ በኢትዮጵያ ሕዝበ-ክርስቲያን ላይ ወዲያውኑ አዲስ አሳብ አልፈጠረም። ምክንያቱም ግብጻውያን ሊቃነ-ጳጳሳት የኢት ዮጵያን ቋንቋ ስለማያውቁ ተልእኮአቸው ማዕረገ-ዲቁናንና ክህነትን መስጠት (መቀባት) ብቻ ነበር። በተጨማሪም እ.ኤ.አ. ከ850 ዓ.ም. እስ ከ 990 ዓ.ም. አካባቢ ኢትዮጵያ ሊቀ-ጳጳሳት ስላልተሰጣት የግብጻውያን አሳብና ትምህርት ከጥቂት በቀር በኢትዮጵያ አልተዘረጋም። ከዚያ ጊዜ በኋላ ብቻ ማለትም ከ11ኛው ክፍለ-ዘመን በኋላ ብቻ ነው ትምህር ታቸው በሊቀ-ጳጳሳቱ ሳይሆን በአኻዚዎቹ መነኮሳት ቀስ በቀስ በሕዝብ መካከል መስፋፋት የጀመረው። ዳሩ ግን ኢትዮጵያውያን በኬልቄዶን ዘመን በግብጽ ለተደረገው መለያየት ትኩረት አልሰጡትም ወይም አል ተቀበሉትም። ምክንያቱም በንጉሣቸው ተመርተው ልዩነትን ሳያስቡ ከሁሉም የዓለም ክርስቲያኖች ጋር በፍቅርና በሰላም ይኖሩ ነበር። ለምሳሌ፦ በፀሐይ ልብነድንግል ዘመን (እ.ኤ.አ. በ1534 ዓ.ም.) ጸጋዘአብ የተባለው መልእክተኛቸው ወደ ሮም ተልኮ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ «ሕዝባችን የመንበረ-ጴጥሮስ ዘሮሜ ሊቃነ ጳጳሳት የሁሉም መናብርት (ጳጳሳት) ራስ (አለቃ) መሆናቸውን ከጥንት ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ ያምናሉ። በዚህ ምክንያት ዛሬም የመንበረ-ጴጥሮስ ታዛዦች ነን»።

የሆነ ሆኖ ከዚያን ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቦታ ርቀት ምክንያትና በእስላሞች ፅንቅፋት የሮሜን ቤተ ክርስቲያን ረስታ፣ በግብጽ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተመርታና ከእርስዋ ጋር አንድ ሆና ተገኘች። ኢትዮጵያውያን ስለ ኬልቄዶን ጉባኤ በሰሙ ጊዜ መሪዎቻቸውን ተከትለው ጉባኤውን አወገዙት፣ ምክንያቱም የኬልቄዶን ጉባኤ የንስጥሮስን ስሕተት የሚደግፍ መስሎአቸው ነበር። ስለዚህ «በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ እናምናለን» ብለው የተዋሕዶ ሃይማኖትን ጠበቁ እዘ ወተሩም። ዓላማቸው ራሳቸውን ከንስጥሮስ ስሕተት ለመጠበቅ ፈልገው ስለነበር አሳባቸው ትክክለኛ ነው። በሁለት ባሕርይ እናምናለን ለማለት ቢፈልጉ ኖሮ ክርስቶስ በሁለት የተከፈለ (ሁለት አካል ያለው) በመሰ ላቸው ነበር። ስለዚህ የክርስቶስ አንድነት እንዳይጠፋ ፈርተው አንድ ባሕርይ ብቻ እናምናለን ይሉ ነበር።



ኢትዮጵያውያን መዘምራን ወደ እግዚአብሔር ውዳሴ ሲያሳርጉ

ዛሬም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምእመናን እንደ ቀድሞዎቹ አባቶቻቸው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ባሕርይ ብቻ ያምናሉ። ይሁን እንጂ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው» በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ እንዳለው ያምናሉ። በሁለት ባሕርይ ከሚያምኑት ክርስቲያኖች የሚለያቸው ነገር የለም፣ ምክንያቱም ልዩነታ ቸው የቃል ወይም የአነጋገር ወይም የአገላለጽ ነው እንጂ የእምነት አይ ደለም። በተጨማሪም በአንዳንድ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ በግልጽ ተጠቅሶ ስለሚገኝ እነዚህን መጻሕፍት የጻፉዋቸው የተመሰገኑ ሊቃውንት የመስማማትን መንገድ ያቀርቡልናል (ይከፍቱልናል)። አንዳንድ ጥቅሶችን እንመልከት፡-

> <u>በሃይማኖተ-አበው</u> መጽሐፍ «የቃል (የወልድ) ባሕርይ ወደ የሰው ባሕርይ አልተለወጠም፣ እንዲሁም የሰው ባሕርይ ወደ የቃል ባሕርይ አለተለወጠም፣ ነገር ግን ሁለቱም ሳይለወጡ በ የራሳቸው ይኖራሉ»።
> <u>በሲንክሳር</u> ደግሞ «ቃል ወደ ሥጋ አልተለወጠም፣ ሥጋም ወደ መለኮት አልተለወጠም፣ ሁለቱም በየራሳቸው ባሕርይ ይቆያሉ።»

በ<u>«አርጋኖነ ማርያም ድንግል»</u> መጽሐፍ፡- «ጌታ (ክርስቶስ) ሆይ! አንተ በሀላዌህ የእግዚአብሔር አብ የበኩር ልጅ ነህ፣ በሥጋዌህ ደግሞ የማርያም የበኩር ልጅ ስለሆንህ፣ በመለኮት የአብ ልጅ በሰውነት ደግሞ የሰው ልጅ መሆንህን አምናለሁ»።

<u>በመጽሐፈ-ቅዳሴ</u>፡- «ይህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም፣ ቅድስትና ንጽሕት ከሆነችው የአምላክ እናትና እናታችን ድንግል ማርያም የወሰደው፣ ያለመቀላቀልና ያለ መደባለቅ፣ ያለ መለያየትና ያለ መለወጥ ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገው»። ይህ መግለጫ በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ከተደረገው ትምህርት ጋር በጣም ይስማማል። ይህ የእምነት ሥራ ዛሬ በመላዋ ኢትዮጵያ፣ በሁሉም መሥዋዕተ-ቅዳሴ፣ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶና በካቶሊክ ካህናት ያለ ምንም ልዩነት ይደገማል።

እንግዲህ በምሥጢረ-ሥጋዌ ላይ ተዋሕዶና ካቶሊክ ልዩነት የላቸውም፣ ሃይማኖታቸው አንድ ናት። ምክንያቱም ሁላችንም «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው» ብለን እናምናለን። እስከ ዛሬ ድረስ አንድነታችንን የሚከለክለን በቃላት ያለ መረዳዳታችን (ያለመስማማታችን) ብቻ ነው።

ዛሬ እኛን የሚለያየን ዋና ነገር አንድ መሪ ማጣታችን ነው። በ መጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት የክርስቶስ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) አንድ ነበረች፣ ምክንያቱም ይመራት የነበረው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አንድ ብቻ ነበርና። ዛሬ ግን የተለያዩ አብያተ-ክርስቲያናት የየራሳቸው መሪ አላቸው። የተዋሕዶ ክርስቲያኖችም በአምስት ክፍሎች ተከፋፍለዋል፣ (ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶርያ፣ አርሜንያና ህንድ) ናቸው። አምስቱም በየራሳ ቸው መሪዎች የሚተዳደሩ ናቸው። ይህ መለያየት እኛን የክርስቶስ ተከ ታዮችን በጣም ያሳዝነናል፣ ምክንያቱም ተለያይተን ሳለን ለጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በትክክል አንመሰክርለትም፣ በአርኢያችንም የዓለምን ሕዝብ አናንጽም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችንም በአንድነት እንድንኖር ይፈልጋል፣ ስለ አንድነታችንም ጸሎት አድርጎልናል (ዮሐ.17፡ 21)። ክር ስቲያኖች በሙሉ አንድ ማኅበር ሆነውና በወንድማማችነት ፍቅር ተሳስ ረው፣ በመንበረ-ጴጥሮስ ተመርተው «አንድ መንጋ በአንድ እረኛ ሥር እንዲሆኑ» እንጸልይ (ዮሐ.10፡ 16)።



እ.ኤ.አ. ሰኔ 23 ቀን 1984 ዓ.ም. ር.ሊ.ጳጳሳት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊና የሶርያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ኢግናጽዮስ ተገናኝተው «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም እምላክና ፍጹም ሰው፣ በመለኮቱ የአብ ልጅ በሰውነቱ የማርያም ልጅ መሆኑን፣ መለኮቱና ሰውነቱ ደግሞ ያለ መቀ ላቀልና ያለ መደባለቅ፣ ያለ መለያየትና ያለ መለወጥ በአንነት ተዋሕደው እንደሚሠሩ እናምናለን» በማለት የኬልቄዶንን ውሳኔ ተቀብለው በመፈራረም የእምነታቸውን አንድነት ገለጹ


2ኛ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መለያየት

የተዋሕዶ ክርስቲያን ከሮማ ሲለዩ፣ ግሪካውያን እንደ ሌሎቹ የ ኤውሮፓ አገሮች በካቶሊካዊ ሃይማኖት ለረጅም ጊዜ ስለቀጠሉ ለሮማዊ ጳጳስ ታማኞች ሆነው ተገኙ። ግሪካውያን ስለ እውነተኛው ሃይማኖት ችግር አልነበራቸውም፣ ምክንያቱም የኬልቆዶንን ጉባኤ ውሳኔ ተቀብለው ነበር። ነገር ግን ቀስ በቀስ በምሥራቅ አውሮፓ የሃይማኖት ሳይሆን የቅ ንዓት ፈተና ተነሣ፣ ማለትም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፖለ ቲካዊ አስተሳሰብ ተገፋፍተው «[redacted]» በማለት ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ፈለጉ።

እ.ኤ.አ. በ879 ዓ.ም. ፎጽዮስ የተባለ ይህንን መለያየት ተግባራዊ ለማድረግ ሞከረ። ነገሩ ስለ አልተሳካለት በዚያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አንድነት አልተጐዳም። ከእርሱ በኋላ ግን እ.ኤ.አ. በ1054 ዓ.ም. ፓትር ያርክ ሚካኤል ቀሩላርዮስ የተባለ ይህንን ድፍረት ስለ ደገመ እስክ መለያየት አደረሰው። ይህ ፓትርያርክ ያለ ብቁ ምክንያት አንዳንድ የ ምዕራባውያንን ልማድ ጥሶ፣ በእውነት ሰሮማዊ ጳጳስ ሊታዘዝ ስላልፈ ለገ፣ ራሱን ከሮማዊ ጳጳስ ጋር እኩል አድርጎ እርሱ ራሱ ማዘዝና መ ወሰን ጀመረ። የሮማዊ ጳጳስ ልኡካን ወደ ቁስጥንጥንያ ሄደው ከሚካኤል ጋር ስምምነት ለማድረግ ሞክረው ነበር። ነገር ግን እርሱ ስለተቃወ ማቸው በመጨረሻ አወገዙት። ሚካኤል የር.ሊ.ጳጳሳትን ደብዳቤ ወደ እሳት ወርውሮ ሕዝቡን በሙሉ ይዞ ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተለ ይቶ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ። ይህች ቤተ ክርስቲያን ለሮማዊ ጳጳስ አለመታዘዝዋ ብቻ ነው እንጂ ሃይማኖትዋ ትክክለኛ ስለሆነ «ኦርቶዶክስ» ተብላለች። (ኦርቶስ=ሐቀኛ፣ ዶክሳ=አሳብ)።

ሚካኤል ቀሩላርዮስ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ስለ አፈረሰ የጌታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስን መንጋ በጣም ጐዳ። ቀስ በቀስ በሁሉም ምሥ ራቃዊ አገሮች (በግሪክ፣ በባልግሪ፣ በሰርብያ፣ በሩሜንያ፣ በራሽያ፣... ወ.ዘ.ተ.) የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በማወቅና ባለማወቅ ስለተለዩ የጴጥሮስ ወራሽነታቸውን አጡ። ይህ ትልቅ መከራ ሆነባቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌላ መከራም አጋጠማቸው፣ ማለትም መሪያቸው ለመሆን ፈልጎ የነበረው ፓትርያርክ ጠፋባቸው። ምክንያቱም እ.ኤ.አ. በ1453

ዛሬ እኛን የሚለያየን ዋና ነገር አንድ መሪ ማጣታችን ነው። በ መጀመሪያዎቹ የክርስትና ዘመናት የክርስቶስ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) አንድ ነበረች፣ ምክንያቱም ይመራት የነበረው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አንድ ብቻ ነበርና። ዛሬ ግን የተለያዩ አብያተ-ክርስቲያናት የየራሳቸው መሪ አላቸው። የተዋሕዶ ክርስቲያኖችም በአምስት ክፍሎች ተከፋፍለዋል፣ (ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶርያ፣ አርሜንያና ህንድ) ናቸው። አምስቱም በየራሳ ቸው መሪዎች የሚተዳደሩ ናቸው። ይህ መለያየት እኛን የክርስቶስ ተከ ታዮችን በጣም ያሳዝነናል፣ ምክንያቱም ተለያይተን ሳለን ለጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በትክክል አንመሰክርለትም፣ በአርአያችንም የዓለምን ሕዝብ አናንጽም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችንም በአንድነት እንድንኖር ይፈልጋል፣ ስለ አንድነታችንም ጸሎት አድርጎልናል (ዮሐ.17፡ 21)። ክር ስቲያኖች በሙሉ አንድ ማኅበር ሆነውና በወንድማማችነት ፍቅር ተባብ ረው፣ በመንበረ-ጴጥሮስ ተመርተው «አንድ መንጋ በአንድ እረኛ ሥር እንዲሆኑ» እንጸልይ (ዮሐ.10፡ 16)።



እ.ኤ.አ. ሰኔ 23 ቀን 1984 ዓ.ም. ር.ሊ.ጳጳሳት ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊና የሶርያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ኢግናጽዮስ ተገናኝተው «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው፣ በመለኮቱ የአብ ልጅ በሰውነቱ የማርያም ልጅ መሆኑን፣ መለኮቱና ሰውነቱ ደግሞ ያለ መቀ ላቀልና ያለ መደባለቅ፣ ያለ መለያየትና ያለ መለወጥ በአውነት ተዋሕደው እንደሚሠሩ እናምናለን» በማለት የኬልቄዶንን ውሳኔ ተቀብለው በመፈራረም የእምነታቸውን አንድነት ገለጹ

2ኛ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መለያየት

የተዋሕዶ ክርስቲያን ክሮማ ሲለዩ፣ ግሪካውያን እንደ ሌሎቹ የ ኤውሮፓ አገሮች በካቶሊካዊ ሃይማኖት ለረጅም ጊዜ ስለቀጠሉ ለሮማዊ ጳጳስ ታማኞች ሆነው ተገኙ። ግሪካውያን ስለ እውነተኛው ሃይማኖት ችግር አልነበራቸውም፣ ምክንያቱም የኬልቆዶንን ጉባኤ ውሳኔ ተቀብለው ነበር። ነገር ግን ቀስ በቀስ በምሥራቅ አውሮፓ የሃይማኖት ሳይሆን የቅ ንዓት ፈተና ተነሣ፣ ማለትም አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፖለ ቲካዊ አስተሳሰብ ተገፋፍተው «ቁስጥንጥንያ የምሥራቃዊ መንግሥት ርእሰ-ከተማ ስለሆነች በምዕራባዊው መንግሥት ከምትገኘው የሮማ ከተማ ጋር እኩል ናትና በማዕረግ እኩል የሆነ ጳጳስ ያስፈልጋታል። ስለዚህ የቁስጥንጥንያ ጳጳስ ለሮማ ጳጳስ ሊታዘዝ አይገባውም፣ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አለበት» በማለት ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ፈለጉ።

እ.ኤ.አ. በ879 ዓ.ም. ፎጽዮስ የተባለ ይህንን መለያየት ተግባራዊ ለማድረግ ሞከረ። ነገሩ ስለ አልተሳካለት በዚያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አንድነት አልተጐዳም። ከእርሱ በኋላ ግን እ.ኤ.አ. በ1054 ዓ.ም. ፓትር ያርክ ሚካኤል ቀሩላርዮስ የተባለ ይህንን ድፍረት ስለ ደገመ እስከ መለያየት አደረሰው። ይህ ፓትርያርክ ያለ ብቁ ምክንያት አንዳንድ የ ምዕራባውያንን ልማድ ጥሶ፣ በእውነት ለሮማዊ ጳጳስ ሊታዘዝ ስላልፈ ለገ፣ ራሱን ከሮማዊ ጳጳስ ጋር እኩል አድርጎ እርሱ ራሱ ማዘዝና መ ወሰን ጀመረ። የሮማዊ ጳጳስ ልኡካን ወደ ቁስጥንጥንያ ሄደው ከሚካኤል ጋር ስምምነት ለማድረግ ሞክረው ነበር። ነገር ግን እርሱ ስለተቃወ ማቸው በመጨረሻ አወገዙት። ሚካኤል የር.ሊ.ጳጳሳትን ደብዳቤ ወደ እሳት ወርውሮ ሕዝቡን በሙሉ ይዞ ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተለ ይቶ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ። ይህች ቤተ ክርስቲያን ለሮማዊ ጳጳስ አለመታዘዝዋ ብቻ ነው እንጂ ሃይማኖትዋ ትክክለኛ ስለሆነ «ኦርቶዶክስ» ተብላለች። (ኦርቶስ=ሐቀኛ፣ ዶክሳ=አሳብ)።


ሚካኤል ቀሩላርዮስ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ስለ አፈረሰ የጌታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስን መንጋ በጣም ጐዳ። ቀስ በቀስ በሁሉም ምሥ ራቃዊ አገሮች (በግሪክ፣ በባልግሪ፣ በሰርብያ፣ በሩሜንያ፣ በራሽያ፣... ወ.ዘ.ተ.) የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በማወቅና ባለማወቅ ስለተለዩ የጴጥሮስ ወራሽነታቸውን አጡ። ይህ ትልቅ መከራ ሆነባቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌላ መከራም አጋጠማቸው፣ ማለትም መሪያቸው ለመሆን ፈልጎ የነበረው ፓትርያርክ ጠፋባቸው። ምክንያቱም እ.ኤ.አ. በ1453

ዓ.ም. እስላሞች ቁስጥንጥንያን ወርረው የፓትርያርክን ነፃነት አጥፍተው ነበር።

እስላሞች ሌሎች አገሮችንም ይዘው ሕዝበ-ክርስቲያንን ገዙ፣ ባል ተገዙት አገሮች ደግሞ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊት ሆነችና በመንግሥት መመራት ጀመረች። ይህ መለያየት በየጊዜው እየበዛ ስለ ሄደ ዛሬ በምሥራቅ ኤውሮፓ የሚገኙት ኦርቶዶክሳውያን በ14 ማኅበራት (አብያተ ክርስቲያናት) ተከፋፍለው ይገኛሉ። ሁሉም የየራሳቸው መሪ አላቸው። ምንም እንኳን በራሳቸው የሚተዳደሩ ቢሆኑም ከመንግሥት ነፃ አይደሉም። በእውነቱ ይህ መለያየት ክርስቶስ ከወሰነልን አንድነት ጋር ተቃራኒ ነው። በቁስጥንጥንያ ያሉት ፓትርያርክ የአንድ ትንሽ አካ ባቢ እንጂ የሁሉም ኦርቶዶክሳውያን አለቃ አይደሉም። ኧረ እንዲያውም ከቱርክ ቁጥጥር ሥር ስለሆነ ችግርና መከራ እያጋጠማቸው ነው።

ከረጅም ጊዜ መጠባበቅ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1964 ዓ.ም. የሮማ ጳጳስ ጳውሎስ ፮ኛ ከፓትርያርክ አተናጐራስ ጋር ተገናኙ። እንደገና እ.ኤ.አ. በ1979 ዓ.ም. እኚህ ዛሬ ያሉት የሮማ ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ ዛሬ ካሉት ፓትርያርክ ዲመጥሮስ ጋር ተገናኙ። ያ የጥንቱ ውግዘት ተደመሰሰ። ስለዚህ በሁለቱም ወገን መልካም ፍላጐት ከተገኘ ካቶሊክና ኦርቶዶክስ እንደ ጥንቱ አንድ እንደሚሆኑ ተስፋ አለን።

ፓትርያርክ አተናጐራስ የሮማ ጳጳስ ወደ ኦርሳቸው እንደሚመጡ በሰሙ ጊዜ በጣም ተደስተው የሚከተለውን የአንድነት ፍላጐታቸውን ገለጹ፡- «እኛ ኦርቶዶክሳውያን ከካቶሊክ ጋር አንድነት ለማግኘት እንጠባ በቃለን፣ እስከ አሁን ያሳለፍነው የብቸኝነት ኑሮ አላስደሰተንም፣ ካቶሊክና ኦርቶዶክስ አንድ የሚያደርጋቸው ብዙ ነገር አላቸው፡- ለምሳሌ፡- አንድ ትምህርተ ክርስቶስ፣ ሰባቱ ምሥጢራት፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት! በተለይም ደግሞ የሰማዕታት አርአያ። ሰማዕታቶቻችን ደማቸውን ያፈ ሰሱት ለአንዲት ሃይማኖት ብለው ስለሆነ ዛሬ እኛን ይገስጹናል። «እኛ ለአንዲት ሃይማኖት ስንሠዋ እናንተ ለምን ተለያያችሁ?» ይሉናል። እንግዲህ እኛ እንደገና አንድ ማኅበር ለመሆን እንፈልጋለን። አሁን ከ ሮማዊ ጳጳስ ጋር ተገናኝተን ዓይን ለዓይን መተያየትና ልብ ለልብ መገላለጽ ምንኛ የሚያስደስት ይሆናል! ይህችን ቀን በከፍተኛ ምኞት እጠባበቃለሁ»። እኛም በክርስቲያኖች መለያየት አዝነናል። ይህን ሁሉ ጉዳት ስለ ተመለከትን ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነት እንመኛለን፣ እን ለምናለንም።



የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ አተናጎራስ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ ጋር ሲገናኙ

3ኛ የወንድሞቻችን የፕሮቴስታንቶች መለያየት

ኦርቶዶክሳውያን ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከተለዩ በኋላ የምዕራ ባዊ ኤውሮጳ ሕዝበ-ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ በአንድነት መኖራቸውን ቀጠሉ፣ ኧረ እንዲያውም ወደ ሌሎች አገሮች ብዙ ሰባክያንን ላኩ። ከ ጥቂት ዘመናት በኋላ ግን አንዳንድ መናፍቃን፡- እነ ዊክልፍና ሑስ

ተነሥተው የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ የሆነውን የስሕተት ትምህርት አስፋፉ።

ከሁሉም መናፍቃን በጣም የታወቀው ማርቲን ሉተር ነው። ይህ ው በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በጀርመን አገር ገዳማዊ ካህን ነበረ። በዚሁ ዘመን ገዳሙን ትቶ መሐላውን አፍርሶ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መሰ ለው (ደስ እንዳለው) በመተርጐም በቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ ብዙ የስ ሕተት ትምህርቶችን አስፋፉ። ለምሳሌ፦ «እምነት እንጂ መልካም ተግ ባር ጸሎትና ጾምም አይጠቅሙንም፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ከንቱ ነው፣ ሰባት ምሥጢራት የሉም፣ ሥርየተ ኃጢአት የለም፣ ንስሐ ቦታ የለም፣ የጳጳስ ሥልጣን የለም፣ አቡናትና ካህናት አያስፈልጉም፣ መነኮሳንና ደናግል አንፈልግም፤ ሁ[redacted]ው [redacted] በማለት እውነተኛውን ሃይማኖት አጠፉ።

ሉተር ኤ.ኤ. በ1517 ዓ.ም. ተከሰሰ፣ እንዲታረም በማለት ከርእሰ-ሊቃነ ጳጳሳት ልኡካን ደብዳቤ ሊያደርሱለት ሄዱ። ሉተር ግን የጳጳሱን ደብዳቤ በእሳት ውስጥ ጥሎ ጳጳሱንም በመስደብ አሻፈረኝ አልታረምም አለ። በዚህ ምክንያት ኤ.ኤ.ኤ. በ1521 ዓ.ም. ተወገዘ። ሉተር ከመጻጸት ፈንታ ብዙ ተከታዮችን ሰብስቦ የጀርመን መሳፍንትን በጳጳሱና በካቶሊካውያን ነገሥታት ላይ አስነሣ። እነሱም ጦርነት ከፍተው ካቶሊካውያን አብያተ-ክርስቲያናትንና ገዳማትን ዘርፈው፣ አቡናትን ከሥልጣናቸው በማውረድና በመግደል የካቶሊክ ሃይማኖት እንዳበቃላት ቆጥረው፣ ካህናት የሌላት ሉተራዊት ሃይማኖት በእነርሱ ሥልጣን ስር እንደተጀ መረች ገለጹ። ኤ.ኤ.ኤ. በ1525 ዓ.ም. የሉተር ተከታዮች ፕሮቴስታንት ተብለው ተጠሩ።

ይህ ሉተር የጀመረው ብጥብጥ ከጀርመን ወደ ስዊድን ስለ ተሻገረ፣ በስዊድን የነበረው ንጉሥ የሃይማኖት መሪ ሆኖ ካቶሊካውያንን አሳደዳ ቸው፣ አጠፋቸውም። እንዲሁም ኤ.ኤ.ኤ. በ1536 ዓ.ም. የዴንማርክ፣ የኖርወይና የአይስላንድ ንጉሥ ይህንን ሃይማኖት ተቀብሎ ሕዝቡ በ ሙሉ ፕሮቴስታንት እንዲሆኑ አደረገ።

በስዊዘርላንድ ደግሞ ኤ.ኤ.ኤ. በ1522 ዓ.ም. የሉተርን ሃይማኖት የሚመስል ሃይማኖት የሰበከው ካህን [redacted] ተከታዮቹ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ንብረት ለመዘረፍ ጦርነት ከፈቱ። ዝዊንግሊ በ1531 ዓ.ም. በጦርነቱ ላይ ስለሞተ፣ በእርሱ ቦታ ለመተካት [redacted] ፈረንሣይ አገር መጥቶ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ። ካል

ቪን ከፕሮቴስታንት መሪዎች በጣም ጨካኝ ስለነበረ፣ እርሱን የማይከተሉ ትን ያሰቃያቸውና ያስገድላቸውም ነበር።

በዚያን ጊዜ በእንግሊዝ አገር የነበረው ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ ካቶሊክና መንፈሳዊ ስለነበረ የሉተርን ትምህርትና መጻሕፍት ነቀፈ፣ አጠፋም። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በፍትወተ-ሥጋ ስለተሸነፈ ሁለተኛ ሚስት ለማግባት ፈልጐ፣ ሮማዊ ጳጳስ ስላልፈቀዱለት በጣም ተቆጥቶ ከካቶሊካ ዊት ቤተ ክርስቲያን በመለየት፣ ኤ.ኤ.ኤ. በ1534 ዓ.ም. የእንግዲዝ አገ ር ቤተ ክርስቲያንን በሥልጣኑ ሥር አደረጋት። ያልተከተሉትን ስለ አስገደላቸው ብዙ አቡናት፣ ካህናትና ሕዝብ በሰማዕትነት ሞቱ። በዚሁ ጊዜ [redacted] እንደ [redacted]። ነገር ግን ካህናት ስለ አሉዋት ከፕሮቴስታንት ይልቅ አርቶዶክስን ትመስላለች።

የፕሮቴስታንት ትምህርት በ1545 ዓ.ም. በትሬንቶ ጉባኤ ስለ ተወገዘ ስሕተቱ ጋብ አለ፣ ቀስ በቀስ ግን መስፋፋቱን አላቋረጠም። በመሆኑም ወደ ሆላንድ፣ ከዚያም ወደ ፊንላንድ፣ እንዲሁም ወደ አስትርያና ሃን ገሪ ስለገባ በሰሜናዊ ኤውሮጳ ግማሹ ሕዝብ ካቶሊክ፣ ግማሹ ደግሞ ፕሮቴስታንት ሆነ። ፕሮቴስታንትም ሁለት ዓይነት ነበሩ፦ ሉተራውያንና ካልቪንስት ነበሩ። ቀስ በቀስ ሌሎች ማኅበራትም ተመሠረቱ። [redacted] ቲስት፣ [redacted] በፊ[redacted]። በእንግሊዝ አገርም በአንግሊካውያን ላይ ሌሎች ማኅበራት፦ ማለትም ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕረስቢተርያን፣ ኳይከር፣ ... ወ.ዘ.ተ. የተባሉት ማኅበራት ተ[redacted]መሩ። ስለዚህ በመካከላቸውም አንድነት ጠፋ።

አሜሪካ ከተገኘች በኋላ ይህ መለያየት እየበዛ ሄደ፣ ምክንያቱም ፕሮቴስታንቶች ከሁሉም የኤውሮጳ ማኅበራት ተውጣጥተው ወደ አሜሪካ በመሻገር ስብከታቸውን ቀጠሉ። በተባበሩት መንግሥታት የሚገ ኙት [redacted]። በእነርሱ ላይ ግን ሌሎች አዲስ ማኅበራትም ተመሠረቱ። እነርሱም፦ ባፕቲስት (ሌላ ዓይነት)፣ ሞርሞን፣ አድቨንቲስት፣ ... ወ.ዘ.ተ. የሚባሉ ናቸው። ጴንጤቈስጣል ከባ ፕቲስት ተለዩ። ከአድቨንቲስት ደግሞ ኤ.ኤ.ኤ. በ1879 ዓ.ም. የጀሆቫውያን መሥራች ተለየ።

በአፍሪካም በባዕዳውያን ገዥዎች ጊዜ፣ በተለይም ባለፈው ዘመን ውስጥ ፕሮቴስታንቶች ተስፋፉ። ብዙ በኤውሮፓና በአሜሪካ ያሉት

ተነሥተው የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ የሆነውን የስሕተት ትምህርት አስፋፉ።

ከሁሉም መናፍቃን በጣም የታወቀው ማርቲን ሉተር ነው። ይህ ሰው በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በጀርመን አገር ገዳማዊ ካህን ነበረ። በዚሁ ዘመን ገዳሙን ትቶ መሐላውን አፍርሶ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መሰለው (ደስ እንዳለው) በመተርጐም በቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ ብዙ የስሕተት ትምህርቶችን አስፋፋ። ለምሳሌ፦ «እምነት እንጂ መልካም ተግባር ጸሎትና ጾምም አይጠቅሙንም፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ከንቱ ነው፣ ሰባት ምሥጢራት የሉም፣ ሥርየተ ኃጢአት የለም፣ ንስሐ ቦታ የለም፣ የጳጳስ ሥልጣን የለም፣ አቡናትና ካህናት አያስፈልጉም፣ መነኮሳንና ደናግል አንፈልግም፤ ሁሉም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ራሱ ሊተረጕመው ይችላል» በማለት እውነተኛውን ሃይማኖት አጠፋ።

ሉተር እ.ኤ.አ. በ1517 ዓ.ም. ተከስሶ፣ እንዲታረም በማለት ከርእሰ-ሊቃነ ጳጳሳት ልኡካን ደብዳቤ ሊያደርሱለት ሄዱ። ሉተር ግን የጳጳሱን ደብዳቤ በእሳት ውስጥ ጥሎ ጳጳሱንም በመስደብ አሻፈረኝ አልታረምም አለ። በዚህ ምክንያት እ.ኤ.አ. በ1521 ዓ.ም. ተወገዘ። ሉተር ከመጻጸት ፈንታ ብዙ ተከታዮችን ሰብስቦ የጀርመን መሳፍንትን በጳጳሱና በካቶሊካውያን ነገሥታት ላይ አስነሣ። እነሱም ጦርነት ከፍተው ካቶሊካውያን አብያተ-ክርስቲያናትንና ገዳማትን ዘርፈው፣ አቡናትን ከሥልጣናቸው በማውረድና በመግደል የካቶሊክ ሃይማኖት እንዳበቃላት ቆጥረው፣ ካህናት የሌላት ሉተራዊት ሃይማኖት በእነርሱ ሥልጣን ስር እንደተጀመረች ገለጹ። እ.ኤ.አ. በ1525 ዓ.ም. የሉተር ተከታዮች ፕሮቴስታንት ተብለው ተጠሩ።

ይህ ሉተር የጀመረው ብጥብጥ ከጀርመን ወደ ስዊድን ስለ ተሻገረ፣ በስዊድን የነበረው ንጉሥ የሃይማኖት መሪ ሆኖ ካቶሊካውያንን አሳደዳቸው፣ አጠፋቸውም። እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1536 ዓ.ም. የዴንማርክ፣ የኖርወይና የአይስላንድ ንጉሥ ይህንን ሃይማኖት ተቀብሎ ሕዝቡ በሙሉ ፕሮቴስታንት እንዲሆኑ አደረገ።

በስዊዘርላንድ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1522 ዓ.ም. የሉተርን ሃይማኖት የሚመስል ሃይማኖት የሰበከው ካህን ዝዊንግሊ ይባላል። ተከታዮቹ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ጉብረት ለመዝረፍ ጦርነት ከፈቱ። ዝዊንግሊ በ1531 ዓ.ም. በጦርነቱ ላይ ስለሞተ፣ በእርሱ ቦታ ለመተካት ካልቪን ከ ፈረንሣይ አገር መጥቶ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ። ካል

ቪን ከፕሮቴስታንት መሪዎች በጣም ጨካኝ ስለነበረ፣ እርሱን የማይከተሉትን ያሰቃያቸውና ያስገድላቸውም ነበር።

በዚያን ጊዜ በእንግሊዝ አገር የነበረው ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ ካቶሊክና መንፈሳዊ ስለነበረ የሉተርን ትምህርትና መጻሕፍት ነቀፈ፣ አጠፋም። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በፍትወተ-ሥጋ ስለተሸነፈ ሁለተኛ ሚስት ለማግባት ፈልጐ፣ ሮማዊ ጳጳስ ስላልፈቀዱለት በጣም ተቆጥቶ ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በመለየት፣ እ.ኤ.አ. በ1534 ዓ.ም. የእንግሊዝ አገር ቤተ ክርስቲያንን በሥልጣኑ ሥር አደረጋት። ያልተከተሉትን ስለ አስገደላቸው ብዙ አቡናት፣ ካህናትና ሕዝብ በሰማዕትነት ሞቱ። በዚሁ ጊዜ አንግሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በእንግሊዝ አገር ተጀመረች፣ እርስዋም እንደ ፕሮቴስታንት ትቆጠራለች። ነገር ግን ካህናት ስለ አሉዋት ከፕሮቴስታንት ይልቅ ኦርቶዶክስን ትመስላለች።

የፕሮቴስታንት ትምህርት በ1545 ዓ.ም. በትሬንቶ ጉባኤ ስለ ተወገዘ ስሕተቱ ጋብ አለ፣ ቀስ በቀስ ግን መስፋፋቱን አላቋረጠም። በመሆኑም ወደ ሆላንድ፣ ከዚያም ወደ ፊንላንድ፣ እንዲሁም ወደ ኦስትርያና ሃንገሪ ስለገባ በሰሜናዊ ኤውሮጳ ግማሹ ሕዝብ ካቶሊክ፣ ግማሹ ደግሞ ፕሮቴስታንት ሆነ። ፕሮቴስታንትም ሁለት ዓይነት ነበሩ፦ ሉተራውያንና ካልቪንስት ነበሩ። ቀስ በቀስ ሌሎች ማኅበራትም ተመሠረቱ። አናባፕቲስት፣ መኖናይት እና ሞራቭያንስ የሚባሉ ደግሞ አስቀድሞ ከሉተር በፊት ነበሩ። በእንግሊዝ አገርም በእንግሊካውያን ላይ ሌሎች ማኅበራት፦ ማለትም ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕረስቢተርያን፣ ኪይካርስ፣... ወ.ዘ.ተ. የተባሉት ማኅበራት ተመሠረቱ። ስለዚህ በመካከላቸውም አንድነት ጠፋ።

አሜሪካ ከተገኘች በኋላ ይህ መለያየት እየበዛ ሄደ፣ ምክንያቱም ፕሮቴስታንቶች ከሁሉም የኤውሮጳ ማኅበራት ተውጣጥተው ወደ አሜሪካ በመሻገር ስብከታቸውን ቀጠሉ። በተባበሩት መንግሥታት የሚገኙት አንግሊካውያን ኤጲስቆጳልያን ተባሉ። በእነርሱ ላይ ግን ሌሎች አዲስ ማኅበራትም ተመሠረቱ። እነርሱም፦ ባፕቲስት (ሌላ ዓይነት)፣ ሞርሞን፣ አድቨንቲስት፣... ወ.ዘ.ተ. የሚባሉ ናቸው። ጴንጤቈስታል ከባፕቲስት ተለዩ። ከአድቨንቲስት ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1879 ዓ.ም. የጀሆቫውያን መሥራች ተለየ።

በአፍሪካም በባዕዳውያን ገዥዎች ጊዜ፣ በተለይም ባለፈው ዘመን ውስጥ ፕሮቴስታንቶች ተስፋፉ። ብዙ በኤውሮፓና በአሜሪካ ያሉት

ማኅበራት ወደ አፍሪካ ተሻገሩ። በተጨማሪም አፍሪካውያን ራሳቸው አዲስ ማኅበራትን መሠረቱ። ስማቸውም የተለያየ ነው። ለምሳሌ፦ የ ክርስቶስ ማሕበር፣ የክርስቶስ ስብሰባ፣ የብርሃን ልጆች... ወ.ዘ.ተ.። እነ ዚህን የመሳሰሉት ብቻቸውን በራሳቸው የሚተዳደሩ ትናንሽ ማኅበ ራት በአፍሪካ ውስጥ በጣም ብዙ ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚበዙት ፕሮቴስታንት ሉተራውያን ናቸው። በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ ወንጌ ላዊት ቤተ ክርስቲያን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ መካነ ኢየሱስ ይበዛሉ።

የትምህርታችን መነሻ ምክንያት ሃይማኖትን መቁጠር አይደለም፣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መመለስ ነው እንጂ። ይህ ከላይ የተመለከት ነው ሁኔታ ሁሉ የክርስቶስ መንጋ ያለመጠን መከፋፈሉን ያስረዳናል። ይህ በጣም ጭፍና መጥፎ አርአያ የሚሰጥ ነገር ነው። አንዳንድ ጉረቤ ቶቻችን «ክርስትና አይጠቅምም፣ ክርስትና ተበላሽቶአል፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ለተከታዮቹ የወሰነላቸው አንድነት ጠፍቶአል» ሲሉ ሰምቻለሁ። በጣም ያሳዝናል። ያለ አንድነት ለክርስቶስ ልንመሰክርለት አንችልም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ የምለምነው ሁሉም አንድ እንዲሆኑ ነው፣ እንዲሁም አባት ሆይ! አንተ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ አን ዳለሁ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው» (ዮሐ.17፡ 21) በማለት ያደረገው ጸሎት እንዲፈጸምልንና የአንድነት መልካም ፍላጐት እንዲሰጠን፣ በተለይም ለአብያተ-ክርስቲያናት መሪዎች ብርሃኑን እንዲያበራላቸው ጸሎት እናድርግ።

በአሁኑ ጊዜ ሁላችንም የክርስቶስ ተከታዮች እርስበርሳችን ተወዳ ጅተን እንከባበራለን። ይህ ብቻ ግን በቂ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ መሪ ሥር አንድነትን ለመመሥረት ይፈልጋል። እር ሱ እንደራሴውን ስለ ሰጠን (ዮሐ.21፡ 16) አብያተ ክርስቲያን በሙሉ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ተመርተው፣ አንድ አመራር፣ አንድ ትምህርትና አንድ ጸሎተ-ሃይማኖት እንዲኖራት ይፈልጋል። (ዮሐ.10፡ 16)።



የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መንጋ የተከታዮቹን አንድነት ያስረዳናል (ዮሐ.10፡ 16)

ማሰላሰል

በ16ኛው ክፍለ-ዘመን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ልጆችዋ በ ተለዩዋት ጊዜ አልጠፋችም። በእርግጥ የመለያየቱ ጉዳይ እንደ ማዕበል ሆኖ ሊያሰምጣት ፈልጎ ነበር። እርሷ ግን እንደ የጴጥሮስ ጀልባ ከማዕበሉ ዳነች። በትልቁ የትሬንቶ ጉባኤ (ኢ.ኤ.አ. ከ1545-1563 ዓ.ም.) ታድሳ፣ ታማኙን ሕዝብ መምራትዋን ቀጠለች፣ ብዙ ቅዱሳንም ተነሥተው ለእውነተኛዋ ሃይማኖት ተከላከሉላት። በሌሎችም አገሮች፣ በተለይም በዚያኑ ጊዜ በተገኘች በአሜሪካ ምእመናን እየበዙ ሄዱ። በሮማዊ ጳጳስ ብዙ ሚስዮናውያን ተልከው በአፍሪካ፣ በእስያና በውቅያኖስ ደሴቶች የ ክርስቶስን ወንጌል ሰበኩ። በስብከትና በትምህርት ብዙ ሚስዮናውያን በሰማዕትነት ደማቸውን ስለ ክርስቶስ አፍስሰው ብዙ ሕዝብን ወደ ክርስትና መለሱ።

ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሳትከፋፈል አንዲት ሆና ወደ ሁሉም አገሮች ልትስፋፋ የቻለችው የሙሉ ዓለም ካቶሊካውያን አቡናት ከሮማዊ ጳጳስ ጋር ስምምነት ስለነበራቸው ነው። በዚህ ዓለም ላይ ፍጹምና (ሙሉ ቅድስና) ስለሌለ በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ጉድለቶች አልታጡም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተነበየው በእርስዋም ውስጥ ስንዴና እንክርዳድ አብሮ ያድጋሉ (ማቴ.13፡ 30)። ኢየሱስ ግን አልተዋትም (ማቴ.28፡ 20)። ስለዚህ እየተሻሻለች ትሄዳለች እንጂ አትጠፋም።

በልዩ ሁኔታ ልንመለከተው የምንፈልገው ነገር ስለ ትክክለኛው ሃይማኖትዋ ነው። እርስዋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋርያቱ በእደራ የተቀበለችውን ሃይማኖት በመልካም ሁኔታ ጠበቀችው። ባለፉት ዘመናት፣ እስከ ዛሬ ድረስ በየቦታው የተዘረጉት ስሕተቶች የክርስቲያንን ሃይማኖት ሊጐዱና ሊያጠፉ ፈልገው ነበር፣ እርስዋ ግን አልተጐዳችም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ «ሃይማኖትህ እንዳይጐድል ጸሎት አድርጌልሃለሁ» ያለው ቃል በሮማዊ ጳጳስም ላይ ተፈጽሞአል። ከትሬንቶ ጉባኤ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳደሩዋት ጳጳሳት በትምህርታቸውና በመንፈሳዊነታቸው አብርተዋት በመልካም ሁኔታ መርተዋታል። ኢየሱስ ለአሥራ አንዱ ሐዋርያት «የእውነት መን ፈስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» (ዮሐ.16፡ 13) ያላቸው በተከታዮቻ ቸውም ላይ ተፈጸመ። ምክንያቱም አቡናት ከጳጳስ ጋር ተባብረው በዕለታዊ አመራራቸው፣ በተለይም በጉባኤዎች አድርገው እውነተኛዋን ሃይማኖት ጠብቀዋል።

የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ጉባኤዎች

ባለፉት ዘመናት ውስጥ፣ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች በሁሉም አገሮች ሰበካዎች ተደርገው ስለነበሩ ሊቆጠሩ አልቻሉም። ስለዚህ እኛ አሁን መላዋን ቤተ ክርስቲያን የሚመለከቱትን፣ በሮማዊ ጳጳስ ትእዛዝና በብዙዎች አቡናት የተደረጉትን ታላላቅ ጉባኤዎች ብቻ በዝርዝር እንመለ ከታለን፣ ምክንያቱም በእንደዚህ ዓይነት ጉባኤዎች የተገለጹት ትምህርቶች ስሕተት የላቸውም።

1ኛ → ኒቅያ — እ.ኤ.አ. በ325 ዓ.ም.፣ በርእሰ-ሊቃነ ጳጳሳት ሲልቨስተር ጊዜ፣ የተሰበሰቡት አቡናት 318 ነበሩ፣
ውሳኔ ⇒ ክርስቶስ አምላክ አይደለም የሚ ለው የአርዮስ ትምህርት ተወገዘ፣ ክርስቶስ

በባሕርይው የአምላክ ልጅና ከአባቱ ጋር እ ኩል መሆኑ ተገለጸ።

2ኛ → 1ኛ ቁስጥንጥንያ — እ.ኤ.አ. በ381 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ቅ.ዳማሱስ፣ አ ቡናት 150፣
ውሳኔ ⇒ መንፈስ ቅዱስ አምላክ አይደለም የሚለውን የመቄዶንዮስ ትምህርት አውግ ዘው፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑንና ከአ ብና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑን አረጋገጡ።

3ኛ → ኤፌሶን — እ.ኤ.አ. በ431 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ቸለስቲኑስ፣ አቡ ናት 200።
ውሳኔ ⇒ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካሉ የአምላክ ልጅ ሲሆን እውነተኛ የማርያም ልጅም ነው፣ እርስዋም የአምላክ እናት ናት። ንስጥሮስ ግን ከማርያም የተወለደው ከእግዚ አብሔር አብ ልጅ የተለየ ነው ስላለ ተወገዘ።

4ኛ → ኬልቄዶን — እ.ኤ.አ. በ451 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ልዮን 1ኛ፣ አቡ ናት 630።
ውሳኔ ⇒ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ስለሆነ፣ በአንድ አካሉ የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ ይገኛል። ከሁለቱ አንድም ባሕርይ አይጐድለውም። አውጣኪ ግን «ሰብአዊ ባሕርይው ከመለኮታዊ ባሕርይው ጋር ስለ ተዋሐደ ጠፋቶአል» ያለ ው ትምህርት ተወገዘ።

5ኛ → 2ኛ፡ ቁስጥንጥንያ — እ.ኤ.አ. በ553 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ቪጂልዩስ፣ አ ቡናት በ165።
ውሳኔ ⇒ አንዳንድ የኦሪጀንስ ትምህርቶች፣ እንዲሁም የንስጥሮስን ትምህርት የሚመስሉ ትምህርቶች ተወገዙ።

6ኛ → 3ኛ፡ ቁስጥንጥንያ — እ.ኤ.አ. በ680 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ልዮን 2ኛ፣ አ ቡናት 170።
ውሳኔ ⇒ በክርስቶስ ሁለት ፈቃድ (ፍላጐት) =(መለኮታዊና ሰብአዊ) እንደሚገኝ ተገለጸ።

አንድ ፊቃድ ብቻ ነው ያለው የሚለው የሰርግ ዮን ትምህርት ተወገዘ።

7ኛ → ኒቅያ 2ኛ: እ.ኤ.አ. በ787 ዓ.ም.፣ ጳጳስ አድርያኑስ 1ኛ፣ አቡናት 300።
ውሳኔ ⇒ የቅዱሳን ምስሎችና ሥዕሎች አክብሮት ክርስቲያናዊ እንጂ አረማዊ ሥርዓት አይደለም ብለው ገለጹ።

8ኛ → 4ኛ: ቁስጥንጥንያ እ.ኤ.አ. በ869 ዓ.ም.፣ ጳጳስ አድርያኑስ 3ኛ፣ አቡናት 102።
ውሳኔ ⇒ የሥዕል ጠላቶች እንደገና ተወገዙ።

9ኛ → 1ኛ: ላቴራን እ.ኤ.አ. በ1123 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ካሊስቱስ 2ኛ፣ አቡናት 300።
ውሳኔ ⇒ የአቡናት ምርጫ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት እንጂ የመንግሥት ኃላፊነት አይደለም።

10ኛ → 2ኛ: ላቴራን እ.ኤ.አ. በ1139 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ኢኖቸንስ 2ኛ፣ አቡናት 800።
ውሳኔ ⇒ ለወገነ ክህነት የሚሆኑ ሕጎችና ዕድሎች ተወሰኑ።

11ኛ → 3ኛ: ላቴራን እ.ኤ.አ. በ1179 ዓ.ም.፣ ጳጳስ እስክንድር አቡናት 1000።
ውሳኔ ⇒ የአልቢጀንስስ እና የቫልደንስስ መናፍቅነት ተወገዘ።

12ኛ → 4ኛ: ላቴራን እ.ኤ.አ. በ1212 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ኢኖቸንስ 3ኛ፣ አቡናት 412፣ ሌሎች መነኮሳንና ልኡካን 1000።
ውሳኔ ⇒ ስለ ምሥጢረ-ሥላሴ፣ ምሥጢረ-ሥጋዌና፣ ቅዱስ ቍርባን ብዙ ትምህርት ተገለጸ፣ ምእመናን በየዓመቱ እንዲናዘዙና እንዲቆርቡ ተወሰነ።

13ኛ → 1ኛ ልዮን እ.ኤ.አ. በ1245 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ኢኖቸንስ 4ኛ፣ አቡናት 150።

ውሳኔ ⇒ ስለ ክህነትና ስለ ቅዱስ ቍርባን እንዲሁም ስለ የንስሐ ቦታ ገለጻ ተደረገ።

14ኛ → 2ኛ ልዮን እ.ኤ.አ. በ1274 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ጎርጎርዮስ 10ኛ፣ አቡናት 500።
ውሳኔ ⇒ ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ምርጫና ስለ ቤተ ክርስቲያን አድንድነት ውሳኔ ተሰጠ። ስለ የሰው ፍጻሜዎች (ፍርድ፣ ማንግሥተ-ሰማይ፣ ገሃነመ-እሳት... ወ.ዘ.ተ.)፣ ስለ መን ፈስ ቅዱስም ገለጻ ተደረገ።

15ኛ → ቪን እ.ኤ.አ. በ1311 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ቀለሜንጦስ 5ኛ፣ አቡናት 132።
ውሳኔ ⇒ ተምፕላር የሚባሉት ማኅበር ተሸንፎ፣ ለካህናትና ለገዳማውያን የሚሆኑ ሕጎች ተወሰኑ። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት የሚመለከቱ ሥርዓቶች (ደንቦች) ተወሰኑ።

16ኛ → ኮስታንስ እ.ኤ.አ. በ1414 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ጎርጎርዮስ 12ኛ፣ አቡናት 200።
ውሳኔ ⇒ የዊክልፍና የሑስ (ፕሮቴስታንቶች) ትምህርት ተወገዙ።

17ኛ → ፌረንጳ እ.ኤ.አ. በ1438 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ኤውጀንዮስ 4ኛ፣ አቡናት (ካቶሊካውያንና ኦርቶዶክሳውያን) ከ100 በላይ።
ውሳኔ ⇒ የር.ሊ.ጳጳሳት ሥልጣን ከአቡናት ሥልጣን ይበልጣል የሚለው ትምህርት ተገለጸ። የካቶሊካዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አንድነት ተፈረመ።

18ኛ → 5ኛ: ላቴራን እ.ኤ.አ. በ1512 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ዩልዮስ 2ኛ፣ አቡናት 95።
ውሳኔ ⇒ ነፍስ ትሞታለች የሚል ስሕተት ተወገዘ። ር.ሊ.ጳጳስ በጠቅላላ ጉባኤ የበላይ ሥልጣን አላቸው ተብሎ ተወሰነ።

19ኛ → ትሬንቶ እ.ኤ.አ. በ1545 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ጳውሎስ 3ኛ፣ አበ-ናት 255፣ ከገዳማውያን ልኡካንና ከቴም ሎጋውያን ጋር ሆነው የክርስቲያናዊ ሃይ ማኖት ትምህርቶችን በሙሉ መርምረው ትክ ክለኛውን መንገድ አሳዩ።
ውሳኔዎች ⇒ ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ትርጓ ሜው፣ ስለ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት፣ ስለ የአዳም ኃጢአት፣ ስለ ጥምቀትና ሌሎች ም ሥጢራት፣ በተለይም ስለ ምሥጢረ-ቍር ባን፣ ስለ መስዋዕተ-ቅዳሴና ስለ ንስሐ፣ ስለ ንስሐ-ቦታ... ወ.ዘ.ተ. ውሳኔ ተሰጠ። የ ፕሮቴስታንቶች ስሕተት በሙሉ ተወገዙ።

20ኛ → 1ኛ፡ ቫቲካን እ.ኤ.አ. በ1869 ዓ.ም.፣ ጳጳስ ፒዮስ 9ኛ፣ አበ-ናት 600።
ውሳኔዎች ⇒ ሮማዊ ር.ሊ.ጳጳሳት ስለ ሃይ ማኖትና ስለ ሞራል ሊያስተምሩ በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ስለሚያስተምሩ አይሳሳቱም የሚል ትምህርት ተገለጸ። ሌላ የሃይማኖት ጉዳይም ተወሰነ።

21ኛ → 2ኛ ቫቲካን እ.ኤ.አ. በ1962፣ ጳጳስ ዮሐንስ 23ኛ፣ አበ-ናት 2870።
ውሳኔዎች ⇒ የቤተ ክርስቲያንን መታደስ የሚደግፉ ነገሮች በሙሉ ተዘረዘሩ፣ ተወሰ ኑም። ለምሳሌ፡- ሥርዓተ አምልኮ፣ የሁሉም ክርስቲያኖች መቀራረብ (አንድነት)፣ ክርስቲ ያናዊ ሥነ አስተዳደግ፣ የቤተ ክርስቲያን መብትና ግዴታ፣ በተለይም በዚህ ዘመን በ ዓለም ልትፈጽማቸው የሚገባት መንፈሳዊ ተግባሮች... ወ.ዘ.ተ. ተዘረዘሩ።



2ኛ የቫቲካን ጉባኤ ታላቅ ስብሰባ (እ.ኤ.አ. ጥቅምት 1963 ዓ.ም.)

ምዕራፍ 2

የእውነተኛ የክርስቶስ ማሕበር ምልክቶች

አስቀድመን እንደ ተመለከትነው፣ አንዳንድ በቤተ ክርስቲያን ሁኔታ የሚቆረቁሩ ተማሪዎች፣ የአብያተ-ክርስቲያናትን መለያየት አይተው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡልናል። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዲት ማኅበር እንጂ ብዙ ማኅበራትን አልመሠረተም፣ ያች እርሱ የመሠረታት አለች ወይ? አሁን ካሉት አብያተ-ክርስቲያናት የትኛዋ ናት? እንዴት ናት? ይላሉ። እነዚህን ጥያቄዎች ስንመልስ፣ ሁሉንም እንዲጠቅም በማለት የክርስቶስ ማሕበር መታወቂያዎችን እናቀርብላቸዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጴጥሮስ ላይ የመሠረታት ማሕበር በ እርግጥ አለች። እስከ ዓለም መጨረሻም አትጠፋም። ምክንያቱም ጌታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ይህችን ማሕበር (ቤተ ክርስቲያን) የሞት ኃይ ል እንኳ አያሸንፋትም» (ማቴ.16፡ 18) ብሎ ትንቢት ተናግሮአል። ለይ ተን እንድናውቃት የመታወቂያ ምልክቶች ያስፈልጉናል፡[redacted]

[redacted]

ምክንያቱም በመካከላቸን ወዳጅነት እንጂ ጥላቻ እንዲኖር አንፈልግም።

[redacted]

ማለት «ወ[redacted]ን ነገር በየ[redacted]ን ያቱም ሁላችንም የሰማያዊው አባታችን ልጆች ነን፣ ሁላችንም የሥላሴ አማኞች፣ የክርስቶስ ተከታዮች፣ የእመቤታችን ድንግል ማርያም አክባሪዎችና ምሥጢራትን የምናዘወትር ክርስቲያኖች ስለሆንን፣ በዚህ ስምምነት ደስ ይበለን፣ ተከባብረንም እንኑር።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ እውነትን ሙሉ በሙሉ እንዲያውቅ መል ካም ነው። «በተለይም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሃይማኖት እውነትን መፈለግ ግዴታው ነው» (2ኛ የቫቲካን ጉባኤ 15፡ 1፤ 2)። እውነትን ተግቶ ካልፈለጋት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አይፈጽምም (1ጢሞ.2፡ 4)። ስለዚህ እያንዳንዳችን ጸሎት ካደረግን በኋላ፣ በተሰጡን መታወቂያዎች ተጠቅመን የክርስቶስን ማሕበር ልናውቃት እንችላለን። ጳጳስ ፒዮስ 9ኛ እንዳስተማሩት፣ የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ መታወቂያዎች [redacted]

[redacted]

1) «አንዲት ናት»፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ማኅበሬ (ቤተ ክርስቲያኔ)» አለ እንጂ ማኅበሮቼ አላለም (ማቴ.16፡ 18)። አንዲት ለ መሆን የማትከፋፈልና የማትለያይ መሆን ስላለባት በዓለም ሙሉ እም ነቷ አንድ፣ ትምህርትዋ አንድ፣ መሪዋም አንድ ነው። አንድ መሪ ማለ ት ቤተ ክርስቲያንን የሚመራት ልዑል አለቃ ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳ ት አንድ ነው። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንድ ሐዋርያ ብቻ «መንጋዎቼን ጠብቅ» (ዮሐ.21፡ 16) ስላለ «አንድ መንጋ በአንድ እረኛ ሥር እንዲሆኑ» ይፈልጋል። በውጭ ያሉት በጎች (የተለዩት ክር ስቲያኖች) በአንድ እረኛ ሥር እንዲመለሱ ይፈልጋል (ዮሐ.12፡ 16)።

ቅ.ጳውሎስም አንድነት አስፈላጊ መሆኑን ይነግረናል፡- «ወንድሞቼ ሆይ! እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ፣ እኔ የጴጥሮስ ነኝ፣ እኔ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ወንድሞቼ ሆይ! መለያየት በመካከላ ችሁ አይኑር፣ ሁላችሁም ተስማምታችሁ በአንድ አሳብና በአንድ ዓላማ ጸንታችሁ ኑሩ፣ ክርስቶስ ተከፍሎአልን?...» (1ቆሮ.1፡ 10-13)። «ሁላችን ም አንድ አካል (አንድ ማኅበር) ለመሆን በአንድ መንፈስ ቅዱስ ተጠምቀ ናል» (1ቆሮ.12፡ 13)። እንግዲህ እውነተኛ የክርስቶስ ማኅበር ወደ ሁለ ት ወይም ሦስት ወይም ብዙዎች ማኅበራት ልትከፋፈል በጭራሽ አት ችልም።

2) «ቅድስት ናት»፣ በእግዚአብሔር በኩል ቤተ ክርስቲያን ቅድስት መሆንዋ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (ኤፌ.4፡ 16)፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ቅዱ ስ ነው፣ ነፍስዋ የሆነውና ሕይወትን የሚሰጣት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፣ የተቀበለችው የጸጋ ሃብት በተለይም ምሥጢራት ቅዱሳን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በሰው በኩልም ቅድስት ናት፣ ምክንያቱም የ ክርስቶስ ማኅበር ለምእመናን ቅድስና ስለተመሠረተች እውነተኛ ከሆነች የግድ ቅዱሳንን ታፈራለች። ምእመናን የክርስቶስ አካል ስለሆኑ ወደ ቅድስና የተጠሩ ናቸው (1ቆሮ.12፡ 27)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እነርሱ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ፣ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ ቅዱስ አደርጋለሁ» አለ (ዮሐ.17፡ 19)፣ የክርስቶስ ተልእኮና መሥዋዕትነት

ምዕራፍ ፭

የእውነተኛ የክርስቶስ ማሕበር ምልክቶች

አስቀድመን እንደ ተመለከትነው፣ አንዳንድ በቤተ ክርስቲያን ሁኔታ የሚቆረቁሩ ተማሪዎች፣ የአብያተ-ክርስቲያናትን መለያየት አይተው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡልናል። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዲት ማኅበር እንጂ ብዙ ማኅበራትን አልመሠረተም፣ ያች እርሱ የመሠረታት አለች ወይ? አሁን ካሉት አብያተ-ክርስቲያናት የትኛዋ ናት? እንዴት ናት? ይላሉ። እነዚህን ጥያቄዎች ስንመልስ፣ ሁሉንም እንዲጠቅም በማለት የክርስቶስ ማሕበር መታወቂያዎችን እናቀርብላቸዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጴጥሮስ ላይ የመሠረታት ማሕበር በ እርግጥ አለች። እስከ ዓለም መጨረሻም አትጠፋም። ምክንያቱም ጌታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ይህችን ማሕበር (ቤተ ክርስቲያን) የሞት ኃይ ል እንኳ አያሸንፋትም» (ማቴ.16፡ 18) ብሎ ትንቢት ተናግሮአል። ለይ ተን እንድናውቃት የመታወቂያ ምልክቶች ያስፈልጉናል። ዛሬ በየራሳ ቸው ስም የሚጠሩት አብያተ-ክርስቲያናት እነ ኦርቶዶክሳዊት፣ ተዋ ሕዶ፣ ካቶሊካዊት፣ ወንጌላዊት፣ አንግሊካዊት... ወ.ዘ.ተ. ብዙ ናቸው። እነዚህ በሙሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚያከብሩ፣ ይህች ቤተ ክርስቲያን ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ትበልጣለች ለማት አንወድም። ምክንያቱም በመካከላችን ወዳጅነት እንጂ ጥላቻ እንዲኖር አንፈልግም። ጳጳስ ዮሐንስ 23ኛ ለኦርቶዶክሳውያን ልኡካን እንዳሉዋቸው ሁሉ፣ ማለት «ወንድሞቼ ሆይ የሚለያየንን ነገር ትተን አንድ የሚያደርገንን ነገር በደንብ እናስብ»፣ እኛም ስለ ወንድማማችነታችን እናስብ። ምክን ያቱም ሁላችንም የሰማያዊው አባታችን ልጆች ነን፣ ሁላችንም የሥላሴ አማኞች፣ የክርስቶስ ተከታዮች፣ የአመቤታችን ድንግል ማርያም አክባሪዎችና ምሥጢራትን የምናዘወትር ክርስቲያኖች ስለሆንን፣ በዚህ ስምምነት ደስ ይበለን፣ ተከባብረንም እንኑር።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ እውነትን ሙሉ በሙሉ እንዲያውቅ መል ካም ነው። «በተለይም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሃይማኖት እውነትን መፈለግ ግዴታው ነው» (2ኛ የቫቲካን ጉባኤ 15፡ 1፤2)። እውነትን ተግቶ ካልፈለጋት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አይፈጽምም (1ጢሞ.2፡ 4)። ስለዚህ እያንዳንዳችን ጸሎት ካደረግን በኋላ፣ በተሰጡን መታወቂያዎች ተጠቅመን የክርስቶስን ማሕበር ልናውቃት እንችላለን። ጳጳስ ፒየስ 9ኛ እንዳስተማሩት፣ የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ መታወቂያዎች በቦኛው

የቀኖጥንጥንያ ጉባኤ ላይ አበው ባስተላለፉልን ጸሎተ-ሃይማኖት የ ሚገኙት አራት ነገሮች ናቸው። እነርሱም ቤተ ክርስቲያን አንዲት፣ ቅድስት፣ ዓለም-አቀፋዊትና ሐዋርያዊት ናት የሚሉት ናቸው። እነዚህን አራት መታወቂያዎች ያላት ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ የክርስቶስ ማሕበር ናት። አሁን አራቱን ምልክቶች አንድ በአንድ እንመልከት።

1) «አንዲት ናት»፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ማኅበሬ (ቤተ ክርስቲያኔ)» አለ እንጂ ማኅበሮቼ አላለም (ማቴ.16፡ 18)። አንዲት ለ መሆን የማትከፋፈልና የማትለያይ መሆን ስላለባት በዓለም ሙሉ እም ነታ አንድ፣ ትምህርትዋ አንድ፣ መሪዋም አንድ ነው። አንድ መሪ ማለ ት ቤተ ክርስቲያንን የሚመራት ልዑል አለቃ ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳ ት አንድ ነው። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንድ ሐዋርያ ብቻ «መንጋዎቼን ጠብቅ» (ዮሐ.21፡ 16) ስላለ «አንድ መንጋ በአንድ እረኛ ሥር እንዲሆኑ» ይፈልጋል። በውጭ ያሉት በጎች (የተለዩት ክር ስቲያኖች) በአንድ እረኛ ሥር እንዲመለሱ ይፈልጋል (ዮሐ.12፡ 16)።

ቅዳውሎስም አንድነት አስፈላጊ መሆኑን ይነግረናል፦ «ወንድሞቼ ሆይ! እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ፣ እኔ የጴጥሮስ ነኝ፣ እኔ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ወንድሞቼ ሆይ! መለያየት በመካከላ ችሁ አይኑር፣ ሁላችሁም ተስማምታችሁ በአንድ አሳብና በአንድ ዓላማ ጸንታችሁ ኑሩ፣ ክርስቶስ ተከፍሎአልን?...» (1ቆሮ.1፡ 10-13)። «ሁላችን ም አንድ አካል (አንድ ማኅበር) ለመሆን በአንድ መንፈስ ቅዱስ ተጠምቀ ናል» (1ቆሮ.12፡ 13)። እንግዲህ እውነተኛ የክርስቶስ ማኅበር ወደ ሁለ ት ወይም ሦስት ወይም ብዙዎች ማኅበራት ልትከፋፈል በጭራሽ አት ችልም።

2) «ቅድስት ናት»፣ በእግዚአብሔር በኩል ቤተ ክርስቲያን ቅድስት መሆንዋ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (ኤፌ.4፡ 16)፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ቅዱ ስ ነው፣ ነፍስዋ የሆነውና ሕይወትን የሚሰጣት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፣ የተቀበለችው የጸጋ ሃብት በተለይም ምሥጢራት ቅዱሳን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በሰው በኩልም ቅድስት ናት፣ ምክንያቱም የ ክርስቶስ ማኅበር ለምእመናን ቅድስና ስለተመሠረተች እውነተኛ ክሆነች የማድ ቅዱሳንን ታፈራለች። ምእመናን የክርስቶስ አካል ስለሆኑ ወደ ቅድስና የተጠሩ ናቸው (1ቆሮ.12፡ 27)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እነርሱ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ፣ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ ቅዱስ አደርጋለሁ» አለ (ዮሐ.17፡ 19)፣ የክርስቶስ ተልእኮና መሥዋዕትነት

ለከንቱ ስላልሆነ ምንም እንኳ ብዙዎች ባይከተሉትም ብዙዎች ክርስቲ ያኖች ደግሞ ተቀድሰዋል። እነዚህ ቅዱሳን ክርስቲያኖች ወደ ሰማይ ከመሻገራቸው በፊት በዚህ ምድር የቅድስናቸውን ምልክት ትተውልናል። ያደረጉት ብዙ ተአምራትም የቅድስናቸው ማስረጃ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በዚህች ዓለም እስካለች ድረስ በየዓይነቱ ዓሣ የ ምትሰበስብን መረብ ትመስላለች (ማቴ.13፡ 47)፣ ስለዚህ ልጆችዋ ክኃጢ አት ነፃ አይደሉም፣ ሁላቸውም ቅዱሳን ባይሆኑም ብዙ ቅዱሳንን ስለ አፈራች እርስዋም ቅድስት ናት።

3) «ዓለም-አቀፋዊት ናት»፣ ይህም ማለት ሁሉንም ሰው ለማቀፍ ትፈለጋለች። እንደ ብሉይ-ኪዳን ሃይማኖት ሳትሆን ለዓለም ሕዝብ በሙሉ የተመሠረተች ናት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የእግዚ አብሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል» ብሎአል (ማቴ.24፡ 14)። እንዲሁም «ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፣ በአብና በወልድ፣ በ መንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ-መዛሙርት አድርጉ አቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩአቸው» ብሎአል (ማቴ.28፡ 19)። ቤተ ክርስቲያን ከሰናፍጭ ዘር በወጣችው ዛፍ ትመሰላ ለች። ለሁሉም የሰው ልጆች ማረፊያ (ጥላ ከለላ) ለመሆን ቅርንጫፎች ዋን ወደ ሁሉም አቅጣጫ ትዘረጋለች (ማቴ.13፡ 32)። ስለዚህ እውነተኛ የክርስቶስ ማኅበር ክርስቶስ ለሐዋርያቱ አደራ ያላቸውን ተልእኮ (ማቴ. 28፡ 20) በመቀጠል ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መዳን ተግታ ትሠራለች። ወደ አንድ ወይም ወደ ጥቂት አካባቢ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ሁሉም ሀገ ሮች የወንጌል ሰባኪዎችን ትልካለች። በሁሉም ሰዎች ልብ ውስጥ የ እግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ትጥራለች። እውነተኛዋን የክር ስቶስ ማኅበር በዚህ ሐዋርያዊ ሥራ ልናውቃት እንችላለን።

4) «ሐዋርያዊት ናት»፣ ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበሩን መሥርቶ ለሐዋርያቱ አደራ ሰጣቸው፡- «እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል» አላቸው (ሉቃ.10፡ 16)። ለጴጥሮስ «እነሆ ለአንተ የ መንግሥተ-ሰማይን መክፈቻዎች (የማኅበሬን ሙሉ ሥልጣን) እሰጥ ሃለሁ» (ማቴ.16፡ 19)፣ «በጎቼን ጠብቅ» (ዮሐ.21፡ 17) ስላለው ቤተ ክርስቲያን በመላው ዓለም የተስፋፋችውና የጠነከረችው በሐዋርያት መሪነትና ሥራ ነው። በዚህ ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ «በሐዋርያትና በነቢያትም መሠረት ላይ ታንጻችኋል» ይላል። (ኤፌ.2፡ 20)። ሐዋርያት ከክርስቶስ የተቀበሉትን ማዕረግና ሥልጣን ለተከታዮቻቸው አስተላለፉ ላቸው። ይህንንም ማስተላለፍ የሚፈጽሙት እጃቸውን በመጫን ነበር (2ጢሞ.1፡ 6)።

የሐዋርያት ተከታዮች በሉሁ ጊዜ ጳጳሳትና አቡናት ናቸው። የ አነርሱ ሥልጣን ከሐዋርያት ሥልጣን ጋር እኩል ነው፣ ምክንያቱም የትሬንቶ ጉባኤ እንደሚያስተምረው ሐዋርያት ማዕረጋቸውንና ሥልጣ ናቸውን ለወራሾቻቸው የሚያካፍሉት በክርስቶስ ትእዛዝ ነው። ከሐዋርያ ትና ከወራሾቻቸው እጅ ማዕረገ ጵጵስናን የተቀበሉት ማዕረጋቸው ከእነርሱ ጋር ትክክል (እኩል) ነው። ከማንም ተራ ሰው የተቀበሉት ግን ማዕረግ የላቸውም። እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ወራሾች ማለትም በር.ሊ.ጳጳሳትና በአቡናት ትመራለች። አንዲት ማኅበር አቡን (ጳጳስ) ከሌላት፣ ወይም አቡኑ ከጴጥሮስ ወራሽ (ከር.ሊ.ጳጳሳት) ጋር ስምምነት ከሌለው በእውነቱ ሐዋርያዊት ናት ልንላት አንችልም።

መደምደሚያ

የክርስቶስን ማኅበር መታወቂያዎች ከገለጽን ዘንድ፣ እያንዳንዱ ሰው በጎሊናው እውነተኛዋን የክርስቶስ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ለይቶ ሊያውቃት ይችላል። ከምናውቃቸው አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥ አንድዋ በመላው ዓለም ተስፋፍታ የምትገኝ፣ ልጆችዋ በሙሉ በአንድ ጳጳስ ብቻ የሚመሩ ከሆኑ፣ አቡኖቻቸው ከአንዱ ጳጳስ (ከየጴጥሮስ ወራሽ) ጋር ስምምነትና ተአዝዞ ያላቸው ከሆኑ፣ ቅዱሳንን ያፈራችና እስከ ዛሬም የምታፈራ ከሆነች፣ ምንም እንኳ አንዳንድ ልጆችዋ መልካም አርአያ የሚሰጡ ባይሆኑም፤ እርስዋ እውነተኛ የክርስቶስ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ናት። እርስዋ መሪያችን ልትሆን ይገባታል። በዚህ ዓለም አንዳንድ ጉድለቶች አይታጡባትም። ስለ ሃይማኖት ግን ከሁሉም ስሕተት ትጠበቃለች። በመንግሥተ-ሰማይ ደግሞ እንከን የሌለባት ንጽሕትና ውብ ሆና (ኤፌ.5፡ 27) ለዘለዓለም ትበራለች፣ ትከብራለችም።



ኦርቶዶክሳውያን አቡናት ወደ ሮማ ሄደው የጴጥሮስን ወራሽ እንደ ጉበኙ

ምዕራፍ 3

ክርስቲያን ያልሆኑ ሃይማኖቶች

በዚህ ዓለም ላይ ከክርስትና ሃይማኖት ሌላ ብዙ ሃይማኖቶች አሉ። እነሱም አይሁዳውያን፣ እስላሞች፣ ሂንዱ፣ ቡዲስት፣ ኮንፍዩሽኒስት፣ ተኦይስት፣ ሺንቶይስት፣.... ወዘተ. ናቸው። የእነዚህ ሃይማኖቶች ተከታዮች ምንም እንኳ እምነታቸው ከእምነታችን የተለየ ቢሆንም ወንድሞቻችን ናቸውና ከእኛ ጋር አንድ ቤተሰብ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም ፈጣሪያችን አንድ ነው። 2ኛ የቫቲካን ጉባኤ 16፡ 1 ክርስቲያን ስላልሆኑት

ወንድሞቻችን ሲናገር «የሰው ልጆች ሁሉ ምንጭ አንድ ነው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ሰው (ከአዳም) ፈጠረ፣ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩም አደረገ (የሐዋ.ሥራ 17፡ 26)፣ ጥበቃው፣ የቸርነቱ ምስክርነትና የድኅነቱ ውሳኔም ለሰው ሁሉ ስለሆነ፣ እርሱ የሁሉም ሰው የመጨረሻ (ዋና) ዓላማ ነው» ይላል። ከላይ በስም ከ ጠቀስናቸው ሃይማኖቶች ውስጥ አንዳንዱን እንመልከት፣

አይሁዳውያን፡- እነዚህ በብሉይ-ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆነው በሙሴና በነቢያት ተመርተው መድኃኔ-ዓለምን በተስፋ የሚጠ ባበቁ የነበሩት የልጅ ልጆች ናቸው። የእግዚአብሔርን ሕግ በመቀበል፣ መጽሐፍ ቅዱስን በመድረስና በመጠበቅ የሕዝበ-ክርስቲያን መሠረት የ ሆኑት እነርሱ ናቸው። ሕዝበ-ክርስቲያን «እንደ የዱር ወይራ ዛፍ ተቆ ርጠው በመልካሙ የወይራ ዛፍ (በእስራኤላውያን) ላይ የተተከሉ ናቸ ው» (ሮሜ 11፡ 24)፣ በመሆናቸውም ወራሾቻቸው ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እመቤታችን ማርያምና ሐዋርያት ከዘራቸው ስለ ተወለዱ አይሁዳውያን ክቡራን ናቸው። «እነርሱ የእግዚአብሔር ወዳጆች ናቸው» (ሮሜ 11፡ 29)።

እስላሞች፡- እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ ልዑል፣ ሁሉን ቻይና መሐሪ መሆኑን አምነው ያመልኩታል፣ ያወድሱታልም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ነቢይ፣ እናቱን እመቤታችን ማርያምን ደግሞ ድንግልናዋን አምነው ያከብሩዋቸዋል። የራሳቸውንም ሕግ በመጠ በቅ፣ ጸሎት፣ ጾምና ምጽዋትን በማዘውተር፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለ ማግኘት ይታገላሉ። ልክ እንደ እኛ የፍርድ ቀንና የሙታንን ትንሣኤ በእምነት ይጠባበቃሉ።

ሂንዱ፡- በዓለም ውስጥ ካለው ሥቃይና ብስጭት ለመዳን በ እምነትና በፍቅር ወደ ብራህማ (አምላካቸው) ይማጠናሉ፣ በንስሐና በተጋድሎ ይኖራሉ። እነርሱ እንደሚያስቡት፣ ከሞታቸው በኋላ የሚያጋ ጥማቸውን የተለያየ የመንጻት (ንጹሕ የመሆን) ሕይወት ከአሳለፉ በ ኋላ በመጨረሻ ዘለዓለማዊ ብፅዕናን ለማግኘት ተስፋ ያደርጋሉ።

ቡዲስት፡- የልብን ሰላምና ንጽሕናን ለማግኘት ብለው ይጸልያሉ፣ ተጋድሎም ያደርጋሉ። ከአሥሩ ትእዛዛት ጋር የሚመሳሰሉትን ልዩ ትእ ዛዞች ይጠብቃሉ። በተለይም መነኩሴዎቻቸው ጸሎተኞች ናቸው። የ ዓለምን ምኞት ሁሉ ትተው በድኽነት ይኖራሉ። ምግብና ዕንቅልፍ አያበ ዙም፣ በመንፈሳዊ ነገሮች ደግሞ ብርቱዎች ናቸው።

በእውነቱ ከነዚህ ከዘረዘርናቸው ሃይማኖቶች (ሕዝቦች) መልካም ትምህርትና ሞራላዊ ተግባር ይገኛል። በሌሎች ያልጠቀስናቸው ሃይማኖቶችም አንዳንድ እውነቶችና ቅዱስ ነገሮች ስለሚገኙ ልናከብራቸው ይገባል። በቀና እምነት ፈጣሪን የሚያመልኩ፣ እንደ ጎሊናቸው፣ ማለትም በልባቸው እንደሚሰማቸው አድርገው የእግዚአብሔርን ፍላጎት የሚፈጽሙ በደኅንነት ጐዳና ላይ የሚገኙ ናቸው።

የሰው ልጆች በሙሉ፣ ያለ ምንም ልዩነት ለዘለዓለማዊ ሕይወት ስለ ተፈጠሩ፣ ከዚያ እነርሱ ከያዙት በቀር ሌላ የበለጠ መንገድ እንደሌለ በልባቸው አምነው፣ በመልካም ሁኔታ ከተካሄዱ፣ በየትኛውም ሃይማኖት ሳሉ፣ በቀና አስተሳሰባቸውና በእግዚአብሔር ቸርነት ድኅነትን እንደሚያገኙ እናምናለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፣ ከአብርሃም ከይስሐቅ፣ ከያዕቆብ ጋር በመንግሥተ-ሰማይ ይቀመጣሉ» (ማቴ.8፡ 11) ያለው ቃል የዓለምን ሕዝብ በሙሉ ይመለከታል። እንግዲህ በወዲያኛው ዓለም እነርሱም ከእኛው ጋር የ መንግሥተ-ሰማይ ወራሾች ናቸውና በዚህ ምድር ከሁሉም ጋር በወንድ ማማችነት፣ በፍቅርና በሰላም መመላለስ፣ ስለ ሁሉም ድኅነት ደግሞ ጸሎት ማድረግ ኃላፊነታችን ነው።

ቤተ ክርስቲያን የዓለምን ሕዝብ በሙሉ ታከብራለች፣ ሕዝበ-ክርስቲያንም ክርስቲያን ካልሆኑት ሕዝቦች ጋር በወንድማማችነት እንዲኖሩ አደራ ትላቸዋለች፣ ሁሉም ባለፉት ዘመናት ውስጥ በመካከላቸው ያነበረው ጥላቻን ረስተው በስምምነት ሰላምና ነፃነትን እንዲደግፉ፣ ይህችንም ዓለም እንዲያሻሽሉ ታበረታታቸዋለች። ቤተ ክርስቲያን የዓለምን ሕዝብ የምታግዘው በተለይም ክርስቶስን በመስጠት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ሁሉ መድኃኒትና አስተማሪ ስለሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለመፈጸም ሁሉንም የሰው ልጆች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው (ማቴ.28፡ 19)። ጸጋውንና ትምህርቱንም ታቀርብላቸዋለች።

> «እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁ፣ ደግሞም በሰማይ ያለው አባታችሁ አንድ ብቻ ነው» (ማቴ.23፡ 8-9)።
> «ሸክማችሁ የከበደባችሁ እናንተ ደካሞች ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ! እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ» (ማቴ.11፡ 28)።
> «መንገድና እውነት ሕይወትም እኔ ነኝ» (ዮሐ.14፡ 6)።

የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሕዝብ ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

(«ታይም» ከተባለ መጽሔት፡- እ.ኤ.አ. ግንቦት 1982 ዓ.ም. የተወሰደ)

ካቶሊካውያን	809,000.000	1 ማኅበር
ኦርቶዶክሳውያን (ግሪክ)	150,000.000	14 ማኅበራት
ኦርቶዶክሳውያን (ተዋሕዶ)	30.000.000	5 ማኅበራት
ፕሮቴስታንቶች	345.000.000	በጣም ብዙ ማኅበራት
የክርስቲያኖች ጠቅላላ ድምር =	1,434.000.000	
አይሁዳውያን	17,000.000	
እስላሞች	723,000.000	
ሂንዱ	583,000.000	
ቡዲስት	274,000.000	
ኮንፍዩሽኒስት (ቻይና)	480,000.000	
ታኦይስት (ቻይና)	40,000.000	
ሺንቶይስት (ጃፓን)	60,000.000	
ኣቴይስት	520,000.000	
አኒሚስት (ትራይባል)	36,000.000	
ሌሎች ዓይነቶች	270,000.000	
የዓለም ሕዝብ ድምር =	4,374.000.000	

«እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁ፣ ደግሞም በሰማይ ያለው አባታችሁ አንድ ብቻ ነው»። (ማቴ.23፡ 8-9)

የክርስቲያን ጸሎቶች



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን የጸሎት አደራረግ አስተማራቸው (ማቴ.፮፡ ፱)

በስመ አብ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ አሜን።
አምላኬ ሆይ እሰግድልሃለሁ፣ በልቤ በፍጹም እወድሃለሁ፣ ስለ ፈጠርከኝና ክርስቲያን ስላደረግኸኝ፣ በዚህች ሌሊት (በዚህች ቀን) ስለ ጠበቅኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሥራዬን ሁሉ ላንተ አቀርባለሁ፣ በዚህች ቀን (በዚህች ሌሊት) ከኃጢአት እንድትጠብቀኝ ከክፉ ነገርም ሁሉ እንድታድነኝ እለምንሃለሁ።

አባታችን

በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ! ስምህ ይመስገን መንግሥትህ ይምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን።
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን። እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በልልን፣ ከክፉ ሰውረን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፣
መንግሥት፣ ኃይልና ክብር ለዘላለም ያንተ ነውና አሜን።

ሰላም ላንቺ

ጸጋ የመላሽ ማርያም ሆይ! ሰላም ላንቺ ይሁን።
እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው፣ ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ፣ የሆድሽም ፍሬ ኢየሱስ የተባረከ ነው።
ቅድስት ማርያም የአምላክ እናት ለእኛ ለኃጢአተኞች አሁንም በሞታችንም ጊዜ ለምኝልን።

ምስጋና

ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይሁን።
አሁንም ዘወትርም ለዘለዓለምም አሜን።

የሐዋርያት ጸሎተ-ሃይማኖት

ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ፣

የአብ አንድ ልጅ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም አምናለሁ፣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ተፀነሰ ከድንግል ማርያም ተወለደ፣ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን ተሠቃየ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ ወደ ሲኦል ወረደ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ፣ ወደ ሰማይ ወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ፣ ያሉትንና የሞቱትን ሊፈርድ ዳግመኛ ይመጣል። በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ፣ የሁሉም በሆነችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳንም አንድነት አምናለሁ፣ በኃጢአት ሥርየት፣ በሙታን ትንሣኤ፣ በዘለዓለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።

የሃይማኖት ሥራ

አምላኬ ሆይ! አንተ የገለጽከውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምታም ነውንና የምታስተምረውን ሁሉ አምናለሁ።

የተስፋ ሥራ

አምላኬ ሆይ! ተስፋ የሰጠኸው ቃልህ እውነተኛ ነውና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትሩፋት የዘለዓለምን ሕይወት እንደምትሰጠኝና ወደዚያውም ለመድረስ ጸጋህን እንደምታድለኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

የፍቅር ሥራ

አምላኬ ሆይ! አለመጠን ደግ አለመጠንም ተወዳጅ ነህና እወድሃለሁ፣ ስላንተ ፍቅር ሰውንም ሁሉ እወዳለሁ።

የንስሐ ሥራ

አምላኬ ሆይ! ፍጹም ተወዳጅ ነህ፣ ኃጢአትን የምትጠላ ነህ፣ በ ኃጢአቴ ስለበደልሁህ እጅግ አዝናለሁ፣ ማረኝ፣ ዳግመኛ ወደ ኃጢአት አልመለስም፣ በጸጋህ ከኃጢአት ምክንያት ሁሉ እርቃለሁ።

ወደ እመቤታችን መማጠኛ ጸሎት

እጅግ ርኅሩኅት የሆንሽ ድንግል ማርያም ሆይ! ባንቺ ጥበቃ ከተማ ጠኑ እርዳታሽን ከለመኑ፣ አማላጅነትሽንም ከፈለጉ ሰዎች አንድ እንኳ የተሰነነ እንዳልተሰማ አስቢ፣ የድንግሎች ድንግል የሆንሽ እናቴ ሆይ! እኔም በዚህ እምነት ተጽናንቼ ወዳንቺ እሮጣለሁ፣ በኃጢአቴም እየተጨ ነቅሁ በፊትሽ እቆማለሁ። የቃሉእግዚአብሔር እናት ሆይ ራርተሽ ቃሌን ስሚ አድምጪ እንጂ ችላ አትበይኝ። አሜን።

ጸሎት ወደ ቅድስት ቤተሰብ

ኢየሱስ ማርያም ዮሴፍ ልቤን፣ ነፍሴን፣ ሕይወቴን አሰጣችኋለሁ፣
ኢየሱስ ማርያም ዮሴፍ በሞት ጊዜ እርዱኝ፣
ኢየሱስ ማርያም ዮሴፍ በእቅፋችሁ በሰላም ልሙት። አሜን።

«እርሱ ብቻ ፕበበኛ ስሆነው ለጌንደ ስምላክ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም ምስጋና ይሁን፣ ስሜን» (ሮሜ.16: 27)